ክፍል አንድ

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ

መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ምን ማለት ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ሐረግ ‹‹መጽሐፍ›› እና ‹‹ቅዱስ›› ከሚሉት ቃላት የተገኘ ሐረግ ሲሆን መጽሐፍ የሚለው ቃል ተጠቃሎ በአንድ ጥራዝ ስር የተሰበሰበ ጽሑፍን ሲገልፅ ቅዱስ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ክዳሽ በሱርስት ካዲሽ በግዕዝና በዐረብኛ የተለየ ማለት ነው ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ ማለት በአንድ ጥራዝ ስር የተሰበሰበ የተለየ ፅሁፍ ማለት ነው
መጽሐፍ ቅዱስን የሚከተሉት ስድስት ጠቅለል ያሉ ምክንያቶች ቅዱስ ወይም ልዩ ያደርጉታል፡፡

ሀ) በእግዚአብሔር መንፈስ የተነሳሱ ሰዎች የጻፉት በመሆኑ

ለመጽሐፍ ቅዱስ ባለቤቱ ወይም አስገኝው እግዚአብሔር በመሆኑ ከሌሎች ይለያል፡፡ ይህንንም የእግዚያብሔር ባለቤትነት ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ሲል ይነግረናል ‹‹በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም›› ት.ኢሳ 34÷16 የመጽሐፍ ቅዱስ ባለቤቱ እግዚአብሔር ነው ማለት በርሱ ተጽፎ በአንድ ጊዜ ከሰማይ የተሰጠ ማለት ሳይሆን በተለያዩ ዘመናት ባስነሳቸው ቅዱሳን ላይ በፀጋ አድሮ የሚፅፉትን እያመለከታቸው የተፃፈ ነው ማለት ነው፡፡ዘፀ 17÷14 ‹‹እግዚአብሔርም ሙሴን የአማሌቅን ዝክር ከሰማይ በታች ጨርሼ እደመስሳለሁና ይህን ለመታሰቢያ በመጽሐፉ ፃፍ በኢያሱም ጆሮ ተናገር አለው››፡፡ 2 ኛጴጥ 1÷20-21 ‹‹በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፣ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ››ዮሐ.ራዕ 1÷11 ‹‹የምታየውን በመጽሐፍ ፅፈህ ወደ ኤፌሶን፣ወደ ሰርሞኔስ፣ወደ ፌላደልፌያ፣ወደ ሎዶቅያም በእስያ ወዳሉት ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ላክ አለኝ››እንዲል፡፡

ለ) በዕድሜው

ከመጽሐፍ ቅዱስ ቀድሞ ወይም በፊት የተፃፈ መጽሐፍ ባለመኖሩ በእድሜ ባለፀጋነቱ ልዩ ያደርገዋል፡፡

ሐ) የሰው ልጅ ከመፈጠሩ በፊት ስለለው ሁኔታ በእርግጠኛነት የሚናገር በመሆኑ

መጽሐፍ ቅዱስን መጻፍ የተጀመረው ከ 1486 ዓ.ዓ ጀምሮ ሲሆን ጸሐፊዎች ግን ከእነርሱ በፊት ስለተደረገው ድርጊት በእርግጠኛነት እንደተናገሩ እናያለን፡፡ ሊቀ ነብያት ሙሴ የኦሪት መጻሕፍትን የፃፈው ከ 3800 ዓ.ዓ በኋላ ወይም ከክርስቶስ ልደት (1700 ዓመት 11300 ዓመት የሚሉም አሉ) በፊት ሲሆን ይህን ያህል ብዙ ሺህ ዓመት አስቀድሞ ስለተፈፀመ የስነ-ፍጥረት ስራ ሲጽፍ ግን በይሆናል ወይም በግምት ሳይሆን በእርግጠኛነት ነው፡፡ ዘፍ 1÷1 ‹‹እግዚአብሔር በመጀመርያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ፡፡›› በተጨማሪም የሰው ልጅ ከተፈጠረ በኋላ ፀሐፊው ከነበረበት ዘመን በፊት ስለለው ሲናገርም እንዲሁ በእርግጠኛነት ነው፡፡ለምሳሌ ዘፍ 12÷1 ‹‹እግዚአብሔር አብርሃምን አለው ከሀገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ፡፡››

መ) ወደ ፊት ስለሚመጣው በእርግጠኝነት የሚናገር ስለሆነ

ሌሎች መጻሕፍት ወደፊት ስለሚመጣው ነገር የራሳቸውን መለምት በጥናትና በምርምር አልያም በግምት እንዲህ ‹‹ሊሆን ይችላል›› ቢሉ እንጂ እንዲህ ይደረጋል በማለት በእርግጠኝነት አይናገሩም፡፡ለምሳሌ ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ ‹‹እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች፡፡›› አለ እንጂ ‹‹ትፀንስ፤ትወልድ ይሆናል፤አማኑኤል ሊባልም ይችላል›› አላለም፡፡ ኢሳ 7÷14 ነቢዩ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ትንቢት የተፈፀመው እርሱ ከተናገረ ከ 700 ዓመት በኋላ ሲሆን ከቃሉ ምንም ሳይፈፀም የቀረ የለም፡፡እንዲሁም ቅዱስ ዳዊት ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት በእርግጠኝነት ‹‹ ከክብሩ ውበት ከጽዮን እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል›› አለ እንጂ ‹‹ ይመጣ ይሆናል›› ወይም ‹‹ ሳይመጣ አይቀርም፡፡›› አለለም፡፡ መዝ 49÷2

ሠ) የሚያነብቡትንና የሚሰሙትን ስለሚባርክ

ሌሎች መጻሕፍትን በማንበብ ዕውቀት ይገኛል መጽሐፍ ቅዱስን በማ”በብ እና ቃሉን በመስማት ግን ቡራኬ ይገኛል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የሚመክር፣ የሚገስፅና የሚያረጋጋ መምህር ነው፡፡ ራእ 1÷3 2 ጢሞ 3÷17 ራእ 3÷15-19

ረ) ዘመን የማይሽረው በመሆኑ

‹‹የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች፡፡›› በማለት መጽሐፍ ቅዱስ የማያረጅ የዘመን ብዛት የማይገታው ዘላለማዊ መሆኑን ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ ሲነግረን ት.ኢሳ 40÷8 መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ‹‹ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም፡፡›› ሲል መናገሩ መጽሐፍ ቅዱስ ከተፃፈ ብዙ ጊዜ ሆኖታል በዚህ ጊዜ አይሠራም የማይባል ሰማይና ምድር እንኳን ሲያልፍ እርሱ ፀንቶ የሚኖር መሆኑን ያስረዳል፡፡ማቴ 24÷35 ቅዱስ ጴጥሮስም ‹‹የጌታ ቃል ለዘላለም ይኖራል፡፡›› ብሎ እነደተናገረ ቃለ እግዚአብሔርን ዘመን አይሽረውም 1 ኛ ጴጥ 1÷25

መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ቅዱስ ተባለ?

ሀ) ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ‹‹ሀ›› እስከ ‹‹ረ›› በተዘረዘሩት ምክንያቶች ከሌሎች መጻሕፍት ሁሉ የተለየ በመሆኑ ቅዱስ ነው፡፡

ለ) አሰገኝው እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ቅዱስ ተብሏል፡፡

የእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ ቅዱስ ነውና፡፡‹‹እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ፡፡›› ዘሌ 19÷2 ሰዎች ከእግዚአብሔር ሲለዩ ማለትም እግዚአብሔር ለተለየ ሥራ ሲመርጣቸው ቅዱስ ይባላሉ ለዚህም ነው እግዚአብሔር ሊቀ ነቢያት ሙሴን ዘጸ 28፡40-41‹‹ለአሮን ልጆች ሸሚዞችን መታጠቂያዎችንም ቆቦችንም ለክብርና ለጌጥ ታደርጋቸዋለህ ይህንም ሁሉ ወንድምህን አሮንን ከአርሱም ጋር ልጆችህን ታለብሳቸዋለህ በክህነት እንዲያገለግሉ ትቀባቸዋለህ ትቀድሳቸውማለህ››

ሐ) ሰውን ወደ ቅድስና የሚያደርስ ስለሆነ ቅዱስ ተብሏል

መጻሕፍትን አምኖ መቀበል የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት ነው ወደ ፅድቅ ለመድረስ አስቀድሞ ማመን ያስፈልጋል ‹‹እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው››እንደተባለ ሮሜ 10÷17 እምነትን ለመያዝ ደግሞ ቃለ እግዚአብሔር መስማት ቀዳሚው ነገር ነው እንዲሁም ‹‹ባልሰሙት እንዴት ያምናሉ ያለ ስባኪስ እነዴት ይሰማሉ፡፡›› ሮሜ 10÷14 ቃለ እግዚአብሔር የሚጠብቁትን ሁሉ ወደ ቅድስና ያደርሳል፡፡ለዚህም ነው ለነባቤ መለኮት /ታኦሎጎስ/ ለቅዱስ ዮሐንስ ‹‹የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁዕ ነው፡፡›› ራእ 22፡7 ሲል አምላካችን እግዚአብሔር የገለጠለት፡፡

መ) ክብረ ቅዱሳን የሚዘክር ስለሆነ ቅዱስ ተብሏል፡፡

ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም
ስለ ቅዱሳን መለአክት
ቅዱሳን ፃድቃን ሰማዕታት
ስለ ቤተ መቅደስ ስለነዋያተ ቅድሳት ስለ ተቀደሱ ዕለታት.... ወዘተ የሚናገር ስለሆነ ቅዱስ ተብሏል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ይጠቅማል?

የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅም ዘርዝሮ መዝለቅ ባይቻልም ጠቅለል ባለ መልኩ የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

አንደኛው፡- የሰው ልጅ እንዲመራበት

‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታመኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተፅፏል›› ዮሐ 20÷31 መጽሐፍ ቅዱስ እውነትን ከሐሰት ብርሃኑን ከጨለማ ደጉን ከክፋ ለይተው ያውቁበታል፡፡

ማህቶተ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ለመንፈስ ቅዱስ ልጁ ለቅዱስ ጢሞቴዎስ ‹‹ነገር ግን ክፋዎች ሰዎችና አታላዮች እየሳቱና እያሳቱ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ፡፡አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ፀንተህ ኑር ከማን እነደተማርኸው ታውቃለህና ከህፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስ በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቀሃል፡፡ የእግዚአብሔር ሰው ፍፁምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በፅድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡››2 ጢሞ 3፡16 በማለት ዘርዝሮ ነግሮታል

ሁለተኛው፡- የእግዚሐብሔርን ትዕዛዝና ፈቃድ ለማወቅ

‹‹እኔ ያዘዝኋችሁን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትጠብቃላችሁ እንጂ ባዘዝኋችሁ ላይ አትጨምሩም ከእርሱም አታጎድሉም››በማለት ከምድራዊና ከሰው ፈቃድ ጋር እንዳንቀላቅለው የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ፈቃድ ያሳውቀናል፡፡ ዘፍ 4፡2 ፈቃዱን አስመልክቶ ደግሞ ‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶታልና ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አላከውምና፡፡›› ዮሐ 3÷16

ሦስተኛው፡- ስለ እግዚአብሔር መግቦትና ሕልውና ለማወቅ

መግቦት ማለት ሥልጣንን አገዛዝን ጥበቃን የሚያጠቃልል ቃል ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ
ስለ እግዚአብሔር ሥልጣን ‹‹በሰማይና በምድር በባህርና በጥልቆች ሁሉ እግዚአብሔር የወደደውን ሁሉ አደረገ፡፡›› መዝ 134÷6
ስለ ገዢነትም ‹‹እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ መንግስቱም ሁሉን ትገዛለች፡፡›› መዝ 102÷19
የእግዚአብሔር ጥበቃን አስማልክቶ ‹‹እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል፡፡›› መዝ 126፡1
መጽሐፍ ቅዱስን ማን ጻፈው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ባለቤቱ እግዚአብሔር ሲሆን ፀሐፊዎቹ ግን ከእርሱ የተላኩ ቅዱሳን ሰዎች ናቸው፡፡ብዛታቸውም ከ 40 በላይ ሲሆን አንዳቸውም እንኳን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አልፃፉም፡፡ ት.ኤር 36÷2 ‹‹አንድ የመጻሕፍት ክርታስ ውሰድ ለአንተም ከተናገርሁበት ቀን ከኢዮስያስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በእስራኤልና በይሁዳ ላይ በአህዛብ ሁሉ ላይ የተናገርሁህን ቃል ጻፍበት›› ‹‹ በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ፡፡›› 2 ኛ ጴጥ 1÷20-21 ‹‹የምታየውን በመጽሐፍ ጽፈህ ወደ ኤፌሶንና ወደ ሰርምኔስ ወደ ጴርጋሞንም፤ወደ ትያጥሮንም ወደ ሰርደስም ወደ ፊልድልፍያም፤ወደ ሎደቅያም በእስያ ወዳሉት ወደ ሰባቱ አብያት ክርስቲያናት ላክ አለኝ›› ራእይ 1÷11

መጽሐፍ ቅዱስን ከጻፉት ውስጥ ካህናት ነቢያት ነገስታትና ገበሬዎች ይገኙበታል፡፡

ብሉይኪዳን

ኤርሚያስ ሕዝቅኤል ዘካሪያስ ፡- ካህናት
ሳሙኤል ኢሳይያስ ዳንኤልና ሆሴዕ ፡- ነቢያት
ዳዊት ሰሎሞን ፡- ነገስታት
አሞጽ ፡- ገበሬ/አረኛ/

ሐዲስ ኪዳን

ቅዱስ ጴጥሮስ ያዕቆብና ዮሐንስ ፡- ዓሣ አጥማጆች
ሉቃስ ፡- ሐኪም
ቅዱስ ማቴወስ ፡- ቀራጭ/ግብር ሰብሳቢ/

መጽሐፍ ቅዱስ መቼና የት ተጻፈ?

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ሰዎች እንደተፃፈ ሁሉ፤ የተፃፈበት ዘመንና ቦታ እንዲሁ የተለያየ ነው፡፡*የመጀመሪያው መጽሐፍ መጽሐፈ ሄኖክ* ከተፃፈበት *1486* ዓ.ዓ ጀምሮ የመጨረሻው *ዮሐንስ ራእይ እስከተፃፈበት እስከ 98 ዓ.ም* ድረስ መጽሐፍ ቅዱስን ለመፃፍ *4100* ዓመት በላይ ወስዷል ማለት ነው፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት	የተፃፈባቸው ቦታዎች
የአሪት መጻሕፍት	ሲና ምድረ በዳ
መጽሐፈ ኢያሱ	ምድረ ከነዓን (እስራኤል)
መጽሐፈ አስቴር	ፋርስ
ትንቢተ ዳንኤል	ባቢሎን
የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት	ሮም
ዮሐንስ ራእይ	ፍጥሞ ደሴት

በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ ያሉ መጻሕፍት ስያሜ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ መጻሕፍት በፀሐፊዮች በይዘታቸው እና በክተሞች ስያሜ ተሰጥቷቸው እናገኛለን፡፡

ሀ.በፀሐፊው ስም የተሰየሙ

ምንም እንኳ በፀሐፊዎቹ ስም የተጠሩ ቢሆንም ቁጥራቸው ግን ከቅድሳት መጻሕፍት ነው፡፡በመጽሐፍ ቅዱስ በፀሐፊው ስም ከተሰየሙት ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል ፦

መ.ሄኖክ . የቅዱስ ዮሐንስ //
መ.ሳሙኤል . የቅዱስ ያዕቆብ //
መ.ዕዝራ . የቅዱስ ይሁዳ //

ለ.ከይዘታቸው በመነሳት ስያሜ የተሰጣቸው

ለምሳሌ፦ *ኦሪት ዘፍጥረት የተጻፈው በሊቀ ነቢያት ሙሴ* ሲሆን የሚጠራው ግን ኦሪት ዘፍጥረት ተብሎ ነው።ይህም የስነ ፍጥረትን ነገር የሚናገር በመሆኑ የተሰጠው ስም ነው።

ኦሪት ዘዳኦት፦ ዘዳኦት ቃሉ የግዕዝ ሲሆን ትርጉሙ *መውጣት* ማለት ሲሆን የእስራኤላዊያንን ከግብፅ ባርነት መውጣትን ይተርካል።

ኦሪት ዘሌዋውያን፦በዚህ ስም የተጠራበት ምክንያት የአሮን ልጆች ሌዋውያን በእግዚአብሔር ዘንድ ለክህነት የተመረጡ ነበሩ።ይህ መጽሐፍ ደግሞ ስለ/ሲመተ ክህነት/ ካህናት አኗኗም እና ሊፈፅሟቸው ስለሚገባቸው ሕግጋት የተፃፈ በመሆኑ ነው።

ኦሪት ዘኁልቁ ፤-ዘኁልቁ የግዕዝ ቃል ሲሆን *ቆጠራ* ን የሚያለክት ነው።መጽሐፉም ስለ እስራኤል ልጆች መቆጠር ስለሚተርክ ስያሜው ተሰጥቶታል።

መጽሐፈ መሳፍንት- በእስራኤል ስለተነሡት መሳፍንት የሚናገር

መጽሐፈ አስቴር፦ ፀሐፊው አጎቷ መርዶክዮስ ሲሆን የሚጠራው ግን በባለታሪኳ በአስቴር ነው።

ሐ.በፀሐፊውና በይዘታቸው /በሁለቱም/ የሚጠሩ

መኃልየ መኃልየ ዘሰለሞን -መኃልየ ማለት የመዝሙራት ሁሉ መዝሙር ማለት ነው።በይዘቱ ክርስቶስን፣ እመቤታችንና ቤተ ክርስቲያንን የሚያወድስ ነው።

ት.ኢሳያስ የማቴዎስ ወንጌል...ወ.ዘ.ተ ከዚህ ምድብ ይቆጠራሉ

መ.በከተማ ስም የተጠሩ መጻሕፍት

ከአሥራ አራቱ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ውስጥ ዘጠኙ በተላኩላቸው ከተሞች የተጠሩ ናቸው።

-ሮሜ - ፊልጵስዩስ
-ቆሮንቶስ 1ኛ ና 2ኛ - ቆላስያስ
-ተሰሎንቄ 1ኛ ና 2ኛ ናቸው -ገላትያ
-ኤፌሶን

ሠ,በተላኩላቸው ሰዎች ስም የተጠሩ

አንደኛና ሁለተኛ ጢሞቴዎስ፣ ቲቶ እና ፊልሞና በተላኩላቸው ሰዎች ስም የተጠሩ ሲሆን መልዕክቱ በተላከለቸው ወገኖች የተጠራው ደግሞ የዕብራውያን መልዕክት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት መጣ?

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ከሚገኙ ብዙ ሀገሮች ተለይታ በዘመነ ብሉይ እና በዘመነ ሐዲስ ሁለቱንም ኪዳናት በመቀበል ብቸኛ ሀገር ናት። ኢትዮጵያውያን በብሉይ ኪዳን ትዕዛዘ እግዚአብሔርን ከመስማት በተጨማሪ ለማንበብና ወደ ራሳቸው ቋንቋ ለመመለስ (ለመተርጎም) ችለዋል።ኢትዮጵያዊቷ ንግስት ማክዳ ከ ፪ሺህ ኪ.ሜ በላይ ተጉዛ የሰሎሞንን ጥበብ ልታደንቅ የሄደችው ከነበራት ፈሪሀ እግዚአብሔር የተነሳ ነው።ጥበብንም በዓይኗ ካየች በኃላ << በእምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ንጉስ እንድትሆን በዙፋኑ ላይ ያስቀምጥህ ዘንድ የወደደህ አምላክህ እግዚአብሔር ብሩክ ይሁን>> ስትል እምነቷን ተናግራለች። 2ኛዜና 9÷8፣1ኛነገ 10÷9 ጌታችንም ስለዚህ እምነቷ መስክሮላታል። ማቴ 12÷42

በ 1917 ዓ.ም የታተመው የመጽሐፈ ሰሎሞን ወሲራክ ትርጓሜ መግቢያ ላይ ደግሞ የሚከተለው ታሪክ ተፅፎ ይገኛል <<በ 4481 ዓ.ዓ ዳዊት ሞቶ ሰሎሞን ነገሰ ሰሎሞንም በነገሰ በ 4ኛው ዓመት የኢትዮጵያ ንግስት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደች ንግስት ማክዳ ከሰሎሞን የወለደችው ምኒልክ 22 ዓመት ሲሞላው ወደ አባቱ ሰሎሞን ላከችው ሰሎሞንም ልጁ መሆኑን ለእስራኤል ባስታወቀ ጊዜ ሕዝቡ ለሁለት ንጉስ መገዛት አንችልምና አንግሰህ ወደ እናቱ አገር ስደደው አሉት እርሱም የበኩር ልጅህን (የበኩር ልጅህን) ስደድ ካላችሁኝ እናንተም የበኩር ልጆቻችሁን አምጡ አላቸው አምጥተው ሰጡ ከዚህ በኃላ ሥርዓተ መንግስት አድርሶ ምኒልክን አንግሶ ከሄኖክ እርሡ እስከ ፃፋቸው ያሉትን መጽሐፍት ሰብስቦ እነዚህን መጻሕፍት ተርጉመው የሚያስተምሩ 318 ሌዋውያንን ጨምሮ ሰጥቶ ሰደደው እነርሡም ወደ ኢትዮጲያ መጥተው ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ መዕሐፍቱን መልሰው (ተርጉመው) አስተምረዋል>>

ስለዚህ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከክርስቶስ ልደት 900 ዓመት በፊት (ብሉይ ኪዳን በሰባው ሊቃውንት ወደ ፅርዕ-ግሪክ ከመተርጎሙ 600 ዓመት በፊት) በራሷ ቋንቋ (ግዕዝ) ቅዱሳት መጻሕፍትን መቀበሏንና መተርጎሟን እንረዳለን ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ በተመለሱት መጻሕፍት ላይ አንዳንድ የዕብራይስጥ ቃላት በቁማቸው መደጋገማቸው ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ የተመለሱ ለመሆኑ ማስረጃ ናቸው።ለምሳሌ

አዶናይ- ጌታ
ኤሎሄ- አምላክ
ጸባያት-ሠራዊት
ከሰሎሞን መጻሕፍት በኃላ የተፃፉት መጻሕፍት እንደት ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ በ 1917 ዓ.ም የታተመው መጻሕፍተ ሰሎሞን ወሲራክ ትርጓሜ መግቢያ ላይ የሚከተለው ተፅፎ ይገኛል ‹‹...ከቀውስጦስ ታሪክ መጽሐፍ ምስክር እናመጣለን በ 4905 ዓ.ዓ እስራኤል ተማርከው ፋርስ ባቢሎን ወረዱ ተማርክው ከሄዱ በኃላ በኢትዮጵያ ያሉ ሊቃውንት ከንጉሱ ጋር መክረው የጥያቄ መልእክት ለኩ ነገሩም እንዲህ ነው ‹‹ የእኛም የእናንተም አባቶች ነቢያት የፃፏቸው መጻሕፍት ተቃጠሉን ወይስ ድነዋል? እናንተስ እንደምን አለችሁ? ትሰግዳለችሁን? ሻራችሁን? የሚል ነው እነዚህም ይህን መልእክት በሰሙ ጊዜ እንዲህ ብለው መልሰዋል ‹‹እኛ በዳንኤል ፀሎት የአብርሃም ፈጣሪ ጠብቆን ደህና ናን መጻሕፍቱን ግን እንዳንፈልጋቸው በምርኮ ነው ያለን እናንተ ግን በፀጥታ በደስታ ነውና ያላችሁት ኢየሩሳሌም ወጥታችሁ ፈልጓቸው ነገር ግን ከተማረክን በኃላ ዳንኤል ከእግዚአብሔር አግኝቶ የጻፈውን መጽሐፍ ፅፈን ልከንላችኃልና ተቀበሉ›› ብለው መጽሐፈ ዳንኤልን ልከውላቸዋል፡፡ ይህም መጽሐፍ የመጣው አይሹር የሚባል የኢትዮጵያ ንጉስ ስለአስራኤል በፋርስ ንጉስ ዳርዮስ በአማለጅነት በለከዉ ሰዉ እጅ ነው፡፡

ይህንንም የዳንኤል መጽሐፍ ተቀብለው በሰሎሞን ጊዜ ከመጡ መጻሕፍት ጋር ደርበውታል፡፡ከምርኮ ከተመለሱ በ(ለ ዘሩባኤል በነገሰ ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉስ ከእናንተ ያሉትን መጻሕፍት ለኩልን እኛም እዚህ ያሉትን እንልክለች(ለን ብሎ ጠይቆ እነዛ የቀሩትን የነብያት መጻሕፍት እነዚህም ከሄኖክ ጀምሮ እስከ ሰለሞን የነበራቸውን መጻሕፍት ሁሉ ልከውላቸዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጲያዊው ጃንደረባ የነብዩ ኢሳያስን መጽሐፍ ይዞ ሲያነብ ከሐዋርያው ፍሊጶስ ጋር በጋዛ እንደተገናኙ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል፡፡የሐ.ስ 8፤26-40 ከዚህም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ኢትዮጵያውያን ክርስትናን ከመቀበላቸው በፊት በ(ን(ቸው ቅዱሳት መጻሕፍትን ተርጉመው ይመሩባቸውና ይጠቀሙባቸው እንደነበር እንረዳለን፡፡

ለሐዲስ ኪዳንም ኢትዮጵያ ሐዋርያት ለስብከተ ወንጌልና ገና ከሀገረ እስራኤል ሳይወጡ ከ 34 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጲዊው ጃንደረባ አማካኝነት ሀገ ወንጌል ተሰብኮላታል፡፡ምንም እንኳን ሕገ ወንጌል ሲሰብክ ቢቆይም የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ወደ ኢትዮጲያ የገቡት ግን በ 4 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን አማካኝነት ወደ ግዕዝ ተተርጉመው ነው፡፡ኋለም በ 5 ኛው መ/ክ/ዛ ወደ ሀገራችን የመጡት ተሰዓቱ ቅዱሳን (ዘጠኙ ቅዱሳን) የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በሙሉ ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተርጉመዋል፡፡
የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በኢትዮጵያ

በሀገራችን በኢትዮጲያ መጽሐፍ ቅዱስ አባ አብርሃም /አባ ሮሜ/ በተባለ መነኩሴ ሙሉ በሙሉ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሟል፡፡ ከነዚህም ውስጥ
1816 ዓ.ም፡- በራቱ ወንጌላት
1821 ዓ.ም፡- ሐዲስ ኪዳን
1832 ዓ.ም፡- ሙሉው መፅሐፍ ቅዱስ
1980 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሀይማኖት ፈቃድ በተለምዶ ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ እየተባለ የሚጠራው ታተመ፡፡
በአለቃ ተወልደ መድኃን፡- ወደ ትግረኛ
አናሲሞስ ነሲቦ፡- ወደ ኦሮሚኛ ተተርጉሟል፡፡
መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በምን ቋንቋ ተፃፈ?

አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተፃፉት በዕብራይስጥ ሲሆን ትንቢተ ዳንኤል የተፃፈው ግን በአረማይክ ቋንቋ ነው፡፡የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በዕብራይስጥ ከተፃፈው ከማቴዎስ ወንጌልና በሮማይስጥ ከተጻፈው ከማርቆስ ወንጌል ውጪ የተቀሩት የተፃፉት በዘመኑ በአብዛኛው ሕዝብ መነጋገሪያ በነበረው በፅርዕ/ግሪክ/ ቋንቋ ነበር፡፡
የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች

መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ 980 አካባቢ ወደ ግዕዝ ተተርጉሟል፡፡ምንም እንኳን ቅዱሳት መጻሕፍት በመጀመሪያ የተተረጎሙት ወደ ፅርዕ/ግሪክ/ ቋንቋ ነው የሚሉ ቢኖሩም ሰባው ሊቃውንት ቅዱሳት መጻሕፍቱን የተረጎሙት ከክ.ል.በፊት 284 ዓመት ዓለም በበጥሊሞስ ዘመነ መንግስት ነው፡፡በዚህም መሠረት ወደ ግእዝ ከተመለሰበት ጋር ሲነፃፀር በመካከላቸው የ 696 ዓመት ልዩነት ይታያል፡፡ስለዚህ የግሪኩ ትርጉም ሁለተኛ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡የግሪኩ ትርጉም ሴኙቱ አጊንት/የሰባው ሊቃውንት ትርጉም/ በመባል ይታወቃል፡፡ ኑክለስ እና ዮናታን (የአይሁድ ሊቃውንት) ብሉይ ኪዳንን ወደ አረማይክ ቋንቋ በ 4 ተኛው መ/ክ/ዘ በሄሮዲመስ ዘመነ መንግስት አባ ጀሮም ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ለ 40 ዓመታት የዕብራይስጥና የግሪክ ቋንቋዎችን ካጠና በኃላ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ሹልጌት ተርጉሞታል፡፡ ትርጉሙም ሹልጌት በመባል ይታወቃል፡፡ሹልጌት በሮም ይኖሩ የነበሩ <<ሹልገስ>> እየተባለ የሚጠሩ ሕዝቦች ቋንቋ ነው፡፡ አባጀሮም/ሄሮኒመስ/ መጽሐፍ ቅዱስን ከሹልገስ ወደ ላቲን እየተረጎመው ሳለ ዐረፈ፡፡ይህን የእሱን ጅምር ከእርሡ በኃላ የተነሡ ሰዎች እንዳጠናቀቁት ይነገራል፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ

ሀ.ትምህርተ ሃይማኖት ማስተማር

የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዓላማቸው ስለ እግዚአብሔር ሕልውና መግለጽና ነገረ ሃይማኖት ማስተማር ነው።ዮሐ 1፡1-14፤14፡ 10፤መዝ 105፡25 አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማያትም የእጅህ ስራዎች ናቸው።

ለ.የእግዚአብሔርን ቸርነት ድንቅ ስራውን ተዓምራቱን መግለጽ

1ኛ ነገ 13፡1 መዝ 50፡1 አቤቱ እንደቸርነትህ መጠን ማረኝ /፤መዝ 74፡7
ማቴ 26፡15 /ይሁዳ በ 30 ብር ለመሸጥ መስማማቱን/ ማቴ 8፡2 /ለምጻሙን እንዳነጻ/ ሉቃ 11፡45

ሐ.የእምነትን ታላቅነት መግለጥ

ለምሳሌ፡-
ሠለስቱ ደቂቅ በእምነት የእሳቱን ኃይል ማጥፋታቸውን
ዳንኤል በእምነት የአናብስቱ አፍ መዝጋቱ
ጌዴዎን ያለ ጦር መሳርያ በእምነት የአሕዛብ ሰራዊትን ድል ማድረጉን

መ.በእግዚአብሔር ያመኑ ቅዱሳንን ተጋድሎ መግለጥ

ምሳሌ፡-የነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር መስራት የአስቴር በጾም በጸሎት ሕዝበ እስራኤልን መታደግ

ሠ.ለሰው ሕሊና የሚከብዱ በእምነት ብቻ የምንረዳቸው ድርጊቶች መግለጥ

የኢያሱንፀሐይንገዝቶማቆምኢያሱ 10፡12፤ሉቃ 1፡37፤ማቴ 9፡23

ረ.የዘለዓለም ሕይወትን መስጠት ሰዎችን ወደ ድህነት /ንስሐ/መጥራት ነው

«የመማራችን ዓላማው የሕይወት ለውጥ ለማምጣት መሆን አለበት» አቡነ እስጢፋኖስ ሐዋ.ስራ 17፡3 « እውነተኛ አምላክ የሆንህ አንተን ብቻ የላኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት» መዝ 89፡3፤ሕዝ 18፡30፤ማቴ 3፡8
የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕልና ቋንቋ
መጽሐፍ ቅዱስ የራሱ የሆነ ባሕልና ዘይቤ አለው ይህም ለተጻፈለት ሰው፤ የጸሐፊውን ሁኔታና በተጻፈበት ቦታ ይወሰናል ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ባህሎችን ጠንቅቆ ሳያውቁ በራስ መተርጎም ለስህተት ይዳርጋል እንደ ራስ ባህልም ማሰብ አይገባም
ለምሳሌ፡- ወንድም የሚለው ቃል በመካከለኛ ምስራቅና በኢትዮጵያ ያለው ትርጉም አንድ ሲሆን በምዕራባዊያን ግን ትርጉሙ ሌለ ነው
በምዕራባዊያኑ ወንድም የሚባሉት
በአንድ ነገድ ልጅነት 2ኛ ሳሙ 19፡11
በዝምድና ዘጸ 36፡1
በባልንጀርነት 2ኛሳሙ 6፡26
በሃይማኖት ሕብረት ሮሜ 1፡13፤ፊል 1፡7፤3፡1
ዕብራዊያን ቃልን ደጋግመው መናገር ባህላቸውና ቃል ማጽኛ ነው
አብርሃም አብርሃም ዘፍ 12፡1
ሙሴ ሙሴ ዘጸ 3፡4
ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ማቴ 23፡37
ማርታ ማርታ ሉቃ 10፡41
«እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ከመንፈስ ቅዱስና ከውሃ ካልተወለደ ...» ዮሐ 3፡5 የዕብራዊያን የሰዓት አቆጣጠር ከ 11፡00 ሰዓት ጀምሮ እንደ ንጋት ይቆጠራል የእረኛ ጠባይ በኢትዮጵያ ልማድ ከሚጠብቋቸው በጎች ከኋላ እየነዳ የሚሄድ ሲሆን በእስራኤል ከፊት ከፊት እየመራ ይሄዳል የስም አወጣጥ የአነጋገር ዘይቤ ማኅበራዊ ኑሮ እንዲሁም የአጻጻፍ ስልት እንደ ሕዝቡ ባህል ስለሚለያይ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ስለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚንጸባረቀውን ባህል ለይቶ ለማወቅ ያስፈልጋል
የመጽሐፍ ቅዱስ መልክዓ ምድር
በመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ድርጊቶች የተፈጸሙባቸው ህዝቦች ሀገሮች ባህሎች ተራሮች ወንዞች ወ.ዘ.ተ ይገኛሉ እነዚህ ሁሉ ግን በየራሳቸው ታሪክ ምሳሌና ትርጉም አላቸው።ነገር ግን ይህን ሁሉ ለመረዳት በመካከለኛው ምስራቅ በተለይም የእስራኤልን ባህል ማወቅ አስፈላጊ ነው።
ሀገረ እስራኤል የተመረጠችበት ምክንያት ምን እንደሆነ ሙሉ ለሙሉ ማወቅ ባይቻልም፡-

1.የሀገሪቱ መልክዐ ምድር ከሚያስደስቱ የዓለም ገጽታዎች መመደቡ (ውብ በሆነ ፀጋ ላይ ሃይማኖታዊ ፀጋ ታክሎ ልዩ ስፍራ ስለሰጣት)
2.የመጀመሪያ ሰው አዳም መኖሪያና መቀበሪያ ስትሆን ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው ያደገው ዞሮ ያስተማረው ተአምራቱን የፈጸመው የሞተው የተነሳውና ያረገው በዚህ ቦታ ነው።
3.በዘመነ ብሉይም ሆነ ሐዲስ በሺህ ለሚቆጠሩ አመታት የአፍሪካ የአውሮፓና የእስያ የንግድ አገናኝ መስመር በመሆኗ
4.ማዕከለ ምድር በመሆኗ
5. አጽመ አዳም ያለበትበመሆኗ

አዋልድ መጻሕፍት

ጥሬ ትርጉሙ የመጻሕፍት ልጆች ማለት ነው። ልጅነታቸው ለአሥራው መጻሕፍት ነው አሥራው መጻሕፍት የሚባሉትም ቁጥራቸው ሰማንያ አንድ የሆኑት አምላካውያት መጻሕፍት ናቸው። አሥራው መጻሕፍትን የሚተረጉሙ የሚተነትኑ ሚስጥሩን አራቅቀው ትርጓሜውን አቃንተው የሚያቀርቡ በነቢብ የተገለጠውን በገቢር በትምህርት የተሰጠውን በሰው ሕይወት የሚያሳዩ መጻሕፍት አዋልድ መጻሕፍት ይባላሉ በመሆኑም በሚስጥርም በትምህርትም ከአሥራው መጻሕፍት የሚቃረን መጽሐፍ ከአዋልድ መጻሕፍት አይመደብም አይቆጠርም ምክንያቱም በሐዋርያው ቃል «ነገር ግን እኛ ብንሆን ዌም ከሰማ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብኩላችሁ የተረገመ ይሁን።»ተብሏልና ገላ 1፥9

የአሥራው መጻሕፍትና የአዋልደ መጻሕፍት ግንኙነት

በአይነታቸው	አሥራው መጻሕፍት	አዋልድ መጻሕፍት
የሕግ መጻሕፍት	-አምስቱ ብሔረ ኦሪት	
	መጽሐፈ ኢያሱ	
	መጽሐፈ መሳፍንት	ፍትሐ ነገስት
	መጽሐፈ ሄኖክ	
	መጽፈ ኩፋሌ	
የታሪክ መጻሕፍት	-መጽሐፈ ሳሙኤል	
	መጽሐፈ ንግስት	
	ዜና መዋዕል	ተአምረ ማርያም
	መጽሐፈ ዕዝራ	ገድለ ተክለሃይማኖት
	መጽሐፈ ነህምያ	
	መጽሐፈ መቃብያን	
	መጽሐፈ ሳሙኤል	
የጥበብ የምስጋና መጻሕፍት	-መዝሙረ ዳዊት	
	መጽሐፈ ሲራክ	ውዳሴ ማርያም
	መጻሕፍተ ሰለሞን	መጽሐፈ ሰዓታት
የትንቢት መጻሕፍት	-የነቢያት ትንቢት የያዙ መጻሕፍት	ፍካሬ ኢየሱስ

2.በባለቤታቸው፡- ቅዱሳት መጻሕፍት ባለቤታቸው ቅድስት ቤተክርስቲያን ናት። ከእግዚአብሔር የተላኩ ቅዱሳን መንፈስ ቅዱስ ገልጦላቸው መጽሐፍ ቅዱስንና አዋልድ መጻሕፍትን የጻፉት ለቤተክርስቲያን ልጆች ለምእመናን ነው። በመሆኑም ባለቤታቸው ቤተክርስቲያን ስለሆነች ለትርጉማቸው፣ ለታሪካቸውና ለምስጢራቸው ሁሉ መጠየቅ ያለባት ቤተክርስቲያን ናት።
3.በቅድስናቸው፡- አሥራው መጻሕፍትንም ሆነ አዋልድ መጻሕፍትን ያጻፈው መንፈስ ቅዱስ ነው። የአሥራው መጻሕፍትን ጸሐፍት እንደመረጠ እንዳተጋ ምስጢር እንደገለጠላቸው የአዋልድ መጻሕፍት ፀሐፍትንም የመረጠ ያተጋ ምስጢሩን የገለጠላቸው መንፈስ ቅዱስ ነው።

አሥራው መጻሕፍት ስለ አዋልድ መጻሕፍት ምን ይላሉ

መጽሐፍ ቅዱስ /የአሥራው መጻሕፍት/ ራሱ እርሱን ምሉዕ ሊያደርጉ የሚችሉ የጎደለውን የሚሞሉ የሚያብራሩ መጻሕፍት መኖራቸውን ይገልጣል።ለአብነት ያህልም የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መመልከቱ ይጠቅማል።
1.በ2ኛው ሳኤል 1፥18-27 የተጻፈው የዳዊት መዝሙር ከያሻር መጻሕፍት የተወሰደ ነው። ያሻር ደግሞ ከአሥራው መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ አልተካተተም። ይሁን እንጂ ሁለቱም በመንፈስ ቅዱስ የተጻፉ በመሆናቸው ቃሉ እንዳለ ተወስዷል።

2.ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን ጽፎ ሲያበቃ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል ያልተጻፉ ብዙ ትምህርት እንዳስተማረ ብዙ ተአምራትንም እንዳደረገ ነገር ግን የተጻፈው ሰዎች የክርስቶስን የባህርይ አምላክነት ለመረዳት እንዲችሉ ያህል መሆኑን ገልጾ እንዲያውም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውን ሁሉ እያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ እንደማይበቃቸው ያስረዳሉ። ዮሐ 20፡30-31፣ 21፡25

3.አሥራው መጻሕፍት (መጽሐፍ ቅዱስ) በእነርሱ ያልተገለጹትን እውነታዎች፣ ምስጢራት፣ ታሪኮች ከሌሎች ማለትም አዋልድ መጻሕፍት መገኘታቸውን ያስረዳሉ። ለዚህም የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መመልከት ይጠቅማል። 1ኛ ነገ 11፡41፣ 14፡29፣ 2ኛ ዜና 9፡29፣ 12፡15፣ 20፡34 እንዲሁም ሐዋርያው ይሁዳ በመልእክቱ ም 1፡8-10 ላይ የገለጠው ታሪክ ከአዋልድ መጻሕፍት ወገን ከሆነውና ‹‹ዜናሁ ለሙሴ›› ከተባለው መጽሐፍ ተወሰደ ነው።

የአዋልድና አሥራው መጻሕፍት የይዘት አንድነት

የእግዚአብሔርን ስራ መግለጥ
ለሰው ኅሊና የሚከብዱ በእምነት ብቻ የምንረዳቸው ድርጊቶችን መግለጥ
የእምነትን ታላቅነት መግለጥ
በእግዚአብሔር ያመኑ ሰዎች ደረጉትን ተጋድሎ መግለጥ
ትምህርተ ሃይማኖትን ማስተማር

የአዋልድ መጻሕፍት አከፋፈል

መጻሕፍተ ሊቃውንት፡- ከሁለተኛው መ/ክ/ዘመን ጀምሮ በተነሱ ቅዱሳን ሊቃውንት የተጻፉ ናቸው። ሃይማኖትን ለመግለጽ ለተነሱ መናፍቃን መልስ ለመስጠት በስድ ጽሑፍ፣ በጥያቄና መልስ ዓይነት የተጻፉ ናቸው። በአሥራው መጻሕፍት የተገለጡትን ምስጢረ ሥላሴን፣ ምስጢረ ሥጋዌን፣ የቅድስት ድንግል ማርያምንና የቅዱሳንን ክብርና አማላጅነት በስፋትና በጥልቀት የሚያስረዱ ናቸው።
ምሳሌ፡- ሃይማኖተ አበው - ቄርሎስ
መጽሐፈ ምስጢር - ዮሐንስ አፈወርቅ መጻሕፍት
መጻሕፍተ መነኮሳት፡- የመነኮሳትን ሥራቸውን፣ ተጋድሎአቸውን፣ ክብራቸውን፣ አጠቃላይ በምንኩስና ሕይወታቸው ሊኖራቸው የሚገባውን አኗኗር የሚናገር መጽሐፍ ሲሆን ሦስት ክፍሎች አሉት
ማር ይስሐቅ
ፊልክዮስ
አረጋዊ መንፈሳዊ ናቸው
የሕግና የስርአት፡-
የሕግ መጻሕፍት፡- በመንፈሳዊ ሕይወት ላለ ሰው የሚደረጉና የማይደረጉ፣ የተፈቀዱና የተከለከሉ ነገሮችን የሚናገሩ ናቸው። ከዚህ ክፍል ከሚመደቡ መጻሕፍት መካከል አንዱ ፍትሐ ነገሥት ሲሆን ሁለት ክፍሎች አሉት። እነርሱም ፍትሀ መንፈሳዊና ፍትሕ ሥጋዊ ይባላሉ።
የሥርዓት መጻሕፍት፡- በሕግ በተደነገገው መሠረት በቤተ ክርስቲያን፣ በምእመናን ዘንድ የሚፈጽሙ ጉዳዮችን ሂደትና ቅደም ተከተል እንዲሁም አፈጻጸም የሚያሳዩ ናቸው።
ምሳሌ፡- ሥርዓተ ቤተክርስቲያን፣ ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ሥርዓተ ምንኩስና የመሳሰሉት ናቸው።
የጸሎት መጻሕፍት፡- ውዳሴ ማርያም፣ መጽሐፈ ቅዳሴ፣ መጽሐፈ ተክሊል፣ መጽሐፈ ግንዘት የመሳሰሉት ናቸው።
የዜማ መጻሕፍት፡- የሚባሉት በቤተ ክርስቲያን በማህሌት፣ በሰዓታት ለምስጋና የሚያገለግሉ ናቸው። በቅዱስ ያሬድና በአባ ጊዮርጊስ ከተደረሱት የቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤ/ክ ዜማ መጻሕፍት ለአብነት ያህል የሚከተሉት ይተቀሳሉ።
ድጓ ጸመ ድጓ፣ ምዕራፍ ዝማሬ፣ መዋሥዕት፣ መጽሐፍት ሰዓታት ወ.ዘ.ተ

ድርሳናት፡- ድርሳን ስለአንድ ነገር የተጻፈ ፅሑፍ፣ ሀተታ ማለት ነው። ድርሳናት የቅዱሳን መላእክትን ክብርና አማላጅነት፣ ተራዳኢነት፣ የሰንበትን ክብር፣ ልዕልና የሚገልጡ እንዲሁም በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተንተርሰው የጻፏቸውን ይይዛል።
ምሳሌ፡- ድርሳነ መላእክትድርሳነ ሚካኤል፣ ድርሳነ ገብርኤል
ድርሳነ ሰንበት፡- ስለ ሰንበት ክብር የሚናገር
ድርሳነ ሊቃውንት፡- ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ድርሳነ አትናቴዎስ፣ ድርሳነ ኤፍሬም
ከዚህ በተጨማሪ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም በሥጋ በተገለጠ ጊዜ በለያዩ ቦታዎች ለተለያዩ ሰዎች ያስተማረውን ትምህርት፣ ደረገውን ተአምራት የሚገልጡ እንዲሁም በአይሁድ እጅ የመያዙን ሕመሙን ሞቱን ትንሳኤውን የሚናገሩ ድርሳናት አሉ።
እነዚህም
ድርሳነ ማሕየዊ
ድርሳነ መስቀል

ድርሳነ ብርሃን
ኖለዊ ናቸው
ገድላት፡-የእግዚአብሔር ወዳጆች የሆኑ ቅዱሳን፣ ጻድቃን፣ ሰማእታት ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ስለእግዚአብሔር አምልኮት ስለሕጉና ፈቃዱ መጠበቅ ብለው ከአላውያን ነገስታት፣ ከቢጽ ሀሳውያን ከዚህ ዓለም ገሸር ከዲያቢሎስና ከሥጋ ፈቃድ ጋር የፈጸሙትን ተጋድሎ የሚናገሩ ናቸው፡፡ የቅዱሳንን ገድል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ነው፡፡ 2ኛ ቆሮ 11፡23-27፣ ዕብ 11፡32-40 የሐዋርት ስራ የተባለው መጽሐፍ የሳሩያን ሐዋርያትን ዜና፣ ግብር፣ ገድል የሚያስረዳ መጽሐፈ ገድል ነው፡፡
ገድለ ሰማዕታት፣ ሀዋርያት፣ ቅዱሳን
የቁጥር መጻሕፍት፡- የዘመን አከፋፈልና አቆጣጠርን፣ የአጽዋማነትንና የበዓላትን መዋይ ዕለታት የሚወሰኑ ነገረ ቀመሮችን የያዙ ናቸው፡፡
ምሳሌ፡- አቡሻህር ባሕረ ሀሳብ የመሳሰሉት ናቸው
ክፍል ሁለት
የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት
ብሉይ ኪዳን
-የቆየ፣የጥንት ውል ወይም ስምምነት ማለት ነው፡፡
-የአንድ አምላክ አማኞች የዕብራዊያንን ታሪክ ይተርካል፡፡
-ስለ መሲኽ ክርስቶስ መምጣት የተነገሩት ትንቢቶች በብዛት አሉበት፡፡
ብሉይ ሲባል ሀጉ ወይም ቃል ኪዳኑ ሁሉ ያረጀ ነው ማለት አይደለም፣ግን ዘመኑ አርጅ(ል ብዙ ጊዜም አልፋል ስለዚህም በዚህ ዘመን የነበረ መሆኑን ለማስረዳት ሲል ብሉይ ኪዳን ይለዋል፡፡
የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከተፃፉበት ጊዜ፣በያዙት ሀሳብና ከአፃፃፋቸው ሁኔት አንፃር በአራት ምድቦች ይከፈላሉ፡፡ እነርሡም፡-
የሕግ/የኦሪት/መጽሐፍት
የታሪክ መጽሐፍት
የመዝሙርና የጥበብ መጽሐፍት
የትንቢት መጽሐፍት ናቸው፡፡
1.የሕግ መጻሕፍት
-የኦሪት መጻሕፍትም በመባል ይታወቃሉ፡፡ኦሪት ቃሉ የሱርስት ሲሆን ብርሃን ማለት ነው፡፡
-በዕብራይስጥ ቶራ
-በግሪክ/ፅርዕ/ ፍምስ ይባላል ትርጉሙም ሕግ ማለት ነው በቁጥር አምስት ሲሆኑ ፀሐፊውም ሊቀ ነቢያት ሙሴ ነው፡፡እነዚህም መጻሕፍት እንደየይዘታቸው የተለያየ ስያሜ ተሰጥታቸዋል፡፡
1.ኦሪት ዘፍጥረት/ዘልደት/
-የሰነ ፍጥረትን ልደት፣አጀማመርና አመጣጥ የሚያስረዳ በመሆኑ ይህን ስያሜ አግኝቷል፡፡ከህግ መጻሕፍትም ሲፃፍ የመጀመሪያው ነው፡፡50 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን የመጽሐፉን ይዘት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፍለዋል
ከምዕራፍ 1-5
ስለዓለም አፈጣጠር፣የሰው ልጅ በኃጥያት ስለመውደቁና ስለመጀመሪያዎቹ አባቶች በዝርዝር ቀርቧል፡፡እንዲሁም ለሰው ልጅ የተሰጠውን የፈቃድና የፍላጎት ነፃነትንም ያመለክታል፡፡
ከምዕራፍ 6-11
የሰው ልጅ ኃጥያት መብዛት በንፍር ውሃ እንዲጠፋ መሆን\የባቢሎን ግንብ በመስራታቸው ቋንቋቸውን እግዚአብሔር እንደ ደባለቀባቸው ተመልክቷል፡፡
ከምዕራፍ 12-26
የአብርሃምን መጠራት፣የይስሐቅ ልጆችን ያዕቆብንና ዔሳውን ያነሳል፡፡
ከምዕራፍ 27-50
በሰፊው የያዕቆብን ታሪክ ይይዛል፡፡
-ብኩርናን እንዳገኘ
-በህልሙ ስለተገለጠለት ሰማያዊ ምስጢር
-ጋብቻን ስለመመስረቱ ተብራርቶ ይገኛል፡፡
-እግዚአብሔርም ቃል ኪዳን እንደገባለት
2.ኦሪት ዘጸአት
‹‹ጸአት›› የግእዝ ቀል ሲሆን ትርጉሙም መውጣት ማለት ነው፡፡40 ምእራፎች ሲኖሩት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች መክፈል ይቻላል፡፡
ከምዕራፍ 1-4

ግብፃውያን በእስራኤላውያን ላይ ስለፈፀሙት የግፍ አገዛዝ
ስለ ሙሴ ልደትና፤በሚነደው ቁጥቋጥ ውስጥ የሙሴ መጠራትና ወደ ግብፅ ተመልሶ ወገኖቹን ከባርነት ነፃ እንዲያወጣ ከእግዚአብሔር ስለመታዘዙ የሚያወሳ ነው።።
ከምዕራፍ 5-11
-ሙሴና አሮን በፈርዖን ፊት ስለመቆማቸው፤ በእስራኤላውያን ላይ የባርነት ቀንበር ስለመጥበቁ ።።
- በግብፆች እምቢተኝነት ምክኒያት በግብፅ ህዝብ ላይ ስለደረሱት ዐስር ተከታታይ መቅሰፍቶች።።
ከምዕራፍ 12-15
-ስለ እስራኤል ከግብፅ መውጣትና እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ድንቅ ስራ በማየታቸው ለአምላካቸው የምስጋና መዝሙር ማቅረባቸውን የመለክታል።።
ከምዕራፍ 16-40
-በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ ዐሥሩጹን ትእዛዛት የተግፋብትን ፅላት መስጠቱ
-እስራኤል የወርቅ ጥጃ ሰርተው ስለማምለካቸውና እንደገና የቃል ቂዳኑ ሕግ ስለ መምጣቱ

3.ኦሪት ዘሌዋውያን
-ሌዋውያን ከ 12 ቱ የእስራኤል ነገድ የአንዱ የሌዊ ዘር ናቸው።።የብሉይ ኪዳን ካህናት ሌዋውያን ስለነበሩ፣ ስለ ኦሪት ካህናት፣የክህነት ሥርዓትና አገልግሎት በሰፊው የሚገልፅ ነው።።
-27 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በ 8 ዋና ዋና ክፍሎች ይከፋፈላል።።
ከምዕራፍ 1-7
-በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር ስለሚቀርቡት የመስዋዕት ዓይኖች ማለትም ስለ እንስሳት አዕዋፍ ዱቄት ዘይትና ዕጣን አቀራረብ።። መስዋዕቶቹ የሚቀርብባቸው ምክንያቶች ከእግዚአብሔር ድኃነትን ለመለመን እግዚአብሔርን ለማመስገንና ለካህናት ወይም ስለ ህዝቡ የበደል ዕዳ ማስተሰሪያ መሆናቸውን የሚገልፅ ነው።።
ከምዕራፍ 8-10
-ለእግዚአብሔር አገልጋይነት አሮንና ልጆቹ እንዴት የክህነት ሹመትን እንደተሾሙ
-የዘይት መቀባቱ ሥነ ስርዓት
-ከዚያም ለ 7 ቀናት ከድንኳኑ እንዳይወጡ መደረጉ
-ናዳብና አብድዩ ሥርዓት በማፍረሳቸው የተፈፀመባቸው ቅጣት ተዘርዝራል።።
ከምዕራፍ 11-14
-የእግዚአብሔር ሕዝብ በመብሉ፣በሰውነቱ በልብሱ፣በቤቱ ንፁህ (ቅዱስ) መሆን እንደሚገባው እንረዳለን።።
ከምዕራፍ 15-16
-ከወንድም ሆነ ከሴት ሰውነት በሚፈስ ፈሳሽ ምክንያት ከሚመጣው ርኩሰት የሚቀደሱበትን የመንፃት ሥነ ሥርዓት
-ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንድ ቀን የራሱንና የህዝቡን ኃጢአት ለማስተሥረይ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ስለሚገባበት ስለ ኃጢአት ሥርየት ቀን ይገልፃል።።
ከምዕራፍ 17-19
-ደም መብለትና ደሙ ሳይፈሰው ታንቆ የሞተውን እንስሳ መብላት መከልከሉ
-የተከለከሉ ጋብቻዎችና ልዩ ልዩ ሕግጋት ይገኙበታል።።
ከምዕራፍ 20-22
-ከአረማውያን አሞልኮና የተለያዩ ጥንቆለ ሥራዎች መከልከልና ወደነዚህ ቦታዎች መሄድ የሚያመጣውን ቅጣትና
-ካህናት የተቀደሱ መሆን እንደሚገባቸው ተዘርዝራል።።
ምዕራፍ 23-24
ስለ ልዩ ልዩ ሕጎች በዓለት መደንገግ
በኪዳኑ ታቦት ፊት ለፊት ባለው ቦታ በየቀኑ የወይራ ዘይት መብራት ያለበት ስለመሆኑ
ለእግዚአብሔር ስለሚቀርብ መሥዎዕተ ኅብስት
የድፍረት ኃጢአት በሚያደርጉ ሰዎች ላይ መፈፀም ያለበት ቅጣት ተዘርዝራል።።
ከምዕራፍ 25-27
በሰባተኛው ዓመት ምድሪቱን ከእርሻ ስለ ማሳረፍ
ኢዮቤልዮ በዓል ሕግጋትና ሥነ ሥርዓት
ለእግዚአብሔር ህግጋት መታዘዝ-ስለሚያስገኘው በረከት

አለመታዘዝ-ስለሚያመጣው ቅጣት
ስለ ስእለት የተደነገጉ ህጎች
4.ኦሪት ዘኁልቁ
‹‹ኁልቁ›› በግዕዝ ‹‹ቁጥር›› ማለት ነው፡፡
የእስራኤልን ልጆች ሙሴ እንዲቆጠር እግዚአብሔር ያዘዘው በመሆኑና ስለ አቆጣጠሩም ታሪክ የሚዘረዘር በመሆኑ ይኸን ስያሜውን አግኝቷል፡፡
36 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በዐራት ዋና ዋና ክፍሎች ተክፍሏል፡፡
ከምዕራፍ **1-10**
በሲና ሰፍረው ሳሉ የሕዝብ ቆጠራ መጀመሩንና ከሲና ተነስተው ወደ ዮርዳኖስ ያደረጉት የጉዞ ታሪክ ይገኛል፡፡
ከምዕራፍ **11-12**
እስራኤላዊያን ከሲና ተራራ እስከ ቃደስ በረሃ ያደረጉትን ጉዞ ይተርካል፡፡
ከምዕራፍ **13-25**
ስለ ዐሥራ ሁለቱ ሰላዮች
እስራኤላዊያን በእግዚአብሔር ላይ በማጉረምረማቸው የእግዚአብሔር ቁጣና በሙሴ አማላጅነት ስለ መዳናቸውና እንዲሁም የእግዚአብሔርን ሥራ በመዘንጋታቸው በምድረ በዳ **40** ዓመት እንደተንከራተቱ እና የሞዓብ ንጉስ ባላቅ በበለዓም አማካኝነት እስራኤልን ለማስረገም ቢሞክርም እግዚአብሔር ግን ከመርገም ይልቅ እንዲባርካቸው እንዳደረገ ተገልፃል
ከምዕራፍ **26-36**
እስራኤላዊያን ወደ ከነዓን ለመግባት ስለመዘጋጀታቸው
ስለ እስራኤላዊያን ርስትና የመሬቱም ክፍፍል ድንጋጌዎች ተዘርዝረዋል፡፡
5. ኦሪት ዘዳግም
‹‹ዘዳግም›› በቁሙ የተደገመ ማለት ነው፡፡ይኽም በኦሪት ዘጸአት፣በኦሪት ዘሌዋውያን በኦሪት ዘኁልቁ የቀረቡትን ሕግጋትና ትእዛዛት በሰብከት መልክ ስለሚደግማቸው ነው፡፡
ለዚህም ሙሴ በናብው(በዔባሪ) ተራራ በሞዓብ አገር ኦሪት በመድገም ቃልኪዳኑ መታደሱን አሳወቀ፡፡
34 ምዓራፎች ሲኖሩት በዐራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡እነሱም
ከምዕራፍ **1-3**
እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገላቸውን ያሳያል
ከምዕራፍ **4-26**
እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጣቸውን ሕጎችና ደንቦችን በድጋሚ ይተረጎማል
ከምዕራፍ **27-30**
ግብረገባዊ ሕጎችን ማረጋገጥና የሕግ ፈጻሚነት ምክሮች ይገኛሉ
ከምዕራፍ **31-34**
ኢያሱ የሙሴ ተተኪ ሆኖ ስለመሾሙ
የሙሴ የመጨረሻ ምክርና ለሕዝቡ ያቀረበው ቡራኬ
ስለክርስቶስ የተነበየው ግልፅ ትንቢት ይገኝበታል፡፡

2.የታሪክ መጻሕፍት

ብዛታቸው **17** ነው፡፡እነዚህም መጻሕፍት በአብዛኛው የእስራኤልን ሕዝብና የነገስታትን ታሪክ በሰፊው ይተርካሉ፡፡ **12** ቱ ነገደ እስራኤል ከሙሴ በኋላ የእስራኤል ሕዝብ መሪ ሆኖ በተመረጠው በኢያሱ ወልደነዌ አማካኝነት መከፋፈላቸው፡፡ከኢያሱ ሞት በኃላ እስራኤላዊያን ያለምድራዊ መሪ በእግዚአብሔር መንግስት ብቻ መተዳደራቸው እግዚአብሔር ለእስራኤላዊያን መሳፍንቶችን ማስነሳቱ ከሳኦል-ሰለሞን ድረስ እስራኤላውን ለ **120** ዓመታት ሳይከፋፈሉ በአንድ መንግስት ሰር እንደነበሩና በሮብአም ጊዜ ለሁለት እንደተከፈሉ በበደላቸውም ምክንያት (እስራኤላውያን) ዐስሩ ነገድ በአሶር ሁለቱ ነገድ በባሊሎን እንደተማረኩ፡፡
ከ **70** ዓመት የባቢሎን ምርኮ በኃላ እስራኤላውያን ወደ ሀገራቸው እንደተመለሡ
የመሲኹ የትውልድ ዘር ከዳዊት ቤት መሆኑንም ጭምር እነዚህ መጻሕፍት ያስረዳሉ፡፡

1.መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ
ዐሐፊው ኢያሱ ሲሆን ትርጉሙም እግዚአብሔር አዳኝ ማለት ነው፡፡
ይዘቱ፡-የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ኃይልና በኢያሱ መሪነት ከነዓንን እንደወረሱ ይተርካል፡፡
24 ምዕራፎች አሉት፡፡
2.መጽሐፈ መሳፍንት
መሰፍን፡- ፈራጅ አስተዳዳሪ ማለት ነው፡፡

ይህን ስያሜውን ያገኘው ከኢያሱ ሞት በኋላ እስከ መጀመሪያው የእስራኤል ንጉስ ሳኦል ድረስ እስራኤልን ለ 400 ዓመታት ገደማ ያስተዳድሩ ስለነበሩ መሳፍንት ስለሚገልፅ ነው።

በመጽሐፈ መሳፍንት የተገለፁት 13 ቱ መሳፍንት

፩ ጎቶንያል (መሳ 3፥7-11) ፭ ኢያዐር (መሳ 10፥3-5)

፪ ናዖድ (‘‘3፥12-30) ፮ ዮፍታሔ (‘‘11፥1)

፫ ሰሜጋር (‘‘4፥16-31) ፯ ኢብዓን (‘‘12፥11)

፬ ባርቅ (‘‘4፥1-5,31) ፰ ኤሎም (‘‘12፥8)

፮ ጌዴዎን (‘‘6፥11) ፱ ዓብዶን (“12፥13)

፯ አለሜሎክ (‘‘9፥22) ፲ ሶምሶን (“13፥1-16

፰ ቶላ (‘‘10፥1-2)

መጽሐፈ መሳፍንት *21* ምዕራፎች ሲኖሩት

ፀሐፊው፥-ነብዩ ሳሙኤል፡ነው።

3. መጽሐፈ ሩት

ሩት በዘመነ መሳፍንት የነበረች ሞዓባዊት ሴት ናት።በእስራኤል ሀገር ረሀብ ተከስቶ በነበረ ጊዜ ከይሁዳ ነገድ አቤሜሌክ የተባለ ሰው ኑኃሚን ከተባለች ሚስቱ መሐሎንና ኬሎዎን ከተባሉት ሁለት ወንዶች ልጆቹ ጋር ወደ ሞዓብ አገር ተሰድዶ ነበር አቤሜሌክ ከሞተ በኃላ ከሁለቱ ልጆች መሐሎን ሩትን አግብቶ ነበር እርሱም ልጅ ሳይወልድ ሞተ ኑኃሚን ወደ ሀገሯ ለመመለስ በፈለገች ጊዜ ሩትም ተከትላ ሄደች ከዚያም ቦዔዝ የተባለውን የአቤሜሌክ ዘመድ አግብታ ኢዩቤድ የተባለውን የዳዊትን አያት ወልዳለች መጽሐፈ ሩት ከአሕዛብ ወገን የነበረችውን ሩት በእምነቷ ምክንያት እንደተቀበለት እና የዳዊት አያትም እንደሆነች ያሳያል።

መጽሐፈ ሩት 4 ምዕራፎች አሉት፤ፀሐፊውም ነቢዩ ሳሙኤል ነው።

4. መጽሐፈ ሳሙኤል አንደኛ

ሳሙኤል ማለት፥- የእግዚአብሔር ስም/ አምላካዊ ስም

፥- *እግዚአብሔር ሰማኝ* ማለት ነው።

ሳሙኤል ከዘመነ መሳፍንት መጨረሻ የተገኘ ነቢየ እግዚአብሔር ነው።

ፀሐፊው፥- ነቢዩ ሳሙኤል ነው።

በዚሁ መጽሐፍ ምዕራፍ 25 ላይ ሳሙኤል መሞቱ ስለተገለፀ ከመጽሐፍ የተወሰነው ክፍል በናታን ወይም በጋድ እንደተፃፈ ይገመታል። (1ኛ 29፥29)

ይዘቱ፥- ስለ ካህኑ ኤሊ ልጆች ስለ ሳሙኤል ስለሳዖል መውደቅና ስለ ዳዊት መነሳት ይገልፃል።

31 ምዕራፎች አሉት።

መጽሐፈ ሳሙኤል ሁለተኛ

ይህ ሁለተኛ የሚገልፀው ታሪክ ሳሙኤል ከሞተ በኃላ ያለውን ነው።

ይዘቱ፥- ቅዱስ ዳዊት በይሁዳ 7 ዓመት በኢየሩሳሌም 33 ዓመት በአጠቃላይ 40 ዓመት በንጉስነት እንደመራ ስለታቦተ ጽዮን የቅዱስ ዳዊት በደልና ንስሐ ያደረጋቸውን ጦርነቶች ይገልፅልናል።

24 ምዕራፎች አሉት።

5. መጽሐፈ ነገስት አንደኛ

አንደኛና ሁለተኛ ነገስት መጻሕፍት ከዳዊት ልጅ ከሰለሞን አንስቶ አስከ ይሁዳ መንግስት ማለቂያ ድረስ ያለውን የ 400 ዓመት የእስራኤልንና የይሁዳን መንግስትና ነገስታት ታሪክ ይተርካሉ።

ፀሐፊው፥- በእርግጠኝነት አይታወቅም

በታልሙድ ሰዎች እምነት ፀሐፊው ነቢዩ ኤርሚያስ ነው ሌሎች ደግሞ ንጉስ ሰሎሞንና ንጉስ ሕዝቅያስ የንግስና ዘመናቸውን ታሪክ ሲፅፉ ነቢዩ ኢሳይያስና ኤርሚያስ የነበሩበትን ዘመን ታሪክ ጽፈዋል ይላሉ።

ይዘት፥- ስለ ንጉስ ሰለሞን፣ስለ ቤተመቅደስ መታነፅና እስራኤል ለሁለት መከፈላቸው።

22 ምዕራፎች አሉት።

መጽሐፈ ነገሰት ሁለተኛ

የሁለቱን ነገስታት ታሪክ ከመጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ ተቀብሎ በመቀጠል ሁለቱን ነገስታት በጠለት ተከበው እስከ ተያዙበትና ሕዝቦቻቸውም ወደ ዴዋዊ እስከ ሄዱበት ያለውን ጊዜ ይገልፃል።

25 ምዕራፎች አሉት።

6. መጽሐፈ ዜና መዋዕል አንደኛ

ዜና መዋዕል ማለት *የእለት ‹ዜና›* ማለት ነው።

የተፃፈበት ዘመን ከ.ክ.ል በፊት *400 ዓመት አካባቢ በካህኑ ዕዝራ* ነው።።
29 ምዕራፎች አሉት።።ይዘቱ ፦ከምዕራፍ 1-9 የትውልድ ሀረግ ከአዳም እስከ አብርሃም፣ከይስሐቅና ከያዕቆብ እስከ ዳዊት እስከ ዘሩባቤል ዘርዝራል።።
ከምእራፍ 10-29 የሳኦል መንግስት መውደቅና የቅዱስ ዳዊትን ንግስና ይገልፃል

7.መጽሐፈ ዜና መዋዕል ሁለተኛ

36 ምእራፎች አሉት
የቤተመቅደሱ መሰራትና የነገስተ እስራኤልን ታሪክን ይገልፃል።።

ጸሎተ ምናሴ

ምናሴ ማለት ‹‹ማስረሻ›› ማለት ነው።።ምናሴ ከይሁዳ ነገስታት ቁጥር ያለ የንጉስ ሕዝቅያስ ልጅ ነው።።2ኛ ነገስት 20፣1 ይህም የፀሎት መጽሐፍ ምናሴ ባዕድ አምልኮን እየተከታተለ ከአሞራውያን ይልቅ ክፋትን ባደረገ ጊዜ በእግዚአብሔር ቁጣ የአሶር ንጉስ ማርኮ ወደ ባቢሎን በወሰደው ጊዜ ምህረት አደረገለትና ምናሴም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።።ሕዝቡም እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ አዘዛቸው።።
አንድ ምእራፍና አስራ ሦስት ቁጥሮች አሉት።።

8.መጽሐፈ ዕዝራ

ዕዝራ ማለት ረድኤት ማለት ነዉ።።
ይዘቱ ከባቢሎን ምርኮ ስለመመለሳቸው (ከ70 ዓመት በኃላ)፣ስለመቅደስ መታነጽ፣ወደ እውነተኛ አምልኮ መመለሳቸውን ከአህዛብ ጋር በጋብቻ ስለተቀላቀሉና በዕዝራ ልመናና ልቅሶ ሚስቶቻቸውን እንደሚለዩ ቃል መግባታቸውን ይገልፃል።።
10 ምእራፎች አሉት።።

መጽሐፈ ነህምያ

ነህምያ ማለት እግዚአብሔር አፅናኝ(አዳኝ)ማለት ነው።።ነህምያ የፋርስ ንጉስ ለነበረው አርጤክስ ጠጅ አሳላፊ የነበረ አይሁዳዊ ልጅ ነው።። ፀሐፊው ራሱ ነህምያ ነው ይዘቱም በ42 ቀናት ውስጥ ቅጽር በድጋሚ ማሳነጽን የጸሎትን ኃይልንና ነህምያ በማስተዳደር ዕዝራ በካህንነት ሕዝቡን በማህበራዊ ኑሮና በሃይማኖት ማገልገላቸውን ይገልጻል።።
አስራሦስት ምዕራፎች አሉት።።

9.መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል

ሱቱኤል (ሰላትያል)የፀሐፊውና የካህኑ ዕዝራ ድርብ ስም ነው።።
ይዘቱም ካህኑ ዕዝራ በተማረበት ሀገር ስላያቸው ራዕዮችና ለጠየቀው ጥያቄ የተሰጠው መልስ እንዲሁም ካህኑ እዝራ እግዚአብሔርን በፀሎት ጠይቆ ልዩ መንፈሳዊ ፀጋና ዕውቀት ተሰጥቶታል።።40 ቀን ፆሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደፃፈ ይገለፃል።።አስራ ሦስት ምዕራፎች አሉት።።

መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ

በ2ኛ ዜና መዋዕል ከምዕራፍ 35-36 ፤ በመጽሐፈ ዕዝራ ከምዕራፍ 2-9 ፤ በመጽሐፈ ነህምያ ከምዕራፍ 7-8 የተገለጸውን ታሪክ በድጋሚ በስፋት የሚገልጽ መጽሐፍ ነው።።
ዘጠኝ ምዕራፎች አሉት።።

10.መጽሐፈ ጦቢት

ጦቢት ስለተባለው ቅዱስ በንጉሱ ሰልምናሶር ዘመን ወደ አሶር ከተማረከ በኃላ እሱና ልጁ ጦብያ ተቸግረው ሳለ እግዚአብሔር በመልአኩ ሩፋኤል አማካኝነት ረድቶአቸው ከችግር ሁሉ እንደወጡ የሚተርክ መጽሐፍ ነው።።
አስራ አራት ምእራፎች አሉት።።

11.መጽሐፈ ዮዲት

ዮዲት ማለት ሀያል፣ተጋዳይ ፣አሸናፊ ማለት ነው።። አስራ ስድስት ምዕራፎች አሉት።።ንጉስ ናቡከደነጸር አስራኤላውያንን ለመውጋት የለከው ሆሎፎርኒስ የተባለው የጦር መሪ በአስራኤላዊቷ ዮዲት እጅ እንዴት እንደተገደለ የሚተርክ ነው።።

12.መጽሐፈ አስቴር

አስቴር በፋርስ ቋንቋ ‹‹ኮከብ›› ማለት ነው።።መጽሐፉም በአርጤክስ ዘመነ መንግስት በምርኮኝነት ይኖሩ የነበሩ አስራኤላውያን ላይ የደረሰውን ስደትና ሞት ከአደጋ መዳናቸውን ይገልፃል።።በወቅቱ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ወይም ስለ ሃይማኖት አንስቶ መነጋገር ችግር ስለሚያስከትል በመጽሐፉ ውስጥ በአንድም ቦታ የእግዚአብሔር ስም አልተጠቀሰም።።ነገር ግን እግዚአብሔር ለሕዝብ ያደረገውን ጥበቃና ተራዳኢነት በሰፊው ይናገራል።።ጸሐፊው የአስቴር አጎት መርዶክዮስ ነው አስር ምዕራፎች አሉት።።

13.1 መጽሐፈ መቃብያን አንደኛ

መጽሐፈ መቃብያን፦ መቃብያን ማለት ጀግኖች ማለት ነው 36 ምዕራፎች አሉት አሉት።።
የመቃቢስ ዘብንያም ልጆች አብያ፣ሲላስና፣ፈንቶ ከሁለት ወንድሞቻቸው ጋር
ጽሩጻይደን የተባለው አመፀኛ ንጉሥ ስለሃይማኖታቸው ምክንያት እንዳሰቃያቸው የተቀበሉትን ሰማዕትነት

ከብሊይ ኪዳን ታሪኮችንና ምሳሌዎችን እየጠቀሱ ስለ ትንሳኤ ሙታን መናገራቸውን የሰው ልጅ የነፍስና የስጋ በረከትና ሕይወት ስለሚያገኝበት መንገድ የመከሩትን ይገልፃል።

13.2 መጽሐፈ መቃብያን ሁለተኛ

21 ምዕራፎች አሉት።እስራኤል በበደሉ ጊዜ የሞዓብ ሰዉ የሆነ መቃቢስን እንዳስነሳባቸውና እስራኤልን በሰይፍ ገድሎ ሲደነፋ እግዚአብሔር በመቃቢስ ስራ ተቆጥቶ ራይን የሚባል ነብይ ልቡን በንስሐ እንዲመለስ ቢነግረው ልብሱን አውልቆ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ቢያዋርድ እግዚአብሔር ስለልጆቹ ብሎ እንደማረው።

14.መጽሐፈ መቃብያን ሦስተኛ

አስር ምእራፎች አሉት ይዘቱም የብሉይ ኪዳንን ታሪኮች እየጠቀሰ የፅድቅና የኩነኔን የትንሳኤ ሙታንንና ዲያብሎስ የሰው ልጆችን የሚያሰናክልባቸው መረቦች በዝርዝር የቀረቡበት ነው።

15.መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን

8 ምዕራፎች ከአዳም ጀምሮ በ **70** ዓ.ም እስከተፈፀመው የኢየሩሳሌም ቤተ-መቅደስ መቃጠል ድረስ የአ ይሁድን ታሪክ የሚተርክ ።።

16. መጽሐፈ ኩፋሌ

ኩፋሌ ማለት መክፈል ወይም መግመስ ማለት ነው። ይህ መጽሐፍ ከመጀመሪያ የስነፍጥረት ቀን ጀምሮ እስራኤል ከግብፅ እስከወጡበት ያለው ጊዜና ታሪክ አስፋፍቶ የሚተርክ መጽሐፍ ነው። **34** ምዕራፎች ሲኖሩት ፀሐፊውም ነብዩ ሙሴ ነው።

17.መጽሐፈ ሄኖክ

ከአዳም ጀምሮ ሲቆጠር ሰባተኛ ትውልድ በሆነው በሄኖክ የተጻፈ ባለ *42* ምዕራፎ መጽሐፍ ነው። ይዘት፡-ስለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

ለቅዱሳን መላዕክት

ስለ ፀሀይና ጨረቃ ዑደት

ስለ ዕዕዋት

ስለ ጻድቃንና ኃጥአን

በኖህ ዘመን ስለተፈፀመው ኀጢያትና ቅጣት።

3. የመዝሙርና የጥበብ መጻሕፍት

መዝሙር ማለት ምስጋና ማለት ነው ።። ጥበብ ማለት ደግሞ ማስተዋል መንፈሳዊ ዕውቀት ማንኛውንም ነገር ለማግኘት የመመርመር ችሎታ ማለት ነው። እነዚህ መጻሕፍት በሰምና በወርቅ የተጣፉ በመሆናቸው የቅኔ መጻሕፍት ይባላሉ።

1.መጽሐፈ ኢዮብ

42 ምዕራፎች አሉት መጽሐፍ በሰድ ንባብ መልክ ከተጻፉት የመጀመሪያውና የመጨረሻው ክፍሎች በስተቀር አብዛኛው ምዕራፎች የተጻፉት በግጥም መልክ ነው ይህ መጽሐፍ እግዚሐብሔርና በሚወዱና ለሕጉ በሚታዘዙ ሰዎች ላይ መከራ ሊደርስ እንደሚችልና በትግስት ካሳለፉት መከራው እንደሚወገድ በረከትንም ከእግዚአብሔር በእጥፍ እንደሚያገኙ የሚያስተምር መጽሐፍ ነው መጽሐፉ ስለ ኢዮብ ታሪክ ይተርካል።

2.መዝሙረ ዳዊት

150 የመዝሙርና ጸሎት ትምህርትና ቅኔ በአንድነት ይገኙበታል።።መዝሙረ ዳዊት ብዙውን ጊዜ የዳዊት መዝሙር የሚባልበት ምክንያት አብዛኛው መዝሙር እርሱ ስለደረሳቸው ነው።

መዝሙር **90**፡-የሙሴ መዝሙር

መዝሙር **146**፣**147**።፡-የሐጌና የዘካርያስ መዝሙር

148 በቆሬ ልጆች ስም የሚጠሩ **11** መዝሙሮች አሉ መዝ **2**፣**4**፣**84**፣**86**፣**87**

የአሳፍ መዝሙሮች የሚባሉ አሉ ፤መዝ **50**፤**73**፤**79**፤**81** ወ.ዘ.ተ

መዝሙረ ዳዊትን አሁን ባለበት ሁናቴ ያዘጋጀው ካህኑ እዝራ ነው ።። የሰውን የሕይወት ዘመን ሳይለይ ሰው በሕይወቱ የሚያጋጥሙትን ኃዘንና ደስታ መልካምና ክፉ መውደቅና መነሳት ችግርና ምቶች ከእግዚአብሔር መራቅና መቅረብ የያዘ መጽሐፍ ነው። ለቤተክርስቲያናችን የፀሎትና የመዝሙር መጻሕፍት (ምሳ.ድኃ) መሠረታቸው መዝሙረ ዳዊት ነው።

መዝሙረ ዳዊት በ **5** ክፍሎች የተከፈለ መጽሐፍ ነው

፩ኛ ከመዝ **1-40**

፪ኛ ከመዝ **41-71**

፫ኛ ከመዝ **72-88**

፬ኛ ከመዝ **89-105**

፭ኛ ከመዝ **106-150**

የእያንዳንዱ ክፍል ፍፃሜ የሚታወቀው <<ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም እግዚአብሔር ይባርክ አሜን አሜን>> የሚሉ ቃላት ስለተጻፈባቸው ነው።።በቤተክርስቲያናችን ደግሞ አሰሩን መዝሙሮች በአንድነት <<አንድ ንጉስ>> በሚል ስያሜ በአስራ አምስት ይከፈላል። ከጥንት

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው የመዝሙረ ዳዊት ንባብና ትርጓሜ መሠረት ደግሞ መዝሙረ ዳዊት በ 10 አርእስት እንደሚከፈል ይገልጻል።አነርሱም፦

፩ ለሁሉም የሚሆን ተግሣፅና ምክር መዝ 1፥1
፪ ለክርስቶስ የተናገረ ትንቢት መዝ 2፥1
፫ ስለ ዳዊት የተነገረ ትንቢት መዝ 3፥1
፬ ስለ መናንያን የተነገረ መዝ 4፥1
፭ ስለ ትሩፋት መዝ 5፥1
፮ ስለ ሕዘቅያስ መዝ 13፥1
፯ ስለ ኤርሚአስ መዝ 34፥1
፰ ስለ መቃብያን መዝ 53፥1
፱ ስለ ካህናት ተግሣፅ መዝ 49፥1
፲ ስለ ሰለሞን መዝ 71፥1 የተነገሩ ትንቢቶች ናቸው።የተቀሩት 140 እነዚህ ሥር ይካተታሉ።

በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ የሚገኙት 7 ዓበይት ትምህርቶች

፩ ጠለትን መውደድ መዝ 16፥4
፪ ትህትና መዝ 21፥16
፫ ሀይማኖት መዝ 21 ፥10
፬ ተስፋ መንግስተ ሰማያት መዝ 26፥1
፭ ሀጥያትን ማመን መዝ 37፥4
፮ ይቅርታ መዝ 50
፯ መፅዋት መዝ 111፥8

3. መጽሐፈ ምሳሌ

በጠቢቡ ሰሎሞን የተፃፈ 24 ምዕራፎች አሉት። ስለ ጥበብ ጥቅም ስለእግዚአብሔር ወልድ ልደት ስለ እመቤታችንና ፈሪሀ እግዚአብሔር ማስተማር ነው።

4. መጽሐፈ ተግሳፅ

7 ምዕራፎች ያሉት በአቀራረቡ ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር ተመሳሳይነት ያለው በንጉስ ሰሎሞን አጎርና ሳሙኤል የተጻፈ ነው። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር በአንድነት ከምዕራፍ 25-31 ድረስ በመካተት የሚቆጠር ነው።

5. መጽሐፈ መክብብ

መክብብ ማለት ሰባኪ ወይም አስተማሪ ማለት ነው።

ፀሐፊው፦ ሰሎሞን

ይዘት፦ ስለ ሕይወት አስቸጋሪ ነገሮች ሁሉም ከንቱ መሆኑንና ጥበብ ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን በአለም ላይ ስላሉ ተቃራኒ ነገሮች እያነሳ ሁሉም ከንቱ መሆኑን ይገልጣል።ከንቱ የሚለው ቃል በመፅሐፈ መክብብ 37 ጊዜ ተፅፏል።12 ምዕራፎች አሉት።

6. መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን

ትርጉም፦ ከመዝሙራት ሁሉ የሚበልጥ የሰሎሞን መዝሙር ማለት ነው።

ፀሐፊው፦ ሰሎሞን

ምዕራፍ፦ 8

ይዘት፦ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መሃከል ያለውን ፍቅር በክርስቶስና ቤተ ክርስትያን ያለውን ፍቅር ስለ እመቤታችን ስለሚሰጢረ ቁርባን ይገልፃል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ኤፌ 5፥1 ለሙሽሪትና ለሙሽራው መስሎ በክርስቶስና በቤተክርስቲያን መሃከል ያለውን አንድነት በምሳሌ እንደገለፀ መኃልየ መኃልየ ዘሰለሞን በእግዚአብሔርና እስራኤል መሃል ያለው ፍቅር በሙሽሪትና ሙሽራው መስሎ ይገልፃል።

7. መጽሐፈ ጥበብ

መጽሐፈ ጥበብ ማለት ዕውቀት ብልሀት ፈሊጥ ሕክምና እና ምክር ማለት ነው።

19 ምዕራፍ ያለው፣በጠቢቡ ሰሎሞን የተፃፈ በአቀራረቡ ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር ተመሳሳይነት አለው።ይዘት፦ ስለጥበብ ጥቅም በመምከር ሰው ጥበብን እንዲፈልግ ይመክራል።

8. መጽሐፈ ሲራክ

ሲራክ፦ ፀሐፊ ማለት ነው።

ፀሐፊ፦ ኢያሱ ወልደ አልዓዛር ወልደ ሲራክ ይባላል።

51 ምዕራፎች፦ በአቀራረቡ ከሰሎሞን መጽሐፈ ምሳሌ ጋር ተመሳሳይነት አለው።

ይዘት፦ ለመንፈሳዊና ስጋዊ ህይወታችን ጥበብና ምክር የሚሰጥ ነው።

4 የትንቢት መጻሕፍት
ነቢያት በሁለት መንገድ ቃልን ከእግዚአብሔር ተቀብለው ለሕዝቡ የሚናገሩ ናቸው። ይህም በእግዚአብሔር ውሳኔ ስለሚፈፅሙ ድርጊቶች፣ ስለመንግስት ስለሰዎችና ስለኃጥያት ወደፊት ስለሚሆኑ ድርጊቶች።
የመጽሐፍቱ አቀራረብ በዚህ መልክ በመሆኑና ሁሉም በነቢያት በመጻፋቸው የትንቢት መጽሐፍት ተብለዋል። ነቢያት ትንቢታቸውን ያስተላለፉት በቃልና በፅሑፍ ነው።በቃል ብቻ ትንቢታቸው የተናገሩ ነብያት ትንቢታቸውን በፅሑፍ ያሰፈሩላቸው የታሪክ ፅሀፍት ናቸው።
ምሳሌ፦ የነቢዩ ኤልያስና የነብዩ ኤልሳዕ ትንቢቶችና ትምህርቶች የሰፈሩት በመጽሐፈ ነገስት ነው።በዚህ ክፍል የሚዳሰሱት የፅሑፍ ነቢያት የተባሉት (የተናገሩትን በፅሑፍ ያሰፈሩ) ናቸው።ነቢያት በሚከተሉት 3 ምክኒያቶች በተለያዩ ምድቦች ሊመደቡ ይችላሉ።
በፅሑፎቻቸው ምዕራፎችና ቁጥር ብዛት እንዲሁም በመዓረጋቸው
ዐበይት ነቢያት ኢሳይያስ ኤርሚያስ ሕዝቅኤል እና ዳንኤል
ደቂቅ ነቢያት ሆሴዕ አሞፅ ሚክያስ ኢዮኤል አብድዩ ዮናስ ናሆም ዕንባቆም ሶፎናያስ ሐጌ ዘካሪያስና ሚልክያስ
በኖሩበት ቦታ
የይሁዳ ነብያት ኢሳይያስ ኤርሚያስ ሚክያስ ሚልክያስ አሞፅ ሶፎንያስ ሐጌ
የሰማርያ ነብያት ሆሴዕ፣ዮናስ፣አሞፅ
የባቢሎን ነብያት ሕዝቅኤል፣ዳንኤል
በኖሩበት ዘመን
ከባቢሎን ምርኮ በፊት ኢሳይያስ፣ ሆሴዕ፣ ኢዮኤል፣ አሞፅ፣ ሚክያስ፣ አብድዩ፣
በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ኤርሚያስ፣እንባቆም፣ሕዝቅኤል፣ዳንኤል
ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ሐጌ፣ዘካርያስ፣ሚልክያስ

1 ትንቢተ ኢሳይያስ
የስሙ ትርጉም፦እግዚአብሔር ደኅንነት ነው
ፀሐፊው፦ነብዩ ኢሳይያስ አገልግሎቱን የጀመረው በዖዝያን መንግስት መጨረሻ አካባቢ ነው።በ 4 የይሁዳ ነገስታ (በዖዝያን፣በኢዮአታሞ፣በአካዝና፣በሕዝቅያስ) ዘመን ከ.ክ.ል.በ ከ 740-688 አካባቢ ትንቢት የተናገረ ነብይ ነው
መጽሐፉ የተፃፈው ከ.ክ.ል.በፊት 700 ዓመት ላይ
 ነብዩ ኢሳይያስ ስለጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግልፅ ትንቢቶች በመናገሩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስትያን መጽሐፉን ደረቅ ሐዲስ ሲሉት አርሱን ደግሞ ወንጌላዊው ነብይ ይሉታል።ነብዩ ኢሳይያስ የኖረው እስከ ንጉስ ሞናሴ ዘመን ድረስ ሲሆን፣ንጉስ ሞናሴ ገና በንሰሐ ወደ አምላኩ ከመመለሱ በፊት ኢሳይያስን በመጋዝ አስቆርጦ እንዳስገደለው ይነገራል። (መስከረም 6 በሰማዕትናት አልፏል)
66 ምዕራፎች አሉት።
2 ትዕንቢተ ኤርሚያስ
የስሙ ትርጉም፦እግዚአብሔር ከፍ ያደርጋል
ፀሐፊው፦ነብዩ ኤርሚአስ በእናቱ ማህፀን ሳለ የተመረጠና በወጣትነቱ እግዚአብሔር ለአገልግሎት ያዘጋጀው ታላቅ ነብይ ነው።የነብዩም ጥሪ የተፈፀመው የይሁዳ ንጉስ ኢዮስያስ በነገሰው በ 13 ኛው ዓመት ነበር። በኤርሚአስ የነብይነት ዘመን ፭ ይሁዳ ነገስታት ነግሰዋል። እነርሱም፦ኢዮስያስ፣ ኢዮአክስ፣ ሴዴቅያስ፣ ኢዮአቄምና፣ ዮአኪን ናቸው። በእነዚህ ዘመን ለ 40 ዓመታት ያህል በነብይነት አገልግሏል።ነብዩ ኤርሚያስ ሕይወቱ በሥቃይና በለቅሶ የተሞላ ስለነበር የመከራ/የለቅሶ/የስቆቃ/ ነብይ ይባላል። በትንቢተ ኤርሚያስ የተገለፀው የትንቢቱ ቃል ብቻ ሳይሆን ስለራሱ ስለ ኤርሚያስና ስለደረሰበት መከራ ብዙ ነገር ስለተፃፈ፤ከሌሎች ነብያት ይልቅ ጠባዩና ሁኔታውን ገልፃል። የትንቢት ኤርሚያስ ዋና መልዕክት እግዚአብሔር ታላቅና ቅዱስ ስለሆነ ሕዝቡ ከክፋት ተመልሰው በፍፁም ልብ ያለ ሐሰት እርሱን እንዲያመልኩት ማስገንዘብ ነው። ነቢዩ ኤርሚያስ ኢየሩሳሌም በተወረረችና በተደመሰሰች ጊዜ ወደ ግብፅ ከተሰደዱ አይሁድ ጋር አብሮ ሄዶ ነበር።በዛም በስደት አገር ወገኖቹ አይሁድ ስለልባቸው ክፋትና ስለሕግ መተላለፋቸው ይወቅሳቸው ስለነበር በድንጋይ ወግረው ገደሉት።
ምዕራፍ፦52
ሰቆቃወ ኤርሚያስ
ሰቆቃ ማለት ሙሾ፣ልቅስ ማለት ነው።
ፀሐፊው፦ ነብዩ ኤርሚያስ
ምዕራፍ፦ 5
ይዘት፦ኢየሩሳሌም በጠላት እጅ መውደቋን፦የካህናት የነቢያት መገደል።የቤተመቅደስ መፍረሰን የንብረትና የሕዝቧ መማረክን መነሻ በማደረግ ነብዩ ኤርሚያስ ያቀረበውን ሰቆቃ(የኃዘን እንጉርጉሮ) ይዞ ይገኛል።ስለአስከፊው ረሀብ ስለእግዚአብሔር ቁጣና ቅጣት ማዳኑን ተስፋ ስለማድረግና ስለ ምህረቱም ጭምር የተገለጠበት መጽሐፍ ነው።
ተረፈ ኤርሚያስ

ተረፈ ኤርሚያስ ከሰቆቃወ ኤርሚያስ ቀጥሎ ምዕራፍ 6 ብሎ የሚጀምር 6 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።።
ፀሐፊ፡-ባሮክ
ይዘት፡- ስለ ባቢሎን ምክርና የምርኮውን ዘመን እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ ለባሮክና ለአቤሜሌክ እንዳሳለፋቸው እንዲሁም ስለኤርሚያስ ሰማዕትነት ይገልፃል።።
መጽሐፈ ባሮክ
ባሮክ ማለት ቡሩክ ማለት ነው።።ባሮክ የነብዩ ኤርሚያስ ታማኝ ወዳጅና ፀሐፊ ነበር።።
ኤርሚያስ በንጉስ ሴዴቅያስ ዘመን በታሰረ ጊዜ፣ባሮክ የንጉሱን ቁጣ ሳይፈራ ነብዩን ይረዳው ነበር።።
ፀሐፊው፡-ባሮክ(የነብዩ ኤርሚያስ ደቀመዝሙር)
መጽሐፉም ባሮክ በባቢሎን ምርኮ በነበረበት ጊዜ ለኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ፅፎ የላከላቸው ነው።።
ይዘት፡-በምርኮ ስላሉት አይሁድ ኑሮ
ስለ ንስሐ ፀሎትና
ለአይሁድ የቀረቡ ምክሮች ያካትታል።።
ሰቆቃወ ኤርሚያስ ተረፈ ኤርሚያስና መጽሐፈ ባሮክ በተፃፉበት ጊዜና ይዘት አቆጣጠራቸው ከትንቢት ኤርሚያስ መጽሐፍ ጋር በመደመር እንደ አንድ መጽሐፍ ይቆጠራሉ።።
3 ትንቢተ ሕዝቅኤል
ፀሐፊ፡-ነብዩ ሕዝቅኤል
ትርጉም፡-እግዚአብሔር ብርታትን ይሰጣል
ሕዝቅኤል በ 30 ዓመት ዕድሜአቸው እግዚአብሔር ከኪሩቤል ዙፋን ላይ ተቀምጦ ሳለ በራእይ ለመመልከት የበቃ ነበር።።እግዚአብሔርም ሕዝቅኤል በምርኮ ሳለ ለተማረኩት ሕዝበ እስራኤል ነብይ ይሆን ዘንድ ጠራው።።የነብዩ የአገልግሎት ዘመን በሁለት የተለያዩ ክፍሎች ሊከፈል ይችላል።።
1 ከክ.ል.በ በ 587 ዓመት ኢየሩሳሌም በጠላት እጅ ከመውደቋ አስቀድሞ በባቢሎን ምርኮኞች መካከል የፈፀመው የስብከት አገልግሎት (ሕዝ 4፥ምዕ 24)
2 ኢየሩሳሌም በጠላት እጅ ከወደቀች በኃላ በባቢሎን የፈፀመው የስብከት አገልግሎት (ሕዝ ምዕ 33-ምዕ 48)
ሕዝቅኤል በባቢሎን ለ 20 ዓመታት እያስተማረ ቆይቶ እዚያው በምርኮ እያለ በሰማዕትነት ያረፈ ታላቅ ነብይ ነው።።
ምዕራፍ፡-48
ይዘቱ፡-ስለኢየሩሳሌም ውድቀትና ከውድቀት መነሳት ስለጌታችንና ስለ 5 ቱ አዕማድ ምስጢር ስለአመቤታችን ይናገራል።።
4 ትንቢተ ዳንኤል
ፀሐፊ፡-ነብዩ ዳንኤል
ትርጉም፡-እግዚአብሔር ፈራጅ ነው
ዳንኤል በ 605 ዓመት ከክ.ል.በ በናቡከደነፆር ተማርከ ወደባቢሎን የተጓዘ ይሁዳዊ ነው።።ዳንኤል በስደት አገር ሰሙ ብልጣሶር ተባለ።። የከለዳዊያንን ቋንቋ ተምሮ በባቢሎን ተሾመ።።ዳንኤል በሞርኮ ሀገር እያለ 4 የሕዝብ ነገስታትን አሳልፏል።።ናቡከደነፃር ብልጣሶር ዳርዩስና ቂሮስ ናቸው እርሱም እነዚህን ነገስታት በማስተማር ሕልምን በመፍታት ፅሑፍን በመተርጎም አገልግሏል።።
ይዘት፡- በስደትና በፈተና ጊዜ በሃይማኖት መፅናት እንደሚገባ በመከራ ሳሉ ለሃይማኖታቸው ለሥርዓተቸው ታማኝ ስለሆኑት ስለ ሠለስቱ ደቂቃ (አናንያ፣አዛሪያ፣ሚካኤል) ይናገራል።።
ምዕራፍ፡ 12 ሲኖሩት 6 ታሪኮችና 4 ራዕዮችን የያዘ መፅሐፍ ሲሆን
ከምዕ 1-6 የታሪክ ክፍል
ከምዕ 7-12 የራዕይ ክፍል ሊባል ይችላል።።
መዝሙረ ዘሠለስቱ ደቂቅ
ፀሐፊው፡-ነብዩ ዳንኤል
ይዘት፡- ሲድራቅ ሚሳቅ አብድናጎም/አናንያ፣አዛርያ፣ሚካኤል/ስለተባሉት 3 እስራኤላውያን ህፃናት የእምነት ፅናትና በመከራ ተፈትነው በቅዱስ ገብርኤል ረዳትነት ከእሳት ከተረፉ በኃላ እሳት ውስጥ የፀለዩት ፀሎት የዘመሩት መዝሙር ነው።።
ምዕራፍ፡- 1
መጽሐፈ ሶስና
ፀሐፊ፡- ነብዩ ዳንኤል
ትርጉም፡- የዋኅት ርግብ
ይዘቱ፡- ስለ ሶስና ንፅህና ስለአይሁድ መምህራን(ስለ ሁለቱ) የሀሰት ክስና እንዲሁም ስለዳንኤል ጥበብ የሚያሳይ ነው።።
ምዕራፍ፡- 1

ተረፈ ዳንኤል
ፀሐፊ፡- ነቢዩ ዳንኤል
ምዕራፍ፡- 1
ከቁጥር 1-28
ፈረሳዊያን የባቢሎን ሰዎች ያመልኳቸው የነበሩትን ጣዖት ነቢዩ ዳንኤል እንዴት እንዳጠፋ
ከቁጥር 29-42
ነብዩ ዳንኤል እግዚአብሔር ከአንበሶች አፍ እንዳዳነው የሚገልፅ መፅሐፍ ነው።።
5 ትንቢተ ሆሴዕ
ፀሐፊ፡-ነብዕዩ ሆሴዕ
ትርጉም፡- እግዚአብሔር ያድናል
ነብዩ ሆሴዕ ዳግማዊ ኢዮርብዓም በሰማርያ ነገሥ በነበረበት ዘመን በሰሜናዊው የኢየሩሳሌም መንግስት ተነስቶ የነበረ ነብይ ነው።።
ምዕራፍ፡- 14
ሆሴዕ ትንቢት በተናገረበት ዘመን ዖዝያን፣ኢዮአታም፣አካዝና ሕዝቅያስ የሚባሉት የይሁዳ ነገስት ነበሩ።።
ይዘት ታጥያተኛና አመንዝራ ለሆነው ለእስራኤል የእግዚአብሔር ፍቅር ፀጋ ምን ያህል እንደሆነ መግለፅ ነው።።እንዲሁም የእስራኤልን ጣዖት አምልኮ ለባል ታማኝነት በሌለት አመንዝራ ሴት መስሎ አስተምሯል 10 ሩ ነገድ ለምርኮ መቃረባቸውንም ይገልፃል።።
6 ትንቢተ አሞፅ
ፀሀፊ፡-ከበግ አረኝነትና የሾላ ፍሬ ከመጠበቅ ለነቢያት የተመረጠው ነቢዩ አሞፅ ነው።።
ትርጉም፡-ኃይል
ይህ ነቢይ በ 2 ኛ ነገ 19፡20 ላይ እንደተገለፀው የነቢዩ ኢሳይያስ አባት የሆነው አሞፅ አይደለም ።።
ምዕራፍ፡- 9
ይዘት፡- የፍርድ ቃልን በሰፊው ይዘግባል።።በመጽሐፍ መጨረሻ ላይም በፍፃሜ ዘመን ላይ ለእስራኤልም ሆነ ለአሕዛብ የደኃንነትንና የሰላም ጊዜ እንደሚመጣ የአዲስ ኪዳንን ዘመን በትንቢት ተናግሯል።።
7 ትንቢተ ሚክያስ
የስሙ ትርጉም፡- እግዚአብሔርን የሚመስል ማን ነው
ፀሐፊው፡- ነብዩ ሚክያስ
ይኸኛው ነብይ በ 1 ኛ ነ 22፡8 ላይ ከተጠቀሰው በይሁዳ ንጉስ በኢዮሳፍጥና በእስራኤል ንጉስ በአክዓብ ዘመን ከነበረው ነቢይ የተለየ ነው።።ነብዩ ሚክያስ ትንቢት የተናገረው ከከሰማርያ ውድቀት በፊት ስለነበር ስለሰማርያ ስለኢየሩሳሌም መፍረስ ትንቢት ተናግሯል።።
ምዕራፍ፡- 7
8 ትንቢተ ኢዩኤል
የስሙ ትርጉም፡- እግዚአብሔር አምላክ ነው
ፀሐፊ፡- ነቢዩ ኢዩኤል
ይዘት፡- አገልግሎቱ በይሁዳ መንግስት ሲሆን በመጀመሪያ ለአገልግሎት የተጠራበት ምክንያት በሕዝቡ ላይ ሊወርድ ስላለው የአንበጣ መንጋ ዖምና ፀሎት ይደረግ ዘንድ ሕዝቡን እንዲያስጠነቅቅ ነው።።
ምዕራፍ፡- 3
9 ትንቢተ አብድዩ
የስሙ ትርጉም፡- የእግዚአብሔር አገልጋይ ማለት ነው።።
ፀሐፊ፡- ነብዩ አብድዩ
ይዘት፡- ኤዶማውያን የተባሉት የዔሳው ዘሮች በእስራኤላውያን ላይ ስለፈፀሙባቸው ግፍ ነብዩ የወቀሰበትን መልእክት የያዘ ነው።።
ምዕራፍ፡-1
10 ትንቢተ ዮናስ
የስሙ ትርጉም፡- ርግብ ማለት ነው።።
ዮናስ በዳግማዊ ኢዮር ብዓም ዘመን በሰሜን እስራኤል መንግስት የተነሳ ነብይ ነው
ፀሐፊ፡- ነብዩ ዮናስ
ይዘት፡- እግዚአብሔር ለነነዌ ሰዎች ያለውን ፍቅር ነብዩ ዮናስን ወደ ነነዌ መላኩን ነገር ግን ዮናስ ኮብልሎ ወደ ተርሴስ መሄዱንና በመጨረሻም የነነዌ ሰዎች በንሰሐ መመለሳቸውን ይገልፃል።።
ምዕራፍ፡- 4

ነብዩ ዮናስ በቀጥታ ስለክርስቶስ ትንቢት ባይናገርም በዓሳ አንበሪ ሆድ ውስጥ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በማደሩ ለመሲሕ ክርስቶስ ምሳሌ ሆኗል።

11 ትንቢተ ናሆም

የስሙ ትርጉም፡- መጽናናት ማለት ነው።

ፀሐፊ፡- ነቢዩ ናሆም

ስለ ነነዌ ዳግም መጥፋት የተነበየ ነቢይ ነው።

ይዘት፡- ስለ ነነዌ ውድቀት ስለ እግዚአብሔር ምሕረት ይናገራል።

ምዕራፍ፡- 3

12 ትንቢተ ዕንባቆም

የስሙ ትርጉም፡- እቅፍ ማለት ነው

ፀሐፊ፡- ነቢዩ እንባቆም

ይዘት፡- የእይሁዳ ሕዝብ በኃጥያቱ ስለሚደርስበት መከራ ከለዳውያን በሚገዟቸው ሕዝቦች ባደረሱት ግፍ የሚደርስባቸው ቅጣትና ነቢዩ የፀለየውን ፀሎት የያዘው ነው።

ምዕራፍ፡- 3

13 ትንቢት ሶፎንያስ

የስሙ ትርጉም፡- እግዚአብሔር ሰውረል/ጠብቋል ማለት ነው።

ፀሐፊ፡- ነቢዩ ሶፎንያስ

በንጉስ ኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት የነበረ ነቢይ ነው።

ይዘት፡- ክፉ አድራጊዎች ስለእግዚአብሔር የቁጣ ቀን ስለጸዋዊ/ምርኮ/ እና /ስለሚጠት/ መመለስ ይናገራል። <<በዚያን ጊዜ የሕዝቦችን አሳብ አለውጠለሁ ይኸውም ወደ ሐሰተኞች አማልክት ሳይሆን ወደ እኔ በንጹህ ሀሊና እንዲፀልዩ አደርጋለሁ፤ሁሉም በአንድነት እኔን ያገለግላሉ>>ሶፎ 3፡9 በማለት በኋለኛው ዘመን ካለማመን ወደ ክርስትና ማመን እንደሚመለሱ ትንቢት ተናግሯል።

ምዕራፍ፡- 3

14 ትንቢት ሐጌ

የስሙ ትርጉም፡- በዓላዊ ይህም በበዓል ቀን ተወለደ እንደማለት ያለ ነው።

ፀሐፊ፡- ነቢዩ ሐጌ

ይዘት፡- የእግዚአብሔርን ቤተመቅደሱን እንዲሠሩ ማበረታታት ከሁሉ የእግዚአብሔርን ነገር እንዲያስቀድሙ ማሳሳብ ነው።

ምዕራፍ፡- 2

15 ትንቢተ ዘካርያስ

የስሙ ትርጉም፡- እግዚአብሔር ያስታውሳል ማለት ነው።

ፀሐፊ፡- ነቢዩ፡- ነቢዩ ዘካርያስ

ይዘት፡- የሐጌ ትምህርታዊ ማስጠንቀቂያ የራሱንም መልዕክት ያቀረበና እንዲሁም ሐጌ የዘረዘራቸው በሕዝቡ ላይ የደረሱ ችግሮች የሚወገዱት ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ መሆኑን የሚገልፅ።

ምዕራፍ፡- 10

16 ትንቢተ ሚልክያስ

የስሙ ትርጉም፡- መልዕክተኛዬ

ፀሐፊ፡- ነቢዩ ሚልክያስ

ይዘት፡- የእስራኤልን ኃጥያትና ክህድት እንዲሁም በኃጢአተኞች ላይ የሚመጣውን ቅጣት/ፍርድ/ እንዲሁም ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይናገራል።

ምዕራፍ፡- 4

ክፍል ሦስት

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት

ሐዲስ ኪዳን ምንድን ነው?

ሐዲስ ኪዳን የማይሻር ዘለዓለማዊ አዲስ ውል፣ቃልኪዳን፣መሐላ፣ስምምነት ማለት ነው።

የሐዲስ ኪዳን ክፍሎች

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በአምስት እንከፋፍላቸዋለን እነርሱም

የወንጌል

የታሪክ
የመልዕክታት
የትምህርት
የሥርዓትና
የትንቢት ክፍሎች ናቸው።።

1 የምሥራች (ወንጌል) ክፍል

ወንጌል የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም የምስራች ማለት ነው።።ወልድ በሥጋ ተገልዖ ያደረገውን የማዳን ጉዞ ለሰዎች የሰጠውን ከኃጥያትና ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ መውጣት ስለሚገልፅ ወንጌል የምስራች ተብሏል።።፬ሐፊያኑም ወንጌላውያን ሲባሉ ማቴዎስና ዮሐንስ ከሐዋርያት ማርቆስና ሉቃስ ከአርድእት ወገን ናቸው።።ወንጌላውያን ከፍ ብለው አምስት ዝቅ ብለው ሦስት ያልሆኑበት/ አራት ብቻ የሆኑበት ምክንያት የጌታችን ዙፋን ከሚሸከሙት 4ቱ እንስሳት ምሳሌ ወንጌላዊያኑም አራት ሆነዋል ራእይ 4፡7 ፤6፡2 የሰው፣የንስር፣የአንበሳ እና የላም ናቸው።። በአራቱ አፍላጋት(ወንዞች)ይመሰላሉ።።እነዚህም ከገነት ከአንድ አጸ ሕይወት ስር መንጭተው ይህን ዓለም ዙረው አጠጥተው እጽዋትን ከመድረቅ ወደ ልምላሜ፣ከልምላሜውም ጽጌ(አበባ) ከጽጌ ወደ ፍሬ ያደርሳሉ።።ልክ እንደዚሁ አራቱ ወንጌላዊትም ወንጌልን ከአንድ ጌታ ተምረው ይህን ዓለም ዙረው አስተምረው ምዕመናንን በኃጥያት ከመድረቅ ወደ ልምላሜ ንሰሐ፣ከልምላሜ ንሰሐ ወደ ጽጌ ትሩፋት ወደ ፍሬ ክብር ያደርሳሉና።።
በአራቱ አዋክብት ይመሰላሉ እነዚህም አራቱ ክዋክብት ሀልመልሚሊክ ምልክኤል ምኤል ንርኤል በመባል ይጠራሉ።።
በአራቱ ወቅቶች ይመሰላሉ፣እነዚህም ጸደይ ክረምት መጸው ሐጋይ(በጋ) ተብለው ይጠራሉ።።
ጸደይ፡- የዘር ወቅት ነው ማቴዎስ በዚህ ይመሰላል ምክንያቱም የዘር ምሳሌን ከሁሉ ይልቅ አምልቶ አስፍቶ ጽፏልና
ክረምት፡-የውሀ ወር ነው ማርቆስ በዚህ ይመሰላል ምክንያቱም ወንጌሉን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ይጀምራልና
መጸው፡- የነፋስ ወር ነው ሉቃስ በዚህ ይመሰላል ምክንያቱም በነፋስ አምሳል መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ ተናግሯል እንዲሁም እመቤታችን ‹‹መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑል ኃይልም ይፀልልሻል›› እያለ ጽፏልና
ሐጋይ(በጋ)፡-ወርሀ እሳት ነው ዮሐንስ በዚህ ይመሰላል ምክንያቱም እርጥበት የሌለበት ደረቅ ወር ነው መስተጻረር መስተቃረን የሌለበት ደረቅ ቃል በመጀመሪ ቃል ነበር...እያለ ጽፏልና
እንዲሁም አራቱ ወንጌላውያን ሁለቱ ከሐዋርያት ሁለቱ ደግሞ ከአርእድት ወገን ናቸው።።
ለምን ሐዋርያት ብቻ ያልጻፉት?
ጌታ ወንጌሉን ሐዋርያት ጨርሰው እንዲድፋት ቢያደርግ ኖሮ አርድእት ለማስተማር ሲወጡ እናንተንማ ማን ይሰማችኃል የውጭ ሰው ናችሁ የውጭ ሰዎችማ ብትሆቱ ወንጌልን በዳፋችሁ ነበር ብለው አይሁድ ትምህርታቸውን ከከመቀበል ወደኃላ ባሉ ነበር።።
የአርድእት ክብር በአይሁድም ዘንድ ሆነ በክርስትያኖች ባልታወቀ ነበር።።አሁን ግን አርድት በጌታ ዘንድ የከበሩ መሆናቸውን ወንጌልን ለማዳፍ ታወቀ።።
ለምን አርድእት ብቻ ያልጻፉት?
ስለ ወንጌል ክብር

በአጠቃላይ ወንጌል በአርድእት ብቻ ተጽፎ ቢሆን ኖሮ ይህችማ ተርታ ሕግ ናት ደጊቱማ ሕግ ምሥጢረ ታምራትን በቤተ ኢያኢሮስ ምሥጢረ መንግስትን በደብረ ታቦር ምሥጢረ ምጽአትን በደብረዘይት ምሥጢረ ፀሎትን በጌቴ ሰማኒ ባዩ አዕማደ ምድር በተባሉ በልበ ሐዋርያት ቀርታለች በማለት አይሁዳ ደገኛይቱን ሕገ ወንጌል ከመቀበል በተከላከሉ ነበር።።

1.1 የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል

በኢ/አ/ተ/ቤ/ክ ትውፊት መሠረት የቅዱስ ማቴዎስ አባቱ ዲቁ እናቱ ክሩትያስ ይባላሉ።።በማርቆስ ወንጌል ላይ የአባቱ ስም አልፍዮስ ተብሎ ተጠርቷል።።ይህም የዲቁ ሌላ ስሙ ነው/ማር፡14/ የመጀመሪያ ስሙ ሌዊ ስሆን ማቴዎስ የሚለውን ስም ያወጣለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።።ትርጉሙም የተመረጠ ማለት ነው።።

ማቴዎስ የቀድሞ ሥራው ቀራጭነት(ግብር ሰብሳቢ) ሲሆን ይሠራበት የነበረው ቦታ በገሊላ ባሕር አጠገብ በምትገኘው ደማቂ ቅፍረናሆም ከተማ ነበር።።ከቅፍረናሆም ገብያ ወደ ገሊላ ባሕር ወደብ በሚወስደው ዐብይ መንገድ ዳር ሱቅ ከፍቶ ነጋዴዎችን ቀረጥ ያስከፍል ነበር።።ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ ሲያስተምር ወደ ሚቀርጥበት ቦታ ጠጋ ብሎ‹‹ተከተለኝ››አለው።።ቅዱስ ማቴዎስ እርሱ የሚሠራውን አስቦ ደሀችን በነዳ የሚያበለ ድውያንን በነዳ የሚፈውስ ሲያገኝ ተገርሞ ሥራውን እርግፍ አድርጎ ትቶ ተከተለው።።አባቶቻችን ቅዱስ ማቴዎስን ‹‹የቀም ተስካሩን አውጥቶ ጌታን የተከተለ ሐዋርያ›› ይሉታል።።ለሐዋርያነት በተመረጠ ጊዜ በቤቱ ደግሶ ጌታን ጋብዞ ድሆችን መጽውቶ ተከትሎታልና።።/ማቴ 9፡10-13/

ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በፍልስጤም፣በፋርስ፣በባቢሎን፣በኢትዮጵያ ወ.ዘ.ተ እንደሰበከ ይናገራል።።ዩሐንስ አፈወርቅ በበዓለ ሃምሳ ድርሳኑ እንደገለጠው በቤተክርስቲያን ታሪክ በኢትዮጵያ መጀመሪያ ወንጌልን የሰበኩት በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው በነበሩበት ወቅት በሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ካመኑት 3ሺ ምመናን መካከል የነበሩት ኢትዮጲያውያን ሲሆኑም ቀጥሎም ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ነው።። የቅዱስ ማቴዎስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ከእነዚህ በኃላ ነው።።

ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በኢትዮጵያ ወንጌልን እንዳስተማረ የቤተክርስትያን ታሪክ ፀሐፊ ሩፊኖስ አረጋግጧል።የአገራችን ሊቃውንትም ያስተማረው በትግራይ በስተ ምአራብ በአድዋ አውራጃ ልዩ ስሙ ናዕዴር በተባለ ቦታ መሆኑን ይናገራሉ።አንድ በአረበኛ የተፃፈ ስንክሳር ደግሞ በ ገፅ 76 ላይ ወንጌላዊው ማቴዎስ በትግራይ እንደሰበከ ይገልፃል።ሊቃውንተ ቤ/ክ ለዚህ የሚያቀርቡት ማስረጃ የራሱን ወንጌል ነው።ቅዱስ ማቴዎስ ከሌሎች ወንጌላውያን ተለይቶ የሰብዓ ሰገልን (የጥበብ ሰዎችን)ታሪክ የፃፈው በነዚህ አገሮች በማስተማሩ ነው ይላሉ።

«የተርሴስና የደሴቶች ነገስታት ስጦታን ያመጣሉ፤የዓረብና የሳባ ነገስታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ» መዝ 71 (72) ፥40 ባለው የቅዱስ ዳዊት መዝሙር የተርሴስና የደሴቶች የተባሉት ፋርስና ባቢሎን ሲሆን የዓረብና የሳባ የተባሉት ደግሞ የመንና ኢትዮጵያ ናቸው።

ከጥንት ዘመን ጀምሮ ከኢትዮጵያ በስተምሰራቅ ያለው ሀገር እስከ ሕንድ ድረስ ያለው ምስራቅ እየተባለ ይጠራል።ማቴዎስ በወንጌሉ ‹‹ከምስራቅ የመጡ›› ያለው በዚህ መሰረት ነው።ገድለ ሐዋርያት ቅዱስ ማቴዎስ በግሪክ(አጵሎን የተባለ ጣዖት ይመለክበት በነበረ ቦታ)እንዳስተማረ ይናገራል።በመጨረሻ ግን በፍልስጥኤም ሲያስተምር የአይሁድና የአረማውያንንም ትምህርት በመቃወሙ ድውያንን ሲፈወስ አጋንንት ሲያወጣ በማየታቸው የሀገሩ ሰዎች ወደ እስር ቤት ጣሉት።

በእስር ላለ ያጋጠመውን እስረኛ ተአምር ነግሮ ከጌታው ቁጣ በማዳኑ ወሬው በሀገሩ ሁሉ በማቴዎስ ላይ በመዳረሱ ይህንን የሠሙት መኳንንትም ማቴዎስን ለንጉሡ ከስሱት።ንጉሡም በመኳንንቱ ተመርቶ በማቴዎስ ላይ ሞትን ፈረደበት።ጥቅምት 12 ቀን አንገቱን ተሰይፎ አረፈ።

የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል በምራፎች ብዛት የመጀመሪያውን ወንጌል በመሆን 28 ምዕራፎች ይዟል።የተፃፈው ከቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ቀጥሎ በ 58 ዓ.ም አካባቢ ነው።የጌታችን ትምህርት በሰፊው በማቅረብ ቀዳሚውን ስፍራ ይዟል።በዚህም አቀራረቡ ከዮሐንስ ወንጌል ጋር ሲዛመድ ከሉቃስና ከማርቆስ ወንጌል ይለያል።ወንጌሉን የፃፈው ለአይሁድ በመሆኑ ከ 150 በላይ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን አቅርቧል።በነዚህም የተናሳ ብሉይ ኪዳንን አብዝቶ በመጥቀስ ከሌሎች ወንጌሎች ይበልጣል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀድሞ በነብያት የተነገረለት መሲሕ መሆኑን ለማስረገጥ ሲል አንድን ታሪክ ከዳፈ በኋላ በነብይ የተጻፈው ብሎ ይመሰክራል።ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ትውፊትን በብዛት የተጠቀመ ሐዋርያ ነው።ማቴዎስ ወንጌልን ስለፃፈበት ቋንቋ ሦስት ዓይነት ሐሳብ ቀርቧል።

በዕብራይስጥ፡-የቤተክርስቲኒያችንን ሊቃውንት ጨምሮ ብዙ ምሁራን የተስማሙት ቅዱስ ማቴዮስ ወንጌሉን በዕብራይስጥ ቋንቋ ጻፈው በሚለው ሐሳብ ነው።። ነገር ግን እስካሁን ድረስ የዕብራይስጡ ዋና ቅጂ አልተገኘም።።

በአረማይክ፤-ፓፒየስ የተባለው አባት በ 2 ኛው ክ/ዘመን እንደገለጠው ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ አስቀድሞ የጌታችንን ትምህርቶች በአረማይክ ቋንቋ ሎጂያ በተባለ መጽሐፍ ሰብስቦት ነበር።።በኋላም ወንጌሉን ሲጽፍ የጌታችንን ትምህርቶች የገለበጠው ከዚህ መጽሐፍ ነው

በግሪክ፤- አብዛኞቹ ጥንታውያን ቅጂዎች የሚገኙት በግሪክ ቋንቋ በመሆኑ በግሪክ ቋንቋ ተጻፈ የሚል ሀሳብ አለ።

የማቴዎስ ወንጌል ከማርቆስ ወንጌል ቀጥሎ በሁለተኛነት ተጽፎ እያለ የመጀመሪያውን ተርታ ያገኘበት ዋናው ምክንያት አቀራረቡ ለብሉይና ሐዲስ ኪዳን ድልድይ ስለሆነ ብሉይ ኪዳን ትንቢትና ምሳሌ በሐዲስ ኪዳን መፈጸሙን ስለሚያሳይ ነው።።ወንጌሉን የጻፈው በምድረ ይሁዳ ተቀምጦ ሳለ በሶሪያ ውስጥ የሚገኝ በአንጾኪያ ከተማ ነው።።

የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል የተጻፈበት ምክንያት

ሀ. አይሁድ ጌታን በድንግልና አልተወለደም ብለው ስለነበር እመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለአባት መወለዱን ለመመስከር

ለ. አሪትን ሊሸር መጣ ብለውት ስለነበር አሪትን ሊፈጽም እንጂ ሊሸር አለመምጣቱ ለማስረዳት

ሐ. ቡበሉይ ኪዳን ስለመሲሕ መምጣት የተነገሩ ትንቢቶች በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተፈፀመ ለመግለፅ

1.2 የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል

እናቱ ማርያም አባቱ አርስጦቡሎስ ይባላሉ።።የማርቆስ እናት ማርያም ባውፍልያ ቤቷን ለክርስቲያኖች መሰብሰቢያነት የሰጠች ደግ ሴት ነበረች።።ጌታም የመጀመሪያውን የሐዲስ ኪዳን ቁርባን ለሐዋርያት ያቆረባቸው በእርሷ ቤት ነው።።በበዓለ ሃምሳም መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የወረዳለቸው በእርሷ ቤት ተሰብስበው ሲጸልዩ ነው።።ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ከታናሿ እስያ እስከ ሮም ድረስ ሰብኩዋል።።በጫማ ሠፊው በአንያኖስ አማካኝነት የመጀመሪያው የግብፅ ቤተክርስቲያን በአናንያኖስ ቤት ተመሠረተች።።በግብፅ ቤተክርስትያን የትንሳኤን በዓል ሲያከብር ጣዖት አምላኪዎች ተነስተውበት በማሰርና በማንገላታት ከተሰቃየ በኋላ ሚያዚያ 30 ቀን ዐረፈ።።

የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ከወንጌላት ሁሉ አጭሩ ወንጌል ነው።16 ምዕራፎችም ይዟል።ወንጌሉን የፃፈው ለሮማውያን በመሆኑ ከሌሎች ወንጌላውያን (ቅዱስ ማቴዎስና ዩሐንስ) የተለየ አገላለጥና አፃፃፍ ተጠቅሟል።።የተፃፈት ቋንቋ ሮማይስጥ ነው።።ቅዱስ ማርቆስ ወንጌሉን የፃፈው ለአረማውያን በመሆኑ የአረማይክን ቃላትና የዕብራውያንን ባህል ሊያውቁት ስለማይችሉ ተርጉሞ አስቀምጦላቸዋል።።ለምሳሌ፡-

ቦአኔርጌስ፡- የነጎድጓድ ልጆች(3፥17)

ጣቢታ ቁሚ፡- አንቺ ብላቴና ተነሽ(5፥41)

ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ፡- አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ

የማርቆስ ወንጌል የተጻፈበት ምክንያት

ከሮማውያን(ከአሕዘብ) ወገን ወደ ክርስትና ሃይማኖት ተመልሰው ላሉ በሃይማኖት በምግባር እንዲጸኑ

ሮማውያን(አሕዛብ) አማልክቶቻቸውን የሚያውቋቸው በኃይላቸው ስለነበር በወንጌሉ የኢየሱስ ክርስቶስን ኃያልነት፣የአለም ሁሉ ንጉሥና ፈጣሪ መሆኑን እንዲሁም የማዳን ሥራውን በመግለጽ ያለመኑትን ለማሳመን ጽፏል።አንዳንዴ የለቲን፣የአረማይክና ሌሎችንም ቃላት ትርጉማቸውን ለማስረዳት ጽፎላቸዋል።

1.3 የቅዱስ ሉቃስ

ቅዱስ ሉቃስ ወንጌላዊ ሀገሩ አንጾኪያ ሲሆን በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተነሱት ቅዱሳን አንዱ ነው።ቅዱስ ሉቃስ የሕክምና ሙያውን (ቆላ 4፣14) ያጠናው ከአቴናና ከእስክንድሪያ ነው።የሥነ ስዕል ችሎታም ነበረው።ቅዱስ ሉቃስ በሰማዕትነት እስካረፈበት ሰዓት ድረስ የቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙር በመሆን አገልግሎታል። (2 ኛጢሞ 4፣11)

ቅዱስ ሉቃስ በድልማጥያ ወንጌልን በመስበክ ላይ እያለ አይሁድና ካህናተ ጣዖት ተባብረው ትምህርቱን በመቃወም ተነሱበት። መስከረም 20 ቀን 58 ዓ.ም አይሁዳና አረማውያን ጉባኤ አድርገው ነገር በመሥራት ለንጉስ ከሰሱት።እሱን ለመያዝ 200 ወታደሮች በተላኩበት ወቅት በመንፈስ ቅዱስ በመረዳቱ ያስተማራቸው የነበሩትን ምዕመናን ወደ የቤታቸው ላከና ወደ ባሕር ተጠግቶ አንድ ዓሣ አስጋሪ ጋር ቀርቦ ወንጌልን ካስተማረው በኃላ በመጨረሻ ‹‹እንካ እነዚህ የሕያወትን መንገድ ይምሩሃል››በማለት የያዛቸውን መጻሕፍት ሁሉ ሰጠው።ያም ዓሳ አስጋሪ እጅግ ተደስቶ እቃ በማያስቀምጥበት ቦታ በክብር አኑራቸው።

ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ወንጌሉን የጻፈበት ሀገር አካይያ ሲሆን የጻፈው በግሪክ(ዕርዕ) ቋንቋ ነው።ወንጌሉ የተጻፈው ከ 58-60 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ቅዱስ ጳውሎስ በእስር ላይ እያለ ባገኘው አረፍት ነው።ሉቃስ ወንጌል 24 ምዕራፎች የያዘ መጽሐፍ ነው።

የሉቃስ ወንጌል ‹‹የአሕዛብ ወንጌል››፣ስባኬ መንፈስ ቅዱስ ‹‹ስባኬ ጸሎት››፣‹‹ወንጌለ አንስት››እየተባለ ይጠራል።

‹‹የአሕዛብ ወንጌል››፡-እየተባለ የሚጠራው ወንጌሉ የተጻፈው ለአሕዛብ በመሆኑ ነው።

‹‹ስባኬ መንፈስ ቅዱስ››፡-ምክንያቱም ስለ መንፈስ ቅዱስ ደጋ ደጋግሞ ይናገራልና

‹‹ስባኬ ጸሎት››፡-ከሌሎች ወንጌላት በበለጠ ሁኔታ ደጋግሞ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስና የእመቤታችን ድንግል ማርያምን ጸሎትን ጽፏልና።

‹‹ወንጌለ አንስት››፡-ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም ስለ ቅድስት ኤልሳቤጥ፣ስለ ማርያም አንተ እፍረ ወዘተ በስፋት ይናገራልና።

የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል የተጻፈበት ምክንያት

በሮም ግዛት ውስጥ የሚኖሩትን ወደ ክርስትና የተመለሱትን ለማጽናት ያልተመለሱትን ደግሞ ለመመለስ ጽፎላቸዋል።

ለሮም ባለስልጣን (ለቴዋፍሎስ) ለጥያቄው መልስ ለመስጠት ጽፏል።

ከሁሉም መጻሕፍት በበለጠ ሁኔታ የእመቤታችን ድንግል ማርያምን ፍቅርና እናትነት ለመግለጥ ጽፏል።

1.4 የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል

ቅዱስ ዮሐንስ ሀገሩ የገሊላ አውራጃ ሲሆን ከወንድሙ ከያዕቆብና (ከ 12 ሐዋርያት አንዱ የሆነ) ከአባቱ ከዘብዴዎስ ጋር ዓሳ እያጠመደ ይኖር ነበር።አናቱም ከ 36 ቅዱሳት አንስት አንዷ እንደሆነችና ማርያም እንደምትባል የቤተክርስትያን ትውፊት ይመሰክራል።ማቴ 27፣46

የዮሐንስ የተለያዩ ስሞችና ምክንያታቸው

ፍቁረ እግዚእ በኑሮው ጌታን በመምሰል ጌታን ይወደው ስለነበር

ነባቤ መለኮት(ታዖሎጎስ) ነገረ መለኮትን ከሌሎች ወንጌላውያን በበለጠ አምልቶና አስፍቶ በጥልቀት በማስተማሩ

ቦአጌርጌስ(ወልደ ነጎድጓድ) የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በመግለጡና ለጌታችን ባለው ቅንአት ባሳየው የሀይል ስራ

ባለ ራእይ(አቡቀለምሲስ-በግሪክ) ኃላፍያንንና መፃእያንን በራእይ በመግለፁ

ቁጽረ-ገጽ(ፊቱ በሀዘን የጠቆረ) በእለተ አርብ በእግረ መስቀል ተገኝቶ የጌታችንን መከራ መስቀል በማየቱ ከዚያች እለት ጀምሮ ፊቱ በሀዘን ጠቁሯል

የዮሐንስ ወንጌል ከትረካ ይልቅ ነገረ መለኮታዊ ይዘት ስላለው ከሌሎቹ ወንጌላት ይለያል።ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ከጸራቅሊጦስ በኃላ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በኢየሩሳሌም በአንጾኪያ በመቅዶንያ በእስያ ከተሞች በተለይም በኤፌሶን አስተምሯል።ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን፣ 3 ቱን መልእክታትና ራእዩን የፃፈ ሐዋርያ ነው።ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ከፍጥሞ ደሴት ሲመለስ በኤጅያን ባሕር ወደብ በ 96/98 ዓ.ም አካባቢ ነው።

የቅዱስ ዩሐንስ ወንጌል የተጻፈበት ምክንያት

1 ከሶስቱ ወንጌላት የጎደለውን ለመሙላት

2 ቅድመ ዓለም የነበረውን ሥጋን የተዋሐደውን ትንቢት የተነገረለት ሱባኤ የተቆጠረለት መሲሕ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለመግለጥ ጽፏል።

3 የሰው ልጆች ሁሉ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ መሆኑን አምነው የዘለዓለም ሕይወት የሚያገኙ መሆኑን ጽፏል።

4 የሕይወት አወንጀራ የዓለም ብርሃን የበጎች በር መልካም እረኛ ትንሣኤና ሕይወት መንገድ እውነትና ሕይወት ‹‹እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ›› የሚለው የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና አምላክነት የሚገልጽ መሆኑን ለማስረዳት ጽፏል።

2 የታሪክ ክፍል (የሐዋርያት ሥራ)

ሐዋርያት የሚለው ቃል የሐዋርያ ብዙ ቃል ሲሆን ሐዋርያ ሖረ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ተጓዥ ማለት ነው።ሐዋርያት በአይሁዳውያን ዘንድ አለዋቂ ከሚባሉት የተመረጡ ናቸው።በተልኳቸውም ድውይ ሲፈውሱ ሙት ሲያስነሱ ጋኔን ሲያወጡና የወንጌል

ብርሃንነትን ሲመሰክሩ በሀገሀቡ ዘንድ ሞገስ አግኝተው ነበር።የሐዋርያት ሥራ የሚለውን መጽሐፍ የፃፈው ቅዱስ ሉቃስ ነው።በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ሉቃስ ሐዋርያት ያደረጉትን ሥራ በሰፊው ፅፏል።ሥራውንም የሚሰራው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነም ያስረዳል።

የቅዱስ ሉቃስ ዓይነተኛ ሐሳብ ሐዋርያት የኢየሱስ ክርስቶስን ትእዛዝ እየፈፀሙ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ወንጌል ለአለም እንዳዳረሱ ለማስረዳት ነው።ይህ መጽሐፍ እውነተኛ የክርስትና ጠባይን ስለሚገልፅ የተለየ የክርስትና መጽሐፍ ይባላል።ይኸውም ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ ዕርገቱ ከፃፈ በኃላ ከጳራቅሊጦስ ጀምሮ የመጀመሪያውን የቤ/ክ መሰረትና ህብረት፣የቤ/ክንን ታምራት ፣ የመጀመሪያውን ጥምቀት ፣ የመጀመሪያውን የቤ/ክ ስደት ፣የመጀመሪያዎቹን ሰማዕታት ፣ የመጀመሪያውን ሐዋሪያዊ ጉዞ ከአይሁድ አለም ወጥቶ ወደ አሕዛብ መሄዱን ፣ የመጀመሪያዎቹን የዲያቆናት ምርጫና ሹመት የሚያስረዳ ከመሆኑም በላይ ቤ/ክ ከምን ተነስታ ከምን እንደደረሰች የሚያሳይ ከፍተኛ ጠቃሚነት ያለው መጽሐፍ ነው።

የሐዋርያት ሥራ የተጻፈበት ምክንያት

የቅድስት ቤ/ክን አመሰራረትና ዕድገት ለመግለፅ

የርደተ መንፈስቅዱስን ሁኔታ ለማስረዳት

ቅዱሳን ሐዋርያት የኢየሱስ ክርስቶስን ትእዛዝ በመፈፀም ወንጌልን በአራቱም አቅጣጫ እንዳዳረሱ በመግለጥ የቅዱሳን ሐዋርያትን ሃይማኖትና ተግባር(ሥራ) እንድንከተል እውነተኛ የክርስትና ጠባይን ለማሳወቅ ፅፏል።የሐዋርያት ሥራ 28 ምዕራፎች አሉት

3 የሥርዓት ክፍል

ሥርዓት የሚለው ቃል ሠርዓ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጓሜውም አሰራር ደንብ መርሐ ግብር ማለት ነው።ይህም ሥርዓት በክርስቶስ ደም የተመሰረተች ቤ/ክ አምልኮቷን የምትፈፅምበት ሕዝበ እግዚአብሔርን የምትጠብቅበት ጸጋ የሚያሰጥ ቅዱስ ሥርዓት ነው።

የቤ/ክ እምነት ብቻ ሳይሆን ሥርዓቷም እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት የገለጠው ቅዱስ ሥርአተ አምልኮ ነው።የ/ኢ/አ/ተ/ቤ/ክ የአለት ተአለት መንፈሳዊ አገልግሎት የምትፈፅምበት የሥርዓተ ቤ/ክ መጻሕፍት አሏት።እነዚህም መጻሕፍት ሐዋርያትና ሊቃውንት በየጊዜው ለቤ/ክ መተዳደሪያ የወሰኑትና የደነገጉት ነው።

የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ምንጮች

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

የሊቃውንት መጻሕፍት

ቀኖናወ አበው(የአበው ቀኖና)

የሥርዓት መጻሕፍት ወ.ዘ.ተ. ናቸው።

ሥርዓትን መጠበቅና በሥርዓት መኖር አስፈላጊ እንደሆነና መንፈሳዊ ግዴታም እንዳለብን ዋነኛው የሥርዓት ምንጭ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።ለምሳሌ ‹‹...ምድርም ከሚቀመጡባት በታች ረክሳለች ሕጉን ተላልፈዋልና ሥርዓቱንም ለውጠዋልና›› ት.ኢሳ 24፣5

‹‹...ከሥርዓትህ የሚርቁትን አጎሳቆልካቸው›› መዝ 118፣118

‹‹...ያለሥርዓት የሚሔዱትን ገስጿቸው›› 1 ኛተሰ 5፣14

‹‹...ያለሥርዓት ከሚሔድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርክቶስ እንለምናችኃለን›› 2 ኛተሰ 3፣6 በማለት የሥርዓትን አስፈላጊነትና ለሥርዓት ሊሰጥ የሚገባውን ክብር ገልጸውልናል።

የቅድስት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መጻሕፍትን በሐዋርያት ቅዱስ ሲኖዶስ የተደነገጉ ናቸው።ሲኖዶስ ማለትም ስብሰባ ወይም ጉባኤ ማለት ነው።ይህም ሐዋርያት ከክርስቶስ ዕርገትና ርደተ መንፈስ ቅዱስ በኃላ ተሰብስበው የሰሯቸውንና የደነገጓቸው ቀኖናዎች ናቸው።

መጻሕፍቱ የተጻፉበት ቋንቋ

ስምንቱ የሥርዓት መጻሕፍት በመጀመሪያ የተፃፉበት እናት ቋንቋ ሱርስት (የሶርያ ቋንቋ) ነው።አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ በኃለኛ ዘመን እነዚህ የሕግና የሥርዓት መጻሕፍት በየቋንቋው ለመተርጎም መነሻ ሆነው ያገለገሉት ሰነዶች በሙሉም ሆነ በከፊል ተቀርጸው የተገኙት በግሪኩ ቋንቋ ስለሆነ መጻሕፍቱ በመጀመሪያ የተጻፉት በግሪክ /ልሳነ ጽርዕ/ ነው ይላሉ። ሱርስቱንና ግሪኩን መሠረት በማድረግ ወደ ላቲን(ሮማይስጥ)፣ ቅብጥ(ሳይቅና ማምፊቲቅ)፣ ዐረብኛና ግዕዝ ቋንቋዎች በተለያዩ ተርጓሚያን ተተርጉማል።/ፍትሐ ነገሥት መቅድም/

የሥርዓት ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት አከፋፈል

ሐዋርያት የሠራቸው የሐዲስ ኪዳን የሥርዓት መጻሕፍት ስምንት ሲሆኑ እነርሱም በአጠቃላይ በሦስት ይከፈላሉ።አከፋፈላቸውም እንደሚከተለው ነው።

መጽሐፈ ዲዲስቅልያና አራቱ መጽሐፍተ ሲኖዶሳት(ትዕዛዝ፣ግፅው፣አብጥሊስና ሥርዓተ ጽዮን)ሐዋርያት በየጊዜው እየተሰበሰቡ ያዘጋጇቸው መጽሐፍት ናቸው።

ሁለቱ ኪዳናት(መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊና ካልእ) ጌታችን ከትንሳኤው በኃላ የተናገራቸው ናቸው።

መጽሐፈ ቀለሜጦስ በሮም በኤጲስ ቆጶስነት ተሹሞ የነበረው የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀመዝሙር ቀሌሜንጦስ የፃፈው መጽሐፍ ነው።

(ፊሊ 4፣3)

በፍትሐ ነገሥት መጽሐፍ እንደተገለጠው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቁጥር 46 ሲሆኑ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ ስምንቱን የትምህርትና የሥርዓት መጻሕፍትን ጨምሮ 35 ናቸው።

3.1 መጽሐፈ ትእዛዝ

ትእዛዝ ማለት በቁሙ ከስራ አስቀድሞ የሚሰጥ የሚጸፍ የሚነገር ሕግ ሥርዓት ወይም አድርግ አታድርግ የሚል ፈቃድና ደንብ ነው። የመጽሐፈ ትእዛዝ ምልክቱ ወይም በአዕፅሮተ ቃል ልዩ መጠሪያው ረስጠብ በመባል ይታወቃል።ትእዛዘ ሲኖዶስ ከ 72 በላይ አንቀጾች ሲኖሩት እነዚህም

ሊቃነ ጳጳሳት ሥርዓተ ሲመት አተገባበር
ስለ መሰዋእት አቀራረብ
ስለ ንዋየ ቅድሳት ክብር
ሰለ ሥርዓተ ጥምቀት
ሰለ ሥጋ ወደሙ ክብር ወ.ዘ.ተ...የሚናገር መጽሐፍ ነው።

3.2 መጽሐፈ ግጽው

ግጽው ማለት በቁሙ የታየ የተለጠ ጉልህ ማለት ነው።ሐዋርያት ለቀሌምንጦስ የሰጡት ሁለተኛ መጽሐፍ ነው።የዚህ መጽሐፍ መሪ ምልክት ረስጠጅ በመባል እንደሚታወቅ ፍትሐ ነገስት ይናገራል።

መጽሐፉ የእግዚአብሔርን ሕልውና በማስረዳት ጀምሮ ሰለምሥጢረ ሥጋዌ ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ሰለማስተማሩና ስለሠራቸው ሥራዎች ይናገራል።መጽሐፉ 57 ያህል አንቀጾች ያሉት ነው።

3.3 መጽሐፈ አብጥሊስ

አብጥሊስ የመጽሐፉ ስም ሲሆን ትርጉሙ ቀኖና ማለት ነው።46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትንና 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በአጠቃላይ 81 መጻሕፍትን ሙሉ ዝርዝር ይዞ ይገኛል።

የአብጥሊስ መለያ መጠሪያው ወይም መሪ ምልክቱ ረስጠአ(ረስጣ) በመባል ይታወቃል።መጽሐፉ የሚናገረው ስለ ኤጲስ ቆጶሳት ሰለካህናት ሰለ ዲያቆናትና ምእመናን አጠቃላይ የስራ ድርሻና መንፈሳዊ ህይወት፣በስፋትም ሰለ ምስጢረ ንስሐ አሰጣጥና አተገባበር የሚያስረዳና የትምህርተ ሃይማኖትን የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነትና ምንነት የሚያትት ነው።82 አንቀፆች አሉት

3.4 መጽሐፈ ሥርዓተ ጽዮን

ሥርዓተ ጽዮን ቀኖናተ ሐዋርያት ወይም ትምህርተ ሐዋርያት ከሚባሉት የሐዋርያት ሲኖዶስ መካከል አንዱ ነው።ሐዋርያት ለስብከተ ወንጌል ወደ ዓለም ከመለካቸው በፊት በጽርሐ ጽዮን ተሰብስበው የሠሩትና የደነገጉት የቤተክርስትያን ሥርዓት ሕግና ትምህርት ነው።

የሥርዓተ ጽዮን መጽሐፍ መጀመሪያ የተጻፈበት ቋንቋ ጽርሕ ሲሆን በኋላ ግን ወደ አርበኞችና ወደ ግሪክ ቋንቋዎች ተተርጉሟል።የሥርዓተ ጽዮን መሪ ምልክቱ ‹‹ዓይን›› ነው።የሥርዓተ ጽዮን ቀኖና መጽሐፍ የሚገልጸው ስለ በዓለ አስተርእዮ(ኤጲፋንያ) ስለ እሁደ ሰንበት በዓል አከባበር ስለ ገሐድ ጾም ወዘተ ያትታል።የቀኖናቱ ብዛትም 30 የሚደርሱ ናቸው።

3.5 መጽሐፈ ኪዳን

ኪዳን ማለት ውል ስምምነት የፍቅርና የአንድነት መሀለ ሰላማዊ ህግ ትምህርት ምስጋና ሁለቱን ወገን (እግዚአብሔርንና ሰውን/ሰውንና ሰውን) አንድ የሚያደርግ ነው።ለሰው ረብና ጥቅም የሚሆን በተሰፋ የቆሙ ቢጠብቁት በረከት የሚያሰጥ ቢያፈርሱት ደግሞ ጉዳትና ጠብ የሚያመጣ ብዙ በረከትም የሚያሳጣ ነው። (ገላ 3፣15)

መጽሐፈ ኪዳን የኢየሱስ ክርስቶስና የሐዋርያት ቃል ከትንሳኤ - እርገት ያስተማራቸውና እየጠየቁት የመለሰላቸው ነው።ይህም ከእርገት በኋላ በጥንተ ስብከት ሐዋርያት ጽፈውታል።

ጌታ በመዋዕለ ሥጋዊ ሳለ ያስተማረው ወንጌል ሲባል ከትንሳኤው እስከ እርገቱ ያስተማረው ደግሞ ኪዳን ይባላል። ከሞተ በኋላ ተነስቶ ሰለምን ኪዳንን አስተማረ ቢሉ በመዋዕለ ሥጋዊው በፈቃዱ ለሰው ልጅ ድህነት ወንጌልን እንዳስተማረ ከሞተም በኋላ ተነስቶ ለሰው ልጅ ድህነት በፈቃዱ ኪዳንን አስተምሯል።መጽሐፈ ኪዳን የተባሉትም ሁለት መጽሐፍት ናቸው።

ሀ.መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ

‹‹ይህን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የኪዳን መጽሐፍ ዮሐንስ፣ጴጥሮስና ማቴዎስ እያጻፋቸው ጻፉት በዚህም ዓይነት መግለጫም ወደ ኢየሩሳሌም ላከው።››

መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ 59 አንቀጾች ያሉት መጽሐፍ ነው።ይህም ሰለ ስርዓተ ቤተ ክርስቲያን የዘወትር ኪዳናት ትምህርተ ጎቡአት እግዚአብሔር ዘብርሃናት ቅዳሴ እግዚእ በእንተ ቅድሳት ወ.ዘ.ተ...የሚናገር መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ ይዘት ሥርዓተ ጸሎትና ሥርዓተ ቅዳሴ ነው። ይህም ጸሎተ ኪዳን ዘእግኢ፣እንዲጸልዩ በተመደቡ ሶስት የኪዳን ጊዜያት(ጸሎተ ኪዳን ዘሰልስቱ ጊዜያት) ተከፍለው የሚገኙ ዘጠኝ ሥርዓተ ጸሎታትን (ዘጠኙ ኪዳናት የሚባሉትን) ይዟል።እነርሱም፡-

1.ኪዳን ዘመንፈቀ ሌሊት

ሀ.ለክ እግዚኦ ለገባሬ ኩሉ
ለ.አምለክ ብርሃን ለገባሬ ሕይወት
ሐ.ንሴልስ ለክ ዘንተ ስብሐት
2.ኪዳን ዘነግሀ
ሀ.እግዚአብሔር አብ ወሃቤ ብርሃን
ለ.እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ ስምዓነ ቅዱስ
ሐ.ንሴልስ ለክ ቅዱስ ስብሐት
3.ኪዳን ዘሠርክ
ሀ.ለክ ለአብ ዘኢይማሰነ መድኃኔ ነፍስነ
ለ.ንዌድሰክ እግዚኦ
ሐ.ለክ ዘእምልብነ ናቸው
ለ መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ

እንደ መጀመሪያው የኪዳን መጽሐፍ በአንቀጽ የተከፋፈለ አይደለም።በሥርዓት ቅዳሴው መጽሐፍ የቅዳሴ እግዚእ መግቢያ ላይ እንደተገለጸው መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ ደግሞ ወጥ ሆኖ ስለ ካህናት ሹመትና አገልግሎት ስለ ንዑስ ክርስቲያን ጥምቀትና ምሥጥረ ቁርባን እንዲሁም የሐሳዊ መሲሕን የጥጦስን ነገር በመግለጽ ስለ ክርስቶስና ስለ ዳግሞ ምጽአት የሚናገረ መጽሐፍ ነው።በአጠቃላይ የመጽሐፈ ኪዳን ካልዕ መጽሐፈ ስለሐሳዊ መሲሕና ተከታዮች በይበልጥ በስፋት ይናግራል።

3.6 መጽሐፈ ዲድስቅልያ

ዲድስቅልያ የመጽሐፉ ስም ሲሆን ትርጉሙም ትምህርት ማለት ነው።ይህም የኢ/አ/ተ/ቤ/ክ 35 የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ አንዱና ጥንታዊው ነው። <<ዲድስቅልያ ዘቅዱሳን ሐዋርያት>> ይባላል። መጽሐፉ ቀድሞ ሲል ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተተርጉሞና ተጠብቆ ኖሯል።አንዲያውም ከፍተኛ ዋጋው ቀደም ብሎ ስለታወቀ ከእንግሊዘኛ ትርጓሜው ጋር በአውሮፓ ታትሞል።ይህ መጽሐፍ የቅዱሳን ሐዋርያት አስተምህሮ የሥርዓት ክፍል ሲሆን 43 አንቀጾችን የያዘ መጽበለ ትምህርት ወተግሣጽ ነው።እነዚህም ስለሰው ልጅ ሕይወትና ሞት ስለ ፍቅረስብ እና ፍቅረእግዚአብሔር ስለ ምሥጢረ ጥምቀት ስለጸምና ጸሎት ሰለ ምሥጢረ ቁርባን ሰለ ካህናት ክብርና አገልግሎት ሰለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና እንዲሁም በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሰለሚፈፀሙ የተለያየ ምስጢራት ይናገራል። መጽሐፈ ዲድስቁልያ አበይትና ንዑሳን አንቀጾች አሉት።በእያንዳንዱ አብይ አንቀጽ ውስጥ ብዙ የተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች ይገኛሉ።

3.7 መጽሐፈ ቀሌምንጦስ

መጽሐፉ ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውና ቅዱስ ቀሌምንጦስ ከእርሱ አግኝቶ የጻፈው ነው።የቀሌምንጦስ መጽሐፍ በአዕጽሮተ ቃል ልዩ መጠረያው "ጴጥ" ሲሆን ትርጉሙም ጴጥሮስ ማለት ነው ይዘቱም ሥርዓተ ቅዳሴያዊ ቅርጹን አስመልክቶ ስለጽላት ኪዳን ቡራኬ ማለትም በኤጲስ ቆጳስ አዲስ ቤተመቅደስ የሚባረክበትን ሥርዓት ሥርዓተ ጥምቀትና በእጅ መንሻና መተያያ ጥምቀት እንደማይፈቅድ ስለሥርዓተ ቁርባን ወዘተ ይናገራል። በቀኖናዊ ክፍሉም ስለ ሰማዕታትና ስለ ክ በዓላት ስለ ሰንበተ ክርስቲያን የአረፍተ ቀን መሆን በሰሙነ ሕማማት ምዕመናን ከተግባረ ሥጋ ማረፍ ግዴታ ስለመሆኑ ያትታል።/ቀኖና ፩-፲፭/ በትውፊትም ቅዱስ ቀሌምንጦስ የሮማ ጳጳስ መሆኑ ይነገራል። ድህረ ልደተ ክርስቶስ የዓው ቀዳማዊ ቀሌምንጦስ የቤተ ክርስቲያን አበው መምህራን በመገደላቸው ምክንያት አለመግባባት ወደተፈጠረበት የቆሮንጦስ ቤተ ክርስቲያን በሮማው ጳጳስ መልእክት ነው።መልእክቱ የ 70 ው ሊቃናት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገራቸውና እንዲሁም ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት በተለይ ከዕብራውያን መልእክት የተወሰደ መሆኑ ተገልጿል።

የመጽሐፈ ቀሌምንጦስ ክፍሎች

መጽሐፉ በስምንት ዐበይት ክፍሎች የሚከፈል ሲሆን የእያንዳንዱ ክፍል ሐሳብ በከፊል እንደሚከተለው ቀርቧል።

ክፍል 1
መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገ በኃላ ሐዋርያትን በሁሉም አቅጣጫ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ እንደያስተምሩ እንደለካቸው
ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ትምህርት ላይ እንደተመሰረተች
ከአዳም ጀምሮ ስለለው አጠቃላይ የዘር ሐረግ
ሰለ ገነትና ሰለታላለቅ አባቶች የቀረበ ሰለምታ(ምስጋና)
ከገነት ወጥተው ወደ ደብረ ቅዱስ ሰለ ገቡ ሰዎች
ክፍል 2
ቀሌምንጦስ የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀመዝሙር ሆኖ ሰለመመረጡ
ሰለቀሌምንጦስ ሕይወትና አጠቃላይ ኑሮው
የቀሌምንጦስ መንፈሳዊ አገልግሎት
ክፍል 3

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ለሐዋርያት ያደረገውንና ያስተማረውን ሁሉ ለቀሌምንጦስ እንደነገረው በአገልግሎቱ እንዲጸና እንደመከረው

ክፍል 4

እግዚአብሔር ለቅዱስ ጴጥሮስ ስለሳየው ራእይና ተአምራት
ስለሥልጣነ ክህነት ከጳጳሳት እስከ ዲያቆናት አጀማመርና አሰጣጥ
ስለዓለም አፈጣጠርና ሁኔታ
ስለዳግም ምጽአት እንዲሁም ስለጻድቃንና ኃጥአን ሁኔታ
ስለመንፈስ ቅዱስ መውረድና ሁሉን እንደሚገልጥላቸው ይናገራል

ክፍል 5

በሰው ልጆች በሰማይና በምድር ላይ ስለሚሆነው ነገር ሁሉ ቅዱስ ጴጥሮስ ለቀሌምንጦስ እንደነገረው
ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ስለመወለዱ
ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ግብፅ ስለመሰደዱ
ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግብፅንና በዙሪያዋ ያሉ አውራጃዎች ከአምልኮተ ጣዖት ነጻ ስለማድረጉ
ወደ ገሊላ ስለመግባቱ ይናገራል

ክፍል 6

እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረው ሥርዓተ ደብተራ ለቅዱስ ጴጥሮስ እንደተነገረው ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ ለቀሌመንጦስ ይህን ሥርዓት እንዳስተማረው
ሙሴ እንደ ሊቀጳጳስ ሆኖ አሮንና ልጆቹን ስለመሾሙ
ቅዱስ ጴጥሮስ ለቀሌመንጦስ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንዳስተማረው
ስለ ሙሴና ስለጴጥሮስ ንጽጽራዊ ትምህርት
በክርስቶስ የሚያምን የክርስቶስን ሥራ እንደሚሰራ
ቅዱሳን ሐዋርያት ድውያንን ስለመፈወሳቸው
ንጽሐና በረከት ለመቀበልም ለመስጠትም አስፈላጊ እንደሆነ
ክርስቶስ ራሱን ለቤተ ክርስቲያን መስዋእት አድርጎ እንዳቀረበ ይናገራል

ክፍል 7

ስለ ክርስቶስ አምላክነትና አዳኝነት
ስለዲያብሎስ ክፋትና ሸንፈት
ስለ ሙሴ በትርና ስለ ክርስቶስ መስቀል ምሳሌነት
ስለ ቅዱሳን ሐዋርያት አስተምህሮ
ኖህ መርከቡን እንዲሰራ ስለመታዘዙ ይናገራል።

ክፍል 8

ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ንሰሐ አስፈላጊነት ያለውና ያስተማረው
ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ብጹእ ስለመባሉ
ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ጴጥሮስ የቃል መሰረትነት እንደምትሰራ
ቅዱስ ጴጥሮስ የመንግስተ ሰማያትን ቁልፍ ስለመቀበሉ ወ.ዘ.ተ...ይናገራል

ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ስምንቱ የሐዲስ ኪዳን የሰርዓት መጽሐፍት ይዘታቸው በትምህርት፣በትንቢት በይበልጥም በሰርዓተ ቤ/ክ ላይ ያተኩራል።

4 የመልእክታት ክፍል

እነዚህ መልእክታት ተብለው የሚጠሩት የሐዲስ ኪዳን ክፍሎች አጠቃላይ የትምህርት መጻሕፍት ይባላሉ።የተጻፉትም ለግል ሰዎች ለቤተሰብ ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለማኅበር በቀጥታ ትምህርት ተግሳጽ ምክር መሠረተ ሃይማኖት ሥነ ምግባራዊ ሕይወትን በአጽንኦት የሚገልጹና የሚያስተምሩ ናቸው።

አጠቃላይ መልእክታቱ በሶስት ይከፈላሉ።
ለማኅበር የተላኩ መልእክታት ሮሜ፣ፊልጵስዩስ ወ.ዘ.ተ...

ለግል የተላኩ መልእክታት ፊልሞና፣ጢሞቴዎስ፣ቲቶ፣ሁለተኛ የዮሐንስ መልእክት ወ.ዘ.ተ...ናቸው
ለዓለም አቀፍ መልእክት የዕብራውያን መልእክት (ለእስራኤል ዘሥጋ እስራኤል ዘነፍስ)፣1ኛ ዮሐንስ መልእክት ወ.ዘ.ተ...ናቸው።

ተ.ቁ	መልእክቱን የፃፉት	ብዛት
1	ቅዱስ ጳውሎስ	14
2	ቅዱስ ዮሐንስ	3
3	ቅዱስ ጴጥሮስ	2
4	ቅዱስ ያዕቆብ	1
5	ቅዱስ ይሁዳ	1
	ጠቅላላ ድምር	21

4.1 የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት

የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ዘመናቸውንና ቅደም ተከተላቸውን ተከትለው ባይጠረዙም የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት 14 ናቸው።
የጥራቱም ሁኔታም የሚለያየው እንደመልእክቱ ከባድነትና እንደ የሀገሩ የቤተክርስትያን ታላቅነት ነው።መልክታቱንም በክፍል እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን።
የመጀመሪያው ክፍል ሁለቱ ወደ ተሰሎንቄ የተጻፉትን ይይዛል።እነዚህም በሁለተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው በ52 እና 53 ዓ.ም እንደተጻፈ ይነገራል።እነዚህ መልእክታት ምሥጢረ ምጽአትን በሚመለከት የሚናገሩ ናቸው።
ሁለተኛው ክፍል ሁለቱን የቆሮንጦስ መልእክታትንና የገላትያን የሮሜን መልክታት ይይዛል።እነዚህ በ3ኛው የሐዋርያው ጉዞው በ56 እና በ58 ዓ.ም መካከል የተጻፉ ናቸው።በነዚህም ጊዜ አይሁድ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ቤተ ክርስቲያንን የተቃወሙበትን የጳውሎስንም ዛፍ ሆነ ብለው ያበላሹበት ጊዜ ነበር።
ሶስተኛው ክፍል ቅዱስ ጳውሎስ የመጀመሪያው የሮም እስራቱ ጊዜ በ62 እና በ63 ዓ.ም የተጻፉ ናቸው።እነዚህም ወደ ፊሊጵስዩስ ወደ ኤፌሶን፣ወደ ቆላስይስና ወደ ፊልሞና የተጻፉ መልክታት ናቸው።እነዚህ ስለክርስቶስ ማንነት አስፋፍተው የሚናገሩ ናቸው።
አራተኛው ክፍል በመጀመሪያ ከእስራት የተፈታበት ከ63-68 ዓ.ም የተጻፉት 1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስና ቲቶን ይይዛል።እነዚህ መልእክታት የካህናትን ተግባርና የጠባቂዎችንም ኃለፊነት ስለሚገልጡ የጠባቂነት መልክታት ይባላሉ።የቅዱስ ጳውሎስ መልክታት የይዘት ተመሳሳይነት አላቸው።ይኸውም የሚያመለክተው በአንድ መንፈስ ገለጭነት መጻፋቸው ነው።የመልክታቱም ጠባይ አጠቃላይ 6 ክፍል አለው።
ሰለምታ፡-በሰላምታ አገለለጡ ሰፊ ትምህርት ስለሚገኝበት የመሳብ የማቅረብ ወገንም የማድረግ ኃይል አለውና በሰላምታ መጀመርን ተግባር አደረገው።የሰላምታ አሰጣጡ ‹‹ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን›› የሚል ነው።ይኸውም የዕብራውያን ሰላምታ በክርስቶስ የሚሰጠውን ጸጋ እንደሚያገኙ የሚያነቃቃ ነው።
ምስጋና፡-ወደ ዋናው ርእሱ ከመግባቱ በፊት ስለ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታው እግዚአብሔርን አመስግኖ ጽሐፉን ይቀጥላል።
መሠረት ሃይማኖትን ማሳወቅ፡-አንደሚጽፍበት ምክንያት ይለያል እንጂ የያዘውን ርእስ አተኩሮ የርእሱን ዓለማ አስፋፍቶ ይገልጣል።እንዲሁም መልክቱን ለመጻፍ የተነሳሳበትን ምክንያት በመከተል ሰፊ ትምህርት ሃይማኖት ይሰጣል።
ተግባራዊ ትምህርት፡-የክርስትና ምግባር እንዴት መሆን እንደሚገባው አስረድቶ በግልጥ ይፅፋል።ሃይማኖትንና ምግባርን በማዋሐድ ያስተምራል።
ለግል ሰዎች፡-ለጳውሎስ የፍቅሩ መግለጫ ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን አባል የሚሰጠው አክብሮትና አገለለጥ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን እንዴት የሁሉ እናት እንደሆነች የሚያስረዱ ምልክቶች ናቸው።
የራሱ መሆኑን ማረጋገጥ፡-በዚህ ዘመን ይተለለፍ ከነበሩት የሐሰት መልእክታት ለመለየት የሚገለጥበት መንገዱ ነው።ይኸውም ‹‹ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ የጻፍሁት እኔ ነኝከእኔ መልእክት ሁሉ የሚገኘው ምልክት ይህ ነው።የምጽፈውም እንዲህ ነው፣የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን›› በማለት መልእክቱ የራሱ መሆኑን በግልጥ ያስረዳ ነበር።

1 ወደ ሮሜ ሰዎች

ሮም ጥንት ሮምየ ትባል ነበር።አሁን የኢጣልያ ዋና ከተማ ስትሆን በቀድሞ ዘመን ግን ለሚታወቁት አገሮች ሁሉ ርዕሰ ከተማ ነበረች።መደበኛ ቋንቋቸው ግሪክ በመሆኑ ኢሊናርሚስ ወይም የግሪክና የሮም አገዛዝ እየተባለ ይነገር ነበር።

የንጉሰ ነገሥት ከተማ ስለሆነች የልዩ ልዩ ሰዎች መናገሻ አድርገው በተለይም አይሁዶች ምኩራብ ሰርተው ሃይማኖታቸውን አጽንተው ብዙ አሕዛብ እየመለሱ ይኖሩ ነበር።
የክርስትና ሃይማኖትም ፈጥኖ ወደ ሮም የገባው

ቅዱስ ጳውሎስ ከሮም ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ካላቸው ሀገሮች አንደ ኤፌሶን ቆሮንቶስ ተሰሎንቄ አቴና ባሉት ከተማዎች ትምህርቱና ተአምራቱ ተረድቶ ነበር።ከእነዚህም ሀገሮችም ሰዎች ሮም ሲሄዱ ትምህርቱንና ክርስትናውን ለሌላው ያስረዱ ስለነበር ነው።
በጳንጠቆስጤ(መንፈስ ቅዱስ በወረደበት) ዕለት በግል ፍላጎታቸው በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ከነበሩት ሮማውያን አይሁድ ውስጥ የቅዱስ ጴጥሮስን ስብከት ሰምተው አምነው ተጠምቀው ሄደው ቤተክርስቲያን ሮም ውስጥ ያቋቋሙ ሰዎች ስለነበሩ
ቅዱስ ጴጥሮስ ሮም ገብቶ ሲሰብክ ስለነበር

ቅዱስ ጳውሎስ በ 52 ዓ.ም ከአቴና ወጥቶ ወደ ቆሮንቶስ በሄደ ጊዜ በቀላውዲዮስ ቄሳር አዋጅ ከሮሜ ተሰደው የመጡ አቂለንና ሚስቱን ጵርስቅላን አገኘ።ከእነርሱም ጋር አንድ ዓመት ከሰድስት ወር በዚሁ በቆሮንቶስ ቆየ። አቂለና ጵርስቅላ በሮሜ ስለሚገኙ ክርስቲያኖች ለቅዱስ ጳውሎስ ነገሩት። ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን ሲጽፍ ከሮሜ ክርስቲያኖች መካከል የሚያውቃቸው ስለልነበሩ አቂለንና ጵርስቅላ ከከተማዋ ክርስቲያኖች ታዋቂ የሆኑትን የአንዳንዶቹን ስም ሰጥተውት መልእክቲቱን አዘጋጅቶ የክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን ዕቃቢት በነበረችው በፌበን እጅ በ 54 ዓ.ም አካባቢ ለካቸው። ሮሜ 16፥1
የሮሜን መልእክት የጻፈበት ምክንያት
ሮም ውስጥ የሚኖሩት ክርስትናን የተቀበሉት ወንጌል የሞታስተምረውን ፍቅርና ስላሞ ትተው በሥርዓት በባሕል አይሁድና አሕዛብ ባለመስማማት በጭቅጭቅ ይኖሩ ነበር።ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲሰማ ሁለቱን ወገኖች ለማስታረቅና በክርስትና እምነት ትምህርት እንዲኖሩ ለማድረግ መከፋፈል እንዳይኖር ይህችን መልእክት ጽፎለቸዋል።ሮሜ 1፥5-7
አንዳንድ የክርስትና እምነት ጠላቶች የሆኑ ክርስትያኖች በመንግስት ላይ ያምጻሉ ግብርም አይከፍሉም እያሉ የሀሰት ወሬ እያወሩ ክርስትያኖችን በሰጋ ለተሾሙ ሁሉ እንዲገዙ (እምነታቸውን እስካልነኩባቸው ድረስ) በነፍስ ግን ለክርስቶስ መገዛት እንደሚገባ ለማስረዳት ጽፎለቸዋል።ሮሜ 13፥5-7
ወደ ሮም እነርሱን ለመጎብኘት ከመሄዱ በፊት እየተማሩ እንዲቆዩና የጉዞውን ሁኔታም ለማመቻቸት ጽፎለቸዋል።
2.የመጀመሪያይቱ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

ቆሮንጦስ የአካያ ሁለተኛ ከተማ ስትሆን የምትገኘውም በግሪክ ውስጥ ነው።ይህች ከተማ ስመ ጥርና ታላቅ በንግድም የታወቀች የሀብታሞች መናኸሪያ ነበረች።ለምስራቁና ለምዕራቡ አለም ለንግድ አመቺ ስለሆነች የበለጸገች አገር ነበረች።በልዩ ልዩ አገሮች ከመጡ ህዝቦች ጋር ኗሪው በጣም ይበዛ ነበር።
መልእክቱን የጻፈበት ምክንያት
ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሮ ከሄደ በኋላ ከእስክንድርያ የመጣው አይሁዳዊ አጵሎስ ተጠምቆ ለአይሁድ ብሉይን ከሐዲስ እያስማማ ጥልቅ ጠንካራና ምስጢራዊ ትምህርቱን ሲያስተምር ብዙዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ጀምረው ነበር። በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመንም ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው የጌታችንን ትምህርቱን የሰሙት ተአምራቱን ያዩት እንዲሁም በኢየሩሳሌም እያሉ በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት አምነው የተጠመቁ ብዙዎች ነበሩ።እነዚህ በልዩ ልዩ ምክንያት ያመኑ ክርስትያኖች የሐሳብ መለያየትና የወገንተኝነት ስሜት ሰለጠናባቸው ከዚያም <<እኔ የጳውሎስ ነኝ እኔ የጴጥሮስ ነኝ እኔ የአጵሎስ ነኝ>>እያሉ ሲከፋፈሉና ሲለያዩ ክርስቶስ ተከፍሏልን? ጳውሎስስ ስለናንተ ተሰቅሏልን?ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?በመካከላችሁ መለያየት እንዳለ አሰማለሁ (1 ኛቆሮ 1፥12፣11፥17) መለያየት ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን የማይበጅ ነው።በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ችግር ከቀለዮጳ ቤተ ሰዎች ሲሰማ ይህችን የመጀመሪያ መልእክቱን ጻፈላቸው።
ከአምልኮ ጣዖት ከተመለሱ በኃላ የቆሮንቶስ ሰዎች የቀድሞ የአምልኮ ጣዖት ባህላቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓትና ትውፊት በመቀላቀል ይኖሩ ነበር።ለምሳሌ ወደ ቅዳሴ ሲመጡ ሁሉም ለየግሉ ወይንና ኅብስት ይዘው ይመጡና እስኪጠግቡ በልተው አስኪሰክሩ ጠጥተው እየተጨቃጨቁና እየተደባደቡ ቁርባን እንደፈጸሙ ይመስላቸው ነበር።ይባስሞ ብለው ወይንና ኅብስት ማምጣት ያልቻሉ ድሆችን እንደ እነርሱ አሳብ እንዳይቆርቡ ይከለክሏቸው ነበር።ቅዱስ ጳውሎስ ከጌታና ከቅዱሳን ሐዋርያት ያገኘነውን ሃይማኖት ሥርዓትና ትውፊት አብራርቶ ይመክራቸው ዘንድ ይህችን መልእክት ጻፈላቸው።
የቆሮንቶስ ሴቶች ወደ ፍርድ ሸንጎ ገብተው ሳይከናነቡ ያለሥርዓታቸውና ያለባህላቸው ለባሎቻቸው እያገዙ መሟገትን አዲስ ወግና ሥርዓት አድርገው ከካህናቱ ፈቃድ እየወጡ ቤተ ክርስቲያን ካልሰበክን ካልቀደሰን እያሉ ሲያስቸግሩ በዚህም የተነሳ <<ቤተክርስቲያኒቱ ነውረኛ ሴቶች የተሰበሰቡባትና ሥርዓት የሌላት ናት>> እየተባለች በዓለማዊያን ዘንድ እንዳትነቀፍ ቅዱስ ጳውሎስ ፀጉራቸውን እንዲከናነቡ ሥርዓቱን ትውፊቱን ጠብቀው እንዲኖሩ ሲል ይህን መልእክት ፃፈላቸው።
የቆሮንቶስ ሰዎች በዝሙት ኃጥያት ይታወቁ ነበር።በዚያን ዘመን <<ቆሮንቶሳዊ>>ማለት ዘማዊ የሚለውን ትርጉም ይዞ ነበር።ቅዱስ ጳውሎስም በእናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ይወራል።የዚያን ዓይነት ዝሙት በአህዛብ እንኳ የማይገኝ።ቆሮ 5፥1 በዚህም ዘማዊና በኃጥያተኛ ትውልድ መካከል በእኔ በቃሌ የሚያፍር ሁሉ የሰው ልጅ ደግሞ በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመጣ ጊዜ ያፍርበታል።ማር 4፥38 እያለ የተማረውን የወንጌሉን ቃል መሰረት በማድረግ ይህን መልእክት ከዝሙት ጠንቅ እንዲጠበቁ ጻፈላቸው።
የቆሮንቶስ ሰዎች ችግር በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እርስ በርስ መቀናናታቸው ነበር። <<እኔስ ከማን አንሳለሁ>> እያሉ ሁሉም ትንቢት ተናጋሪ ሁሉም ተርጓሚዎች ሁሉም ሰባክያን ሁሉም በልሳን ተናጋሪዎች ስለሆኑ ሁሉም ራሳቸውን ከፍ በማድረጋቸው ጭቅጭቅ ነበር።ለዚህም ሁሉ ችግሮች ክርስቲያናዊ መልሶችን ጽፎ አዘጋጅቶ በጢሞቲዎስ ፣በአስጢፋኖስ በፈርዶናጥስና በአካያቆስ እጅ ይህችን መልእክት በ 54 ዓ.ም ገደማ ለከለቸው። 1 ኛቆሮ 15፥2-58፣1 ኛቆሮ 16፥1-24

በመጨረሻም ቅዱስ ጳውሎስ ጥያቄ አዘል ደብዳቤዎችን ጽፈውለት ነበርና የተለያዩ ችግሮቻቸውን በመጠየቅና መልስ በማዘጋጀት በሃይማኖት ይጸኑ በምግባርም ያድጉ ዘንድ ይህን መልእክት ጻፈላቸው።።

3.ሁለተኛይቱ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን በሃይማኖት ልጁ በጢሞቴዎስ እጅ የመጀመሪያይቱን መልእክት ጽፎ ቢልክላቸውም ከኃጥያት ርቀው ንጽህና ጠብቀው መኖር አልተቻላቸውም።።ክፉ ምግባራቸውንም ቀጠሉ ይህን በልጁ የላከውን መልእክት እንዳልተቀበሉትና ተግባራዊ እንደማያደርጉትም በሰማ ጊዜ ከእንግዲህስ እኔ ብሄድ ይሻለል በማለት ወደ ቆሮንቶስ በሄደ ጊዜ እንዳልተቀበሉትና እንዳሳዘኑት በዚህ መልእክት ገልጿል።።2ኛ ቆሮ 2፥5-11,12፥2 የመጀመሪያ መልእክት ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጉት ለመርዳት ቲቶን ላከ።።2ኛ ቆሮ 2፥1-6 ከቅዱስ ጳውሎስ ጋርም በመቄዶንያ ተገኝተው ሲጠይቀው የለካቸው መልእክት ብዙዎችን በክፉ ሥራቸው እንዲጸጸቱ ንስሐም እንዲገቡ እንዲያውም የአባቱን ሚስት ያገባ እንዲለይ አድርገዋል በማለት ደስ የሚያሰኝ ወሬ ነገረው 1ኛ ቆሮ 7፥5-16 የቲቶን መልእክት ሲሰማ ቅዱስ ጳውሎስ እዚያው በመቄዶንያ እያለ ይህችን <<ሁለተይቱ>>የተባለችውን መልእክት ፃፈላቸው።።

ቅዱስ ጳውሎስ ሁለተኛይቱን መልእክት የጻፈበት ምክንያት

ንስሐ ገብተው በመመለሳቸው ለማመስገንና ለማጽናት

ከአይሁድ ወገን የሆኑ ሐሳውያን መምህራን ወደ ወጋቸውና ልምዳቸው ለመለወጥ በመሞከራቸው ብዙዎች ተታለው በትምህርታቸውም ተሰበው ስለነበር የሐሰተኞች መምህራን ትምህርት ወግና ስርዓት እንዳይከተሉ ለመምከር ፃፈላቸው።።

ቀድሞ በፃፋቸው መልእክት ተደናግጠው(በተግሣጻጽና፣በምክሩ) ሐዘናቸውም ከልክ ያለፈ ነበር።።ከልክ ያለፈ ሐዘናቸውንም ለማስታገስ የመልእክቱን የተገሳጹንና የምክሩን ጠቃሚነት አብራርቶ ጻፈላቸው።።

ይህች በ55 ዓ.ም አካባቢ በቲቶና ሉቃስ እጅ የተላከችበት ምክንያትም ስለ መልእክቷ እውነተኛነትና ስለቅዱስ ጳውሎስ ህይወት መመስከር የሚችሉ በመሆኑ ሲሆን በመጀመሪያዋ መልእክቱ ተግሳፅ ጠልተውት እንዳይቀሩ የመጀመሪያዋን መልእክትም እንዳያቃልሉ ሁለተኛይቱን የምስጋና ምክር አዘል አድርጎ ፅፎላቸዋል።።

የእርሱም ሥልጣን ከእግዚአብሔር እንደሆነ ለማስረዳት አብራርቶ ጽፏል።።

4.ወደ ገላትያ ሰዎች

ይህች ገላትያ የተባለች ሀገር በታናሿ እስያ አጋርዮስና አሊያስ በተባሉ ሁለት ወንዞች መካከል የምትገኝ አውራጃ ስትሆን ዛሬ የቱርክ መናገሻ ከተማ ናት።።ይህች የገላትያ ሰዎች መልእክት የተጻፈላቸው በ48 ዓ.ም ሲሆን የተለከለችውም በቲቶ እጅ ነው።።መልክቲቱም ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ የመጀመሪያዋ እንደሆነች ይነገራል።።ክርስትያኖች በእግዚአብሔር የባህርይ ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ያገኘነውን ጸጋና ክብር ከኃጢያት ባርነት ነጻ እንዴት እንደወጣን የምትናገር የምታስረዳ በመሆኗ <<የነጻነት መልእክት>> በመባል ትጠራለች።።

ይህን መልእክት የጻፈበት ምክንያት

የአይሁድ መምህራን የሐሰት ትምህርት ወጋቸውን ሥርዓታቸውን የገላትያ ሰዎች እንዳይቀበሉ የተማሩትን የሐዋርያት ትምህርት እንዲጠብቁ እንዲጸኑ

የአይሁድ መምህራን እንደ ሌሎች ሐዋርያት ጌታን አለየም ከቅዱሳን ሐዋርያትም እኩል አይቆጠርም ይሉት ስለነበር ይህንን የእርሱን ሐዋርያነትና ሥልጣኑን ያውቁ ዘንድ

ከሐዋርያት እንጂ ከጌታ ስለልተማረ ክብሩ ያነሰ ሰው እያሉ አይሁድ ካህናት የገላትያን ሰዎች ያወናብዱ ያስጨንቁ ስለነበር ይህን ለማስረዳት መገረዝ ጽድቅን ያስገኛል ጳውሎስ ራሱ ተገርዟል እናንተን ግን ጽድቅ እንዳታገኙ <<መገረዝ አይጠቅምም>>ይለችኋል እያሉ በዚህ ምክንያት ከእውነተኛዋ ሃይማኖት ሕግና ሥርዓት ያስወጧቸው ስለነበር ይህን ለማስረዳት

ሐዋርያት ከአይሁድ ተፋቅረው ሕገ አሪትን ጠብቀው ሥርዓተ አይሁድን አክብረው በኢየሩሳሌም እየኖሩ እርሱ ግን እናንተን አላዋቂ አድርጎ የሐሰት ትምህርትን ያስተምራችኋል በማለት የሚናገሩትን ለማስተማር ጽፎላቸዋል።።

5. ወደ ኤፌሶን ሰዎች

ኤፌሶን በሮሜ መንግስት ሥር በታናሿ እስያ በምዕራብ በኩል በከይስተር ወንዝ አጠገብ ወይም በኢጅያን ባሕር ዳር የምትገኝ የልድያ የወደብ ከተማ ነበረች።።ዛሬ በቱርክ ውስጥ የምትገኝ ሀገር ናት።።ቅዱስ ጳውሎስ በ58 ዓ.ም በኢየሩሳሌም ተይዞ ወደ ሮም በመሄድ በቀም አሥር በነበረ ጊዜ የኤፌሶን ሰዎች በእምነት በምግባር መጽናታቸውን በመስማቱ ይህችን መልእክት በደቀመዝሙሩ በቲኪቆስ እጅ ለካቸው።።

ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ታስሮ ሳለ ከጻፋቸው አራት መልእክታት የመጀመሪያይቱ ናት።። አራቱም መልእክታት ወደ ኤፌሶን ወደ ፊልጵስዮስ ወደ ቆላስይና ወደ ፊልሞና ናቸው።።

ወደ ኤፌሶን ሰዎች የጻፈበት ምክንያት

በልዩ ልዩ የዓለም ሰዎች ምቀኝነትና ተንኮል ኤፌሶንን ከለቀቀ በኃላ በክርስትያኖች ላይ የተለያየ ስም ሲያወጡባቸው ይሰማ ነበር።።ይህን በክርስቶስ የተሰጣቸውን አዲስ ስም እርሱም ክርስቲያን መባልን ታላቅ እንደሆነ ለማስረዳት

ከተማዋ ታላቅ እንደመሆኗ መጠን የዝሙት ኃጥያት በጣም ተስፋፍቶ ነበርና የዝሙትን አስከፊነት ገለጸላቸው

ባልና ሚስት የማይከባበሩ የጋብቻውንም ምስጢር ያልተረዱ ስለነበር ስለ ቅዱስ ጋብቻ ታላቅነት በክርስቶስና በቤተክርስቲያን እየመሰለ ጻፈላቸው።።ኤፌ 5፥32

አይሁድና አሕዛብ መለያየትን ያበዙ ስለነበር በክርስቶስ አንድ ስለመሆናቸው በግልጽ ጽፎላቸዋል።።

እንዲሁም የዲያብሎስን ተንኮል ባለማወቅ ተመልሰው ወደ ቀደም ግብራቸው እንዳይመለሱ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ በመልበስ ዲያብሎስን ለመቃወም እንዲችሉ ጻፈላቸው።። ኤፌ 6፥10-18

6 ወደ ፊልጵስዮስ ሰዎች

ፊልጵስዮስ በቀድሞ ዘመን አሊኢደስ ትባል ነበር።።የታላቁ እስክንድር አባት የመቄዶንያው ንጉስ ፊልጶስ ሁለተኛ ግዛቷን አስፋፍቶ በስሙ ፊልጵስዮስ ብሎ ሰይሟታል።።በ 60 ዓ.ም በሮም ታስሮ የጻፋት መልእክት ስለ ክርስቶስ አምላክነትና ሰው መሆን የምታስረዳ የሃይማኖት ት/ት ናት።።በተጨማሪም ክርስቶስ ከአብ ትክክል እንሆን፣በመስቀልም መሞቱን ትንሳኤውን ዕርገቱን መጥቶም ይህም ዓለም እንዲያሳልፍ ያለውን የዳግም ምድአቱን ነገር ትናገራለች።።

መልእክቷ የተጻፈችበት ምክንያት

ቅዱስ ጳውሎስ በሮም እስር ቤት በመሰቃይት ላይ መሆኑን የተረዱ የፊልጵስዮስ ምዕመናን ኤፍሮዲጡ በተባለ ወኪላቸው ያወጡትን አስትዋጽኦ አስይዘው ላኩት።።እርሱም በመከራው የማይዘነጉት በሃይማኖታቸው ጽኑ መሆናቸውን የሚያበረታታ ምስጋናና ምክርና ትምህርት ጻፈላቸው።።

/ፊልጵ 4፥14-20/

ራሳቸውን ከፍ ከፍ ያደርጉ ይመኩም ስለነበር ለዚህ መልስ ጽፎላቸዋል።።

እርሱ መታሰሩን የስሙ ቢጽ ሐሳውያን እኛም መምህራን ነን እያሉ በፊልጵስዮስ ክርስትያኖች ላይ ችግር ፈጥረውባቸው ስለነበር ለዚህ መልስ ጽፎላቸዋል

በተጨማሪም በከተማዋ የነበሩት አይሁድ እኛ የአብርሃም ዘር ነን እያሉ በአህዛብ ላይ ስለተመኩባቸው ከንቱ የሆነ ትምክህታቸውን እኔም እኮ የቢንያም ዘር ነኝ በማለት ለሁሉም መልስ በመስጥት ጽፎላቸዋል።።

7. ወደ ቆላስይስ ሰዎች

የቆላስይስ መልእክት በ 58 ዓ.ም አካባቢ ተጽፎ በቲኬቆስና አጥሲሞስ እጅ ተላከች።።

የተፃፈችበት ምክንያት

ቢጽ ሐሳውያን የፍልስፍና መርዛቸውን እየረጩ መሆኑን ስለነገሩት ከዓለማውያን የቢጽ ሐሳውያን ፍልስፍና እንዲጠበቁ የእግዚአብሔር ማንነትና የጌታችን አዳኝነት በመግለጥ ጻፈላቸው።።

የፊልሞና አገልጋይ አንሲሞስ የቆላስይስን የኑሮ ሁኔት ሰለነገረው ስለክርስቲያናዊ ኑሮ ሁኔታ አብራርቶ ጽፎላቸዋል።።

8. የመጀመሪያይቱ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

ተሰሎንቄ ቀድሞ የመቄዶንያ ዋና ከተማ ስትሆን ዛሬ የግሪክ ሁለተኛ ከተማ ናት።።የቀድሞ ስሟ ቴርማ ይባል ነበር ትጉሙም <<ፍል ውሃ>> ማለት ነው።።አጠገባዋ ከነበረው ከፍል ውሃ የተወሰደ ይመስለል ቅዱስ ጳውሎስ ይህችን የመጀመሪያይቱን መልእክት የፃፋት በአቴና ውስጥ ነው ይህችንም መልእክት በ 50 ዓ.ም አካባቢ ጽፎ በስልዋናስ (በዕብራይስጥ ሲላስ በተባለው) እና በጢሞቴዎስ በደቀመዝሙሩ እጅ ተላከላቸው።።

መልእክቲቱ የተጻፈችበት ዐበይት ምክንያቶች

ቀድሞ በብጥብጥ ምክንያት በድንገት ስለወጣ የተሰሎንቄ ክርስቲያኖችን ለማጽናናት ጠላት ሰይጣን እንዳይቃወማቸው የእርሱም ድካማ ከንቱ እንዳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ልጁን ጢሞቴዎስን አስይዞ ላከላቸው

ምንም እንኳን መከራና ስደት ቢበዛባቸውም ከሃይማኖት ያለ መናወጣቸው እርስ በርስም በፍቅር መኖራቸንነ ቅዱስ ጳውሎስንም ያልረሱ መሆኑን ሌሎችም አስደሳች ዜናዎች ነግሮት ስለነበር በዚህ ምክንያት ጻፈላቸው

የተሰሎንቄ ምዕመናን ክርክርን ያበዙ ስለነበር የተማሩትን ትምህርትና ሃይማኖት መጠበቅ እንጂ መከራከር እንዳይዙ ጻፈላቸው።።

ሰው ሲሞትባቸው የቀቢጸ ተስፋን ነገር እያነሱ ከመጠን በላይ ያለቅሱ ያዝኑ ተስፋ ይቆርጡም ነበርና ይህን የአሕዛብ ሥራ ክርስትያን ሊሠራቸው እንዳማይገባ ጽፎላቸዋል።።

እርስ በእርሳቸው የተፈቃቀሩ እየመሰላቸው አንዱ ሚስቱን ለሌላው በመስጠት የማይገባ ሥራ ይሰሩ ስለነበር ጽፎላቸዋል

በአጠቃላይ ፍፁማኑን የበለጠ ለማበረታት ተከፍሎ ልብ ያላቸውን ለማጽናት አንዳንዶችንም ለመገሰጽ ጽፎላቸዋል

9. ሁለተኛይቱ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

በተሰሎንቄ የሚገኝ አይሁድ ራሱን ቅዱስ ጳውሎስን ሲያስጨንቁት እንደነበር የተሰሎንቄ ክርስቲያኖችም ያስጨንቋቸው ነበርና የሚያጽናና መልእክቱን በ 51 ዓ.ም በጢሞቴዎስና በሲላስ እጅ ልኮላቸዋል።።

መልእክቲቱ የተጻፈችበት ምክንያት

በነገረ ምጽአት ዙሪያ ብዙዎች መናፍቃን ያስቸገሯቸው ስለነበር በሰማ ጊዜ ይህችን መልእክት ጻፈላቸው

የእርሱ መልእክት መሆኗን ስሙን በመጥቀስ እንዲቀበሉት አረጋግጦ ጽፎላቸዋል።።

10. የመጀመሪያቱ ወደ ጢሞቴዎስ

ጢሞቴዎስ የቅዱስ ጳውሎስ (በሃይማኖትና በትምህርት የወለደው) የበኩር ልጁ ነው 1ኛ ጢሞ 1፡2 ቅዱስ ጢሞቴዎስ በዕድሜ ወጣት ሲሆን በሃይማኖትና ምግባር የጸና መንፈሳዊ ቅናት ያለው ስለሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ዲቁና ሰጠው ለቅዱስ ጳውሎስ የሥራ ረዳት የመከራ አጋር ሆኖት በሄደበት ሀገር አብሮ እየዞረ ሲቆይ በልዩ ልዩ ሀገሮችም ብዙ መልእክታትን ሳይደክም እየተላከ መንፈሳዊ ግዳጁን ፈጽሟል።
በመጨረሻም ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስትያን ጳጳስ አድርጎ ሾሞታል።አንድ ጊዜ መታሰሩም ይናገራል ሐዋርያው ተልእኮውን እየፈጸመ እያለ በ96 ዓ.ም አካባቢ በሰማዕታትነት አርፏል።

መልእክቲቱ የተጻፈችበት ምክንያት

ከዚህ ቀድሞ ስለሥርዓተ ኖሎት ያልጻፈ ስለነበር በዚህ ምክንያት ጻፈለት
በኤፌሶን ከተማና በአካባቢዋ ባሉት ሀገሮች የተሰፋፋውን የግኖስቲኮችን ፍልስፍና አጠቃላይ ሁኔታ ክርስቲያናዊ ምላሽ በመሰጠት ጻፈለት
ጢሞቴዎስን ለማበረታት ጽፎታል

11.ሁለተኛይቱ ወደ ጢሞቴዎስ

ይህች መልእክት ለሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛው እሥራቱ በሮም ወኃኒ ቤት እያለ የጻፋት የመሰናበቻ መልእክቱ ናት።በዕድሜ የ74 አመት አዛውንት ሲሆን በጨለማ እስር ቤት ከአንድ ዓመት በላይ በመኖሩ ዓይኖቹ ደክመው ጊዜ ሞቱም ደርሶ እንደነበር ታውቋል መልእክቲቱን በ66 ዓ.ም ጽፎ በአንክሮሎስ እጅ ልኮታል።ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን ከጻፈ ከ1 ዓመት ከ3 ወር በኃላ በሰማዕትነት አርፏል።

መልእክቷ የተጻፈበት ምክንያት

ለጢሞቴዎስ መሰነባበቻ መልእክት ጽፎለታል
የመከረውን ምክር በድጋሚ ለማጽናት ጽፎለታል
ከሐሰተኞች መምህራን ሕዝቡን እንዲጠብቅ ለማሳሰብና ለመሞከር

12.ወደ ቲቶ

ቲቶ በቅዱስ ጳውሎስ ስብከት ስለመነ በሃይማኖት የወለደው ልጁ ነው።ሐዋርያዊ ተልእኮውንና መንፈሳዊ ትጋቱን ተረድቶ ቅዱስ ጳውሎስ በሜድትራንያን ባሕር አጠገብ በምትገኝ ደሴት የቀርጤክስ ቤተ ክርስትያንን እንዲያስተዳድር በውስጧ አይሁድ ለሚኖሩባት ሀገር ሊቀጳጳስ አድርጎ ዲያቆናትንና ቀሳውስትን እንዲሾም እንዲያስተማር ሾሞታል።ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን በ63 ዓ.ም አካባቢ አርጣ በተባለው ደቀመዝሙር ጽፎታል።

መልእክቷ የተጻፈችበት ምክንያት

የቀርጤክስ አብያተ ክርስቲያናት በልዩ ልዩ ቦታዎች ተቋቁመው በቁጥር በዝተው ቢገኙም በጣም ያልተደራጁ የወንጌል አገልግሎትም በአንዳንድ ቦታዎች ያልተዳረሰ መሆኑን ተረድቶ ነበር ወንጌል እንዲያስፋፋባቸው በአስተዳደርም በኩል መመሪያ በመስጠት ይህችን መልእክት ጻፈለት።
የቀርጤክስ ሰዎች ጠባያቸው የከፋ ስማቸው የጠፋ ነበርና መከራ እንዳይበዛበት መከራ ቢመጣበትም እንዲታገስ አስቀድሞ የሰዎቹን ጠባይ በማስገንዘብ አገልግሎቱም እንዳይጎዳ ጽፎታል።
በሀገሪቱ ብዙ ዓለማውያን ሰዎችና መናፍቃን ስለነበሩ ከእነርሱ እንዲርቅ ምእመናኑም ግንኙነት እንዳይኖራቸው በክፋ ትምህርታቸው እንዳይሳቡ ክህደታቸውን እየገለጠ ጽፎለታል።
በመጨረሻም በትምህርትና በግብረ ገብነት የታወቁትን በመምረጥ የቤተ ክርስትያን ጠባቂ የሚሆኑትን እንዲሾም እርሱም በትጋት እንዲያገለግልና እንዲጸና ይህችን መልእክት ጽፎለታል።

13.ወደ ፊልሞና

ሀገሩ ቆላስዮስ የሆነው ፊልሞና ደግ ባለጸጋ ሲሆን ወደ ኤፌሶን ለሥራ በሄደ ጊዜ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን ስብከት ሰምቶ ከእነቤተሰቡ አምኖ ተጠምቋል።ይህ ሰው አብርሃማዊ ሕይወት የነበረው ክርስትያኖችን በቤቱ እየተቀበለ ያበለ ያጠጣና ያሳድርም ነበር ቅዱስ ጳውሎስንም ይንከባከበው ለአገልግሎቱም የሚያስፈልገውን ያደርግ ነበር ከኤፌሶን ወደ ቆላስይስ ተመልሶ አናሲሞስ የተባለ አገልጋይ ነበረው ይህ አገልጋይ የሚጠብቃቸው የፊልሞና ከብቶች ሲጠፋበት አገሩን ቆላስይስን ትቶ ወደ ሮሜ ሲገባ ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያ አስራቱ ላይ ሳለ አናሲሞስ የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት ሰምቶ አምኖ ተጠመቀ።ወደ ሮሜ ለምን እንደመጣም የደረሰበትን ሁኔታ ሲነግረው ይህች የማስታረቂያ መልእክት ለፊልሞናና ለሚስቱ ለአፋብያ እንዲሁም ለልጁ ለአክርጳስ ጽፎ በአናሲሞስ እጅ በ60 ዓ.ም አካባቢ ላከላቸው።

መልእክቷን የጻፈበት ምክንያት

አናሲሞስ ከፊልሞና ተጣልቶ በስደት ወደ ሮሜ እንዳይቀር ይህችን መልእክት አሲዞ ላከው።
ፊልሞናና አፋብያ በአናሲሞስ መጥፋት እንዳያዝኑ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ከመወጣት ወደ ኋላ እናዳይሉ ከብቶችን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የተጠመቁ ክርስትያን ወገኖችን ሁሉ እያስተማረ ከእነርሱ ጋር ሆኖ ያበረታቸው ዘንድ መልእክቱን በእጁ አስይዞ ልኮላቸዋል።
ስለጠፋው የፊልሞና ንብረትና በዚህ ምክንያት በክርስቲያኖች መካከል ልዩነት እንዳይኖር አጠቃላይ ሁኔታ ጽፎለታል።

14.ወደ ዕብራውያን ሰዎች

ዕብራውያን(ከአብርሃም ቅድመ አያት) በአባታቸው በዔቦር ዕብራውያን የተባሉ በኢየሩሳሌም ያሉ ምዕመናን እና አይሁድ ናቸው።ይህ ስም በሐዲስ ኪዳን ዘርን ወይም ዜግነትን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕግ በመጠበቅ ስለሚገኝ ጽድቅ የሚያስረዳ ነው።

ይህች መልእክት የተጻፈችው ሮማውያን የኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ካፈረሱበት ከ 70 ዓመት በፊት ነው።መልእክቷም የሙሴን ሕግ፣የቤተመቅደሱን አገልግሎት የነገስታቱንና የመሳፍንቱን ታሪክ ትውፊትና ሥርዓት ጠንቅቀው የሚያውቁ አይሁዶች በሚበዙባቸው ሀገሮች በኢየሩስአሌም በኢጣሊያና በእስክንድሪያ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች (ከአይሁድነት ወደ ክርስትና ለተመለሱ) የተጻፈች ናት።

የዚህች መልእክት ፀሐፊ ማነው? የሚለው ጥያቄ ለሔሬኔዎስ ለሂፖሊተስ ለጠርጡለስና የማርቲን ሉተርን ሀሳብ መሰረት ላደረጉ ለብዙዎች ነገረ መለኮት ምሁራን አጠጠያያቂ ሆኖ ቆይቷል። ብዙዎች ይህ መልእክት የቅዱስ ጳውሎስ አይደለም ለማለት የሚገልጿቸው ምክንያቶች፡-

አጻጻፉ ከቅዱስ ጳውሎስ የአጻጻፍ ባሕርይ የተለየ ነው

መልእክቱ የተላከው ለዕብራውያን እንደመሆኑ መዘጋጀት የነበረበት በዕብራይስጥ ቋንቋ ነበር ነገር ግን መልእክቱ የተዘጋጀው በግሪክ ቋንቋ ነው

በመልእክቱ መጀመሪያ ላይ በሌሎች መልእክቶች የተለመደውን የሰላምታ አሰጣጥ አልተጠቀመም

የእርሱ ቢሆን ስሙን ሊገልጽ ይችል ነበር...የሚሉ ናቸው።

ከ 185-240 ዓ.ም የነበረው አርጌንስ ከ 150-215 ዓ.ም የነበረው ቀሌምንጦስ ዘእስክንድሪያ ዮሐንስ አፈወርቅ ቅዱስ አትናቴዮስና ሌሎችም የቤተ ክርስትያንን ትውፊት መሠረት በማድረግ ቅዱስ ጳውሎስ እንደጸፈው ተናግረዋል።ታላቁ የቤተ ክርስትያን ታሪክ ፀሐፊ ቅዱስ አውሳብዮስም በ 340 ዓ.ም የዕብራውያን መልእክትን ከቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ዝርዝር ውስጥ አካቶታል።በ 397 ዓ.ም በቅርጠግና(chartage) ላይ የተደረገ የቤተ ክርስትያን ጉባኤም የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት በቀኖና ደንግጎ አስቀምጦታል።

እነዚህ የቤተ ክርስትያን ሊቃውንት መልእክቱ የቅዱስ ጳውሎስ ነው ሲሉ በመረጃና ከላይ ያልቀበሉትን ሰዎች ጥያቄ መልስ እንደሚከተለው በመስጠት ነው።

የአጻጻፉ ባሕሪ የተለየው ቅዱስ ጳውሎስ ጥልቅ የኦሪት እውቀት ስላለው መልእክቱ ተቀባይነት እንዲኖረው ከሌሎቹ መልእክታት ለየት አድርጎታል።

ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራይስጥ ቋንቋ ከጻፈው በሃላ ወደ ግሪክ ቋንቋ የተረጎመው ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ከሌሎቹ መልእክቶቹ ሁሉ በእርሱ እንደተጻፈ ማረጋገጫ አድርጎ የተናገረው የሰላምታ ቃል በዚሁ መልእክትም ተገለጽዋል። ዕብ 13፣25

ጥልቅ ዕውቀት ያለው ለአጻጻፍና ለአቀራረቡ ምንም አይነት ችግር የሌለበት ቅዱስ ጳውሎስ የዕብራውያን ሰዎች ከእግዚአብሔር ተለይተው እንዳይቀሩ ሕጉን ሥርዓቱንና ትውፊቱን እንዲጠብቁ በሚገባቸው አሪታዊ አገላለጽ እንዲመልሱ ለማድረግ የጻፈላቸው በመሆኑ ነው።

ስሙን በመልእክቱ ውስጥ ያልገለጸበት ምክንያት፡-

አስቀድሞ የእርሱ ተማሪና ለወጋቸው ቀናተኛ ስለነበር ስሙን ቢያዩ ኖሮ ለበቀል ስሜት መልእክቱን ስለማይቀበሉት ነው።

ዘመኑ አይሁድ በሮማውያን ላይ ለማመጽ የተዘጋጁበት ጊዜ ስለነበር በሮም መንግስት የቁም እስረኛ ላይ በመሆኑ በግዞትና በጦርነት ጊዜ መተማመን ስለማይኖር ሮማውያን ካወቁ ወገኖቹን ያነሳሳብናል ብለው እንዳይቃወሙትና ምክንያት አግኝተው እስራቱን ወደ ፖለቲካ እንዳያዞሩበት።

ቀድሞውንም ያሳሰሩት አነርሱ ናቸውና ገና ስሙን ሲያዩ ኦሪት አለፈች ሊለን ይሆናል ብለው ከማንበብ እንዳይከለከሉ፣ነጻ ሆነው መልእክቱን አንብበው ወደ ክርስትና ያልመጡትን ለማምጣት የመጡትን ደግሞ ለማጽናት ጽፎላቸዋል።

በመጨረሻም <<ወንድማችን ጢሞቴዎስ እንዲፈታ ዕወቁ>> ከኢጣልያ የሆኑት ሰላምታ ያቀርቡላቸዋል። ዕብ 13፣23፣13፣24 የሚሉት መረጃዎች ፀሐፊው ከጢሞቴዎስ ጋር ያለውን ቅርብ ግንኙነትና በኢጣልያ በአገልግሎት እያለ የጻፈው መሆኑን ያስረዳል በማለት መሠረታውያን የቤተ ክርስትያን አባቶች በእነዚህና በመሳሰሉት መረጃዎች መስክረዋል። ይህች መልእክት በመጀመሪያዋ እስራቱ በሮሜ እያለ በ 60 ዓ.ም አካባቢ ጽፎ በጢሞቴዎስ እጅ ልኮላቸዋል።

መልእክቲቱ የተጻፈችበት ምክንያት

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር መምጣት እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሃ ፈሳሽ አለመሆኑን ለማስረዳት

ኢየሱስ ክርስቶስ ከነቢያት ከመላእክት እንዲሁም በክህነቱ በመሥዋዕቱ በሕጉ በኪዳኑ በሚያወርሰን መካነ ዕረፍት ወ.ዘ.ተ...የሚበልጥ መሆኑን ለማስረዳት

በወቅቱ ክርስትና በተቀበሉ ግሪክኛ ተናጋሪ በነበሩ አይሁድ ላይ ስደትና መከራ ስለጸናባቸው በእምነታቸው ጸንተው መከራውን ታግሰው የጽድቅ አክሊል ተካፋዮች እንዲሆኑ ለመምከርና ለማጽናት

በኦሪት ሕግ ብቻ ይኖሩ የነበሩ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ያልተመለሱ ብዙ አይሁዳውያን መልእክቱን አንብበው ይመልሱ ዘንድ ጽፎላቸዋል።

ሰባቱ መልእክታት

የቅዱስ ጴጥሮስ 1ኛ እና 2ኛ፤ የያዕቆብ የዮሐንስ 1 2 እና 3 የይሁዳ እነዚህ ሰባቱ መልእክታት በመባል ይታወቃሉ።እነዚህም ሰባቱ መልእክታት የተባሉበትም ምክንያት ለአንድ ሰው ወይም ለአንድ ቤተ ክርስትያን ብቻ ስላልተጻፉ ማለትም ለአብያተ ክርስትያናት ስብስቦች የተላኩ መልእክታት መሆናቸው ነው።

መልእክታቱም ሲላኩ ከአንድ ቤተ ክርስትያን ይደርስና ለምእመናኑ ከተነበበና ከተረዱ በኋላ ሀብት ያላቸው አጽፈው ቅጅ ያስቀሩና ዋናውን ለዋሳቸው ወይም ለሌላ ቤተ ክርስትያን እንዲደርስ በማሰብ ያስተላልፉና ይጠቀሙበት ነበር።

.የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክታት

1. የመጀመሪያይቱ የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የመጀመሪያይቱን መልእክት የጻፈው በመከራና በስደት ጊዜ ነው።መልእክቷ የተጻፈችው በቅዱስ ጴጥሮስ ነጋሪነት በስልዋኖስ እጅ ሮም (ባቢሎን) ውስጥ በ 60 ዓ.ም አካባቢ እንደሆነ ይነገራል።

መልእክቷ የተጻፈችበት ምክንያት

መልእክቱ ያለምንም ምክንያት ሊደርስ ከሚችል ፈተናና ችግር ጌታችን እንደታገሰ እንዲታገሱ ለመምከር

በንጹህ ደም የተዋጁ ስለሆኑ በንጽህና እንዲኖሩ በክርስቶስ ላይ እንደተመሰረቱ ካህናትና ቤተመቅደስ እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ

የዘለአለም ህይወት እንዳላቸው ያውቁ ዘንድ

ከሥጋ ምኞት እንዲጠበቁ

ከምእመናን ሁሉ ጋር ባላቸው የሚገባ ግንኙነት ትሁታን እንዲሆኑ ጽፎላቸዋል።

2. ሁለተኛይቱ የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት

ይህች መልእክት በቅዱስ ጴጥሮስ ተጽፋለች።የጻፈላቸውም በኒሮን አዋጅ ተይዞ በእሥራት እያለ በ 67 ዓ.ም አካባቢ ነው።

መልእክቲቱ የተጻፈችበት ምክንያት

ሐሰተኞች ነቢያትና ሐሰተኞች መምህራን

ለዚህ ዓለም ሠራኢ መጋቢ የለውም

ትንሣኤ ሙታን የለውም

ሳልፈተ ሰማይ ወምድር የሌም

አንድ ጊዜ ካመኑ ምግባር አይጠቅምም እያሉ በክህደት ትምህርታቸው ያለመኑትን ምግባር ያላቸውን ክርስትያኖች ያውኳቸው ስለነበር

ለእነዚህ ሰዎችና ለጥያቄዎቻቸው መልስ በመስጣት ይህን መልእክት ጽፎላቸዋል።

የሚገባውን የክርስትያን አኗኗር ሕይወትና መሠረቱ የቤተ ክርስትያን መሥራች የቅዱሳን ሁሉ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ያወቁና በክርስትና እምነት ይጸኑ ዘንድ ጽፎላቸዋል።

ያመኑት ሰዎች ይህን መልእክት ተረድተው በሃይማኖት በምግባር እንዲኖሩ ሌሎች ምግባር ሃይማኖት የሌላቸው አንብበው ተረድተው ይመለሱ ዘንድ ይህን መልእክት ጽፏል።

3. የመጀመሪያው የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት

ቅዱስ ዮሐንስ በኤፌሶን ሳለ በ 96 ዓ.ም አካባቢ እንደጻፈው ይገራል።

መልእክቷ የተጻፈችበት ምክንያት

መናፍቃን

ትንሳኤ ሙታን የለም

ከጥምቀት በኋላ የምንሰራው ኃጢአት አይደለም ከዚህ የተለየ ምግባርም አያስፈልግም

ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ አልተገለጠም

(ግኖስቲኮች) (አዋቂዎች) ነን በማለት ያለ አነርሱ እውነተኛ ክርስትያን እንደሌለ በማሰብ ለእኛ የመጨረሻ እውቀት ተገልጦልናል።ስለዚህ ያለ ሕግ መኖር እንችላለን የሚሉትን የተለያዩ ጥያቄዎቻቸውን አንድ በአንድ በመመለስና በማስረዳት ጽፎላቸዋል።

ይኸውም

1. ስለትንሣኤ ሙታን መኖርና የጌታችንን መለኮታዊ ክብርና ምሥጢረ ስጋዌውን በማረጋገጥ

2. ማንኛውም ክርስትያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መጠበቅ እንዳለበትና ድኅነት የሚገኘውም ለእርሱ አምልኮ በማቀረብ እንደሆነ

3. ክርስቶስ የሰውን ልጅ ስለመውደዱና እርስ በርስ መዋደድ ዓይነተኛ የክርስትና ምልክት እንደሆነ

4. ኃጥያቱን የተናዘዘ የእግዚአብሔርን ምህረት የሚያገኝ እንደሆነ

5. የሐዋርያት ትምህርት አጽንተው መያዝ ያለባቸው ስለመሆኑ

6. ስለ እውቀት ምንነት አጠቃላይ ሁኖታ አስረድቶ ከፍጥሞ ደሴት ግዞቱ ሲወጣ ለመናፍቃን የክህደት ትምህርት መልስ ይሆን ዘንድ ጽፎላቸዋል።

4.ሁለተኛይቱ የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት

ይህች መልእክት ሐዋርያው ዮሐንስን በኤፌሶን ከተማ በ 96 ዓ.ም አካባቢ ለአንዲት ሴትና ቤተሰቧቿ ከመናፍቃን ትምህርት እንድትጠበቅ የጻፈላት መልእክት ነው።

ይህች ሴት በኤጅያን ደሴቶች አንዱ ቀለብ አየተሰፈረለት የነገስታቱን ልጆች የምታሳድግ ሮምና የተባለች ሞግዚት ነበረች ዮሐንስና ደቀመዝሙሩ አብሮኮሮስ በዚህች ደሴት ለማስተማር ፈልገው <<የሮምና የአባታ ባሮች ነበርን ለብዙ ዘመናት ጠፍተን ስንኖር አሁን መጣን>> እያሉ በደሴቷ አስወሩ።ከንቱ ውዳሴ የሚያጠቃት ሴት ነበረችና ወደ ቤቷ ወስዳ ቅዱስ ዮሐንስን እንጨት ፈላጭ ደቀመዝሙሩ አብሮኮሮስን ደግሞ ውሃ ቀጅ አደረገቻቸው።

አንድ ቀን ከምታሳድጋው አንዱን ይዛ ወደ ቤተ ጣዖት ስትገባ ዮሐንስና አብሮኮሮስ ተከትለዋት ገቡ።ያን ጊዜ በቤተ ጣዖቱ ያደረው ሰይጣን እነ ቅዱስ ዮሐንስን ሲያይ የቤቱን እቃ በማተረማመስ ወጣ።በዚህ መካከል አስከትላው የነበረው ልጅ በድንጋጤ ሞተ ያን ጊዜ ‹‹የእናንተ መምጣት ነው ለዚህ ሁሉ ያበቃኝ›› ብላ ደበደበቻቸው ቅዱስ ዮሐንስም ‹‹አስነሱልኛ አትይምን?›› ሲል መለሰላት ‹‹ያሁኑ ይባስ! ከመቼ ወዲህ ነው ደግሞ የሞተ ሰው የሚነሳው ብላ የበለጠ ተቆጣች›› ያን ጊዜ እነ ቅዱስ ዮሐንስ ጸልየው አስነሱላት።በዚህ ተአምር ምክንያት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምና ተጠምቃለች።ወድያውኑም በቤቷ የምእመናን ጉባኤ ተጀምሮ እርሷንም ለዚህ እመ መኔት አድርገው ሾመዋታል።ቅዱስ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት በታሰረ ጊዜ በመናፍቃን የሐሰት ትምህርት የተነሳ በቤቷ ያለው የክርስቲያኖች ጉባኤ መከፋፈል ደረሰበት ጠብ ክርክር ተነሳ ይህን የሰማው ቅዱስ ዮሐንስም የድሮ ኑሮዋን ወይም ህይወቷን አስታውሳ የአሁኑን መከራ እንድትረሳ አመመኔትነቷም ለትአቢት እንዳይሆንባት ታላቁ ሐዋርያ በድሮ ስሟ ‹‹አመቤቱ›› እያለ በትህትና በመጥራት አጠቃላይ ሁኔታውን ጽፎላታል።

መልእክቲቱ የተጻፈችበት ምክንያት

በመጀመሪያቱ የዮሐንስ መልእክት ላይ የተገለጹት መናፍቃን ምእመናንን ለማስካድ ይጣደፉ ስለነበር የሐሰት ትምህርታቸውን በመቃወም እውነተኛዋን የክርስትና ትምህርት እንዲያጸኑ ነው።

5.ሶስተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት

መልእክቱ የተላከችው ጋይዮስ ለተባለ ሰው ነው።በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ጋይዮስ በመባል የሚጣወቁ 3 ሰዎች ሲኖሩ ይህችን መልእክት ለማድረስ የታደለው በሮሜ 16፥23 ለተጠቀሰውና በአብርሃማዊ እንግዳ አቀባበል በረከት ለደረሰው ጋይዮስ ነው።

መልእክቱን የጻፈበት ምክንያት

ጉባኤው ይሰፋ ዘንድ እንግዳ እየተቀበለ የሚያገለግለውን ጋይዮስን ለማመመስገን

በቤተክርስትያን ውስጥ መለያየት እንዳይኖር ለመምከር

ዲዮጥራጢስን ለመገሰጽ ፅፏል

6.የሐዋርያው የቅዱስ ያዕቆብ መልእክት

በሐዲስ ኪዳን ያዕቆብ በመባል የሚጠሩ ቅዱሳን አባቶች አሉ።

ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ (የዮሐንስ ወንድምና ከሚስጥር ሐዋርያ አንዱ)

የይሁዳ(ሐዋርያው) አባት ይህም ታዴዎስ ወይም ልብድዮስ እየተባለ የሚጠራው

የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስትያን መሪ የጌታ ወንድም የተባለውና ይህን መልእክት የጻፈው ነው።

መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት

መልእክቱ የተላከለቸው ሰዎች (ተበትነው ይኖሩ ለነበሩና ክርስትናን ለተቀበሉ አይሁድ) ተበታትነው ስለነበር በያሉበት ለማበረታታትና ለማጽናናት

ስደትና መከራ ይበዛባቸው ስለነበር በደረሰባቸው መከራና ስደት ተሰፋ እንዳይቆርጡና ዋጋ እንደሚያገኙ እንዲሁም ክብር እንዳለው ለመምከር

በቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት የተጻፈውን የነገረ ሃይማኖት ትምህርት እንዲያጸኑና በተጨማሪም ደግሞ ምግባር በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ለማስረዳት

7.የሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳ መልእክት

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የይሁዳ ተብለው የሚጠሩ ብዙ ሰዎች አሉ።የዚህ መልእክት ጸሐፊ የጌታ ወንድሞች ከተባሉት አንዱ ነው።

የያዕቆብን መልእክት የጻፈው የያዕቆብ ወንድም የተባለው የዮሱፍ ልጅ ሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳ ነው።ሁለቱም ወንድማማቾች ከጌታ ትንሣኤ በኃላ ያመኑና የሰበኩ ናቸው።

መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት

በሐሰተኞች መምህራን ትምህርት ችግር የደረሰባቸው ክርስቲያኖች ከክህደት ትምህርት ርቀው ከቅዱሳን ሐዋርያት የተረከቡትን የቀና የክርስትና እምነት አጽንተው እንዲይዙ ለማድረግ

ተመክረው ያልሰሙ ሰዎች እንደሚቀጡ የሚመለሱት ደግሞ እንደሚድኑ ለማሳወቅ ተጽፏል።

የቅዱስ ዮሐንስ ራእይ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልአኩ አማካኝነት በራዕይ በገለጸለት መሠረት የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊ ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው።ዮሐንስ ለቁሳር ድምጥያኖስ ሐውልት የሚሰግዱትን በመቃወም በንጉሱ ትእዛዝ ወደ ፍጥሞ ደሴት ተጓዘ።

የቅዱስ ዮሐንስ ራእይ በግሪክ ቋንቋ ‹‹አቡቀለምሲስ›› በመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ዘንድ ደግሞ ‹‹የሐዲስ ኪዳን የትንቢት መጽሐፍ›› በመባል ይታወቃል።ፍፁምነትን ለመግለጽ በሰባቱ የእስያ አውራጃ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ቢልም ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የተላከ መጽሐፍ መሆኑ ይታመናል።የዮሐንስ ራእይ የትንቢት መጽሐፍ ሲሆን ከስነ ጽሑፍ ሁኔታ አንጻር በአጠቃላይ ሦስት አይነት አቀራረብ አለው።

የጽሑፉ መግቢያና መደምደሚያ በማሳሰቢያ መልክ የቀረበ ነው

በተለይ ምዕራፍ ሁለትና ሦስት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት አለቃዎች የተላኩና በደብዳቤ መልኩ የቀረቡ ናቸው።

ሌላው አብዛኛው ክፍል በራዕይ መልክ የቀረበ ሲሆን በብሉይ ኪዳን የመቅደስ ሥርዓትና ንዋየ ቅድሳት ወ.ዘ.ተ ምሳሌነት ለዮሐንስ የታየ ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ ራዕዩን የጻፈበት ምክንያት
ብዙዎች የፋርስ ነገስታት የሰሩት የአርጤምስ ጣዖት በማምለካቸው ሁሉንም ሊያስተምር
መለእክት(አለቃዎች) ተብለው ለተጠሩ በታናሿ እስያ ለሾማቸው ሰባት ሊቃነ ጳጳሳት በቤተ ክርስትያን መልካም አስተዳደርና ሕይወት ዙሪያ ለመምከር
የክርስቲያኖችን ሰማያዊ ሕይወትና የመለእክትን የጻድቃንን የሰማዕታትን ክብር ለማሳየት ጽፏል፡፡
የጥጦስን የሐሳዊ መሲሀን የምጽአትንና የመንግስተ ሰማያትን ነገር የገለጸለት እግዚአብሔር ጸፍ ብሎት ለማስረዳት ጽፏል፡፡